# ሥርዓተ ቤተ-ክርስቲያን


<u>አዘጋጅ</u>

**ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሊቃውንት ጉባኤ አባል




<u>አሳታሚ</u>

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

**ማኅበረ ቅዱሳን**

**አዲስ አበባ**

1993 **ዓ.ም**



«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷል፡፡ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ህያዋን ይሆናሉና፡፡» 1ኛ ቆሮ. 15.20-21



**«እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ በእርሱ ለእኔ ታላቅ ሥራን አድርጓልና።» ሉቃ.** 1.49

# የአርእስት ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

4. **ሥርዓተ ቤተክርስቲያን**........................................................................88

- የቤተክርስቲያን አተካከልና አሠራር .....................................................................92
- ሥርዐተ ጥምቀት .....................................................................................95
- ሥርዓተ ሜሮን .......................................................................................100
- ሥርዓተ ቁርባን.......................................................................................102
- ሥርዓተ ንስሐ.........................................................................................111
- ሥርዓተ ክህነት .......................................................................................112
- ሥርዓተ ተክሊል .....................................................................................128

# ሥርዓተ ቤተክርስቲያን

ከሊቀ ካህናት ከንፈ ገብርኤል አልታየ
የሊቃውንት ጉባኤ አባል

## መ ቅ ድ ም

ሥርዓት ማለት «ሠርዐ» ሠራ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ የምዕላድነት ዘር ያለው ስም ነው። ትርጉሙ ሕግ ደንብ አሠራር መርሐ ግብር ማለት ነው።

ቤተክርስቲያን ማለትም ሁለት ትርጉም ያለው በስምና በባለቤትነት የተቀመጠ ስም ነው። አንደኛው ትርጉም የክርስቲያን ቤት፣ የክርስቲያን መሰብሰቢያ፣ የክርስቲያን መገናኛ ማለት ነው። ይህም ማለት ክርስቲያኖች በአንድነት በመሰብሰብ የሚጸልዩበት ሥጋወደሙን የሚቀበሉበት የሚሰግዱበት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት ቦታና የጸሎት ቤት ማለት ነው። /ኢሳ.56÷7 ፣ኤር.7÷10-11 ፣ ማቴ.21÷13፣ ማር.11÷17 ሉ.ቃ.19÷46/

ሁለተኛው ትርጉም የክርስቲያን ወገን ክርስቲያን የሆነ ሁሉ የሚጠራበት ስም ነው። «ቤተ እሥራኤል፣ ቤተ ያዕቆብ፣ ቤተ አሮን» ሲል የእሥራኤል ወገን፣ የያዕቆብ ወገን፣ የአሮን ወገን ማለት እንደሆነ ቤተክርስቲያን ማለትም የክርስቲያን ወገን ማለት ነውና። /መዝ.117÷3፣ 113÷1፣ ማቴ.16÷18፣ 18÷17፣ የሐዋ.18፣ 22፣ 20÷28/

በአጠቃላይ አነጋገር የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ወይም ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ሲባል ግን የቤተክርስቲያን ሕግ የቤተክርስቲያን ቀኖና የቤተክርስቲያን የአሠራር መርሐ ግብር ማለት ነው።

የሥርዓተ ቤተክርስቲያን ትምህርት ጥልቅና ምጡቅ የሆነውን የቤተክርስቲያንን ሥርዓት በመጠኑም ቢሆን፣ ለመማርና ለማስተማር ለማወቅና ሥርዓቱን ለመፈጸም ለሚችሉ ሁሉ የሚረዳ ነው።

## የሥርዓተ ቤተክርስቲያን ምንጮች

1. መጻሕፍተ ብሉያት
2. መጻሕፍተ ሐዲሳት
3. የሐዋርያት ሲኖዶስ
4. ሥርዓተ ጽዮን
5. አብጥሊስ

6. ትእዛዝ
7. ዲድስቅልያ
8. ፍትሐ መንፈሳዊ
9. የሦስቱ ጉባኤያት /የኒቅያ፣ የኤፌሶን፣ የቁስጥንጥንያ/ ውሳኔዎች
10. ሥርዓተ ቤተክርስቲያን
11. ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን በየጊዜው የተነሡት የቤተክርስቲያን ሊቃውንት የጻፏቸው ልዩ ልዩ የሥርዓት መጻሕፍት ናቸው::

# መግቢያ

ለሥርዓተ ቤተክርስቲያን መሠረቱ ሥርዓተ ደብተራ ኦሪት፣ ሥርዓተ መቅደስ ኦሪት፣ ሥርዓተ ካህናተ ኦሪትና የመሳሰለው የብሉይ ኪዳን ሥርዓት መሆኑ ግልጽ ነው:: የደብተራ ኦሪት፣ የመቅደስ ኦሪት አሠራር ለቤተክርስቲያን ሕንጻ አሠራር ምሳሌነት አለው:: ደብተራ ኦሪት፣ መቅደስ ኦሪት በሦስት ክፍል ይሠራ እንደነበር ሁሉ ቤተክርስቲያንም ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስት፣ መቅደስ በሚል በሦስት ክፍል ትሠራለች /.ዘጸ.36 /

የመጀመርያው ክፍል ቅኔ ማኅሌት ይባላል :: መዘምራን /ደባትር/ ስብሐተ እግዚአብሔር፣ ማኅሌተ እግዚአብሔር የሚዘምሩበት ነውና:: በዚሁ ክፍል በምዕራብ በኩል ቀሳውስትና ዲያቆናት በመንፈቀ ሌሊት፣ በነግህ ሰዓታት ይቆሙበታል፣ ኪዳን ያደርሱበታል::

በጥንት የቤተክርስቲያን ሥርዓት ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጸመው በዚሁ ክፍል ነበር::

በዚሁ ክፍል በደቡብ በኩል የሚገኘው ቦታ የሴቶች መቆሚያ ነው:: በቤተክርስቲያን ሥርዓት ወንዶችና ሴቶች አብረው ቆመው ስለማይጸልዩ በመጋረጃ ይከፈላል:: ክፍሉ በምሥራቅ የካህናት መግቢያ በሰሜን የወንዶች መግቢያ በደቡብ የሴቶች መግቢያ ሦስት በር አለው::

ለጥምቀተ ክርስትናና ለቁርባን ያልበቁ በትምህርት፣ በንስሐ ገና የሚፈተኑ ሐዲስ አማንያንም /ንዑሰ ክርስቲያን/ ዲያቆኑ «ፃዑ ንዑሰ ክርስቲያን» እስከሚል ድረስ በዚህ በቅኔ ማኅሌት ይቆያሉ:: ዲያቆኑ «የክርስቲያን ታናናሾች ውጡ» ብሎ በደወል ሲያውጅ ወደ መካነ ቀኖናቸው ተመልሰው ይሄዳሉ:: ወንዶች ምእመናንም ቆመው የሚያስቀድሱት በዚሁ ቦታ ነው::

መዘምራን በሚዘምሩበት በቅኔ ማኅሌት ቆመው የሚያስቀድሱ ንፍቀ ዲያቆናት፣ አናጉንስጢስ፣ መዘምራን ናቸው:: /ፍት.መን. /

ሁለተኛው ክፍል ቅድስት ይባላል። ስያሜው ከብሉይ ኪዳን ስያሜ ጋር ተመሳሳይ ነው። የቤተክርስቲያኑ ማዕከላዊ ቦታ ነው። በዚህ ክፍል በስተምዕራብ በኩል ቆመው የሚያስቀድሱት ቆሞሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ናቸው። በስተሰሜን በኩል መነኩሳትና የሚቆርቡ ወንዶች ምእመናን በስተደቡብ በኩል ደናግል መነኩሳይያት የካህናት የዲያቆናት ሚስቶች ቆመው ያስቀድሱበታል። በዚሁ ክፍል ቆመው ላስቀደሱ ምእመናን ሥርዓተ ቁርባን ይፈጸማል። ከሥርዓተ ጥምቀት፣ ከሥርዓተ ቁርባንና ከሥርዓተ ንስሐ በስተቀር የሌሎቹ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ጸሎት የሚፈጸመው በዚሁ ክፍል ነው። በምሥራቅ፣ በምዕራብ፣ በሰሜንና በደቡብ አራት በሮች አሉት።

ሦስተኛውና የመጨረሻው ክፍል መቅደስ ነው። እንደ ብሉይ ኪዳን ቅድስተ ቅዱሳን የዚህም ስያሜው ከብሉይ ኪዳን የተወረሰ ነው። በዚህ ውስጥ ሥርዓተ ቁርባን የሚፈጸምበት መንበረ ታቦቱ ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት ይገኛሉ። በዚህ ክፍል ከርእሰ ሊ. ቃ ጳጳሳቱ ጀምሮ ሊ. ቃ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ያስቀድሳሉ። ወደዚህ ክፍል ለመግባት የሚችሉ ካህናትና ዲያቆናት ብቻ ናቸው። መቅደስ ሦስት በር አለው። ይህም በር በምዕራብ በሰሜንና በደቡብ ነው። ለእያንዳንዱ በር መንጠላዕት /መጋረጃ/ አለው። የዚህ ዓይነት ቤተክርስቲያን ባለአንድ ጉልላት ነው።

በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ቤተክርስቲያን ሲሠራ በጉልላቱ ላይ ምሳሌነት ባለው በተወሰነ ቁጥር የሰጐን እንቁላል ይሰካበታል። ቁጥሩ ሦስት፣ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት ወይም አሥራ ሁለት መሆን አለበት። ሦስት ቢሆን የምሥጢረ ሥላሴ፣ አምስት ቢሆን ጌታ የተቸነከረባቸው አምስቱ ቅንዋተ መስቀል፣ ስድስት ቢሆን የስድስቱ ቃላተ ወንጌል፣ ሰባት ቢሆን የሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን፣ አሥራ ሁለት ቢሆን የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌ ነው።

ምሳሌነት ብቻ ሳይሆን ምሥጢርም አለው። ሰጐን ጫጩቶችዋን የምትፈለፍለው እንደ ሌሎች ወፎች በመታቀፍ አይደለም። ተባእቱም ሆነ እንስቲቱ ሰጐን ዕንቁላሉን ትኩር ብለው ይመለከቱታል። ዕንቁላሉም ነፍስ ዘርቶ ይፈለፈላል። ለጥቂት ፊታቸውን ቢመልሱ ግን ዕንቁላሉ ገምቶ ይቀራል። በእግዚአብሔርና በምእመናን መካከል ያለው ግንኙነትም እንደዚህ የረቀቀ ነው። ምእመናን በጸሎታቸው ጊዜ ኅሊናቸውን ወደ እግዚአብሔር ፊት በተመስጦ ከአቀረቡ የጸሎታቸውን ፍሬ ያገኛሉ። ወዲያና ወዲህ ካወላወሉ ግን ከንቱ ድካም ነው ለማለት ምእመናንን በምሳሌ ለማስተማር ነው።

ቤተክርስቲያን ሲሠራ የሚሠራው አንድ ቤት ብቻ አይደለም። በቤተክርስቲያኑ አካባቢ ሊሠሩ የሚገባቸው ከቤተክርስቲያኑ ጋር አብረው አገልግሎት የሚሰጡ ቤቶች አሉ። በቤተ ክርስቲያኑ ምሥራቅ ዲያቆናቱ ለመሥዋዕት የሚሆነውን ኅብስትና ወይን የሚያዘጋጁበት ሁለተኛ ቤት ይሠራል። ይህም ቤት «ቤተልሔም» ይባላል። ስያሜው የተወሰደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት በቤተልሔም ዘይሁዳ ምሳሌ ነው።

ምሥጢሩና ቁም ነገሩ ደግሞ ዲያቆናት ኅብስቱን በቤተልሔም አዘጋጅተው ወደ ቤተክርስቲያን ለመሥዋዕት መምጣቱ በቤተልሔም የተወለደው በጐልጐታ ለመሥዋዕት የቀረበው ክርስቶስ ይህ ነው ለማለት ነው:: መቅደስ የጐልጐታ ምሳሌ ነውና:: የቤተክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት የሚቀመጡበት አራተኛ ቤትም ይሠራል:: ይህም ዕቃ ቤት ይባላል:: የቤተክርስቲያኑ መገልገያ የሆኑት አልባሳትም መጻሕፍትም የሚቀመጡት በዚሁ ቤት ነው:: /ሕዝ.44÷19:: ፍት.መን12/

ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጸምበት የማጥመቂያ ቤትም አለ:: ከዚህም ሌላ የሙታን በድን የሚያርፍበትና ጸሎተ ፍትሐት የሚፈጸምበት ደጀ ሰላም ከቤተክርስቲያኑ ቅጽር ተያይዞ ይሠራል::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አምስት ቤቶች በግድ ከቤተክርስቲያኑ ሳይለዩ አብረው የሚሠሩ አስፈላጊ ቤቶች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ እንደ ቤተክርስቲያኑ ዐቅም ሊሠሩ የሚገባቸው ቤቶች አሉ እነዚህም፣

- የሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት
- የሰንበት ት/ቤት ክፍሎች
- የምእመናን መማሪያ የሰበከተ ወንጌል አዳራሽ
- የእንግዶችና የካህናት ማረፊያ ቤቶች
- የመንፈሳዊ ት/ቤት የተግባረ ዕድ መማሪያ
- ቤተ መጻሕፍት
- የንዋያተ ቅድሳትና ጧፍ ዕጣን ሽያጭ ክፍሎች ናቸው::

በደብተራ ኦሪት፣ በመቅደስ ኦሪት በግብር አምላካዊ አሥሩ ትእዛዛት የተጻፉበት ጽላተ ኪዳን ታቦተ ሕግ ይቀመጥበት እንደነበረ ሁሉ በቤተክርስቲያንም ይኸው ሕጉ የተጻፈበት ጽላት ታቦት በመሠዊያነት ይኖራል:: መሥዋዕት ይቀርብበታል:: በብሉይ ኪዳን ይሠዋ የነበረው መሥዋዕት ቢያልፍም የመሥዋዕት አቀራረቡ ቢለወጥም በብሉይ ኪዳን በልዩ ልዩ አቀራረብና ሥርዓት መሥዋዕት ይሠዋ እንደነበር ይታወ ቃል:: ዛሬም በቤተክርስቲያን አማናዊ መሥዋዕት የቅዱስ ሥጋው ክቡር ደሙ የወልደ እግዚአብሔር ይሠዋል::

# ክፍል 1

# ሀ. የቤተክርስቲያን አተካከልና አሠራር

## 1. የቤተክርስቲያን ሥራ ፈቃድ

ቤተክርስቲያን ለመትከል ሲፈለግ የክፍሉን /የሀገረ ስብከቱን/ ኤጲስ ቆጶስ ማስፈቀድ ያስፈልጋል:: ያለ ኤጲስ ቆጶስ ፈቃድ ቤተክርስቲያን አይተከልም:: አይሠራም:: /ፍት.መን.አንቀጽ 1 ቁጥር3/

## 2. የቤተክርስቲያን ሥራ እቅድ /ፕላን/

ቤተክርስቲያን ሲሠራ ሦስት ክፍል ማለት መቅደስ፣ ቅድስት፣ ቅኔ ማኅሌት ሆኖ ነው፤ የቤተክርስቲያን /ሕንጻ ቤተክርስቲያን/ አሠራር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ሦስት ነው::

ከእነዚህም አንዱ እንደ ብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ /ምኩራብ/ ቅርጽ ሰቀላ ወይም ሞላላ ቅርጽ ነው:: የዚህ ዓይነት ቤተክርስቲያን ቅርፅ የተወረሰው ከሰሎሞን ቤተመቅደስና ኋላም በዘመነ ክርስትና ታላቁ ቆስጠ ንጢኖስና እናቱ ዕሌኒ በኢየሩሳሌም በቤተልሔም ካሠሩዋቸው አብያተ ክርስቲያናት የተቀዳ ነው::

<u>ለምሳሌ:</u>- ዐፄ ዮሐንስ አራተኛ ያሠሩት የደብረ ሊባኖስ ቤተክርስቲያን ሰቀላ ሆኖ 18 ጉልላት ነበረው ይባላል:: የሰቀላ ቤተክርስቲያን በሩ የተወሰነ አይደለም:: ሦስትም አራትም ከዚያም በላይ ሊሆን ይችላል::

ሁለተኛው ቅርፅ ዙሪያው ክብ ነው:: ቤተንጉሥ ቅርፅ ይባላል:: በግድግዳ ከሦስት ይከፈላል:: የመጀመሪያው ዙሪያ ቅኔ ማኅሌት ይባላል:: ስያሜው ከግብሩ የተወረሰ ነው:: ደባትር /መዘምራን/ ስብሐተ እግዚአብሔር፣ ማኅሌተ እግዚአብሔር የሚያደርሱበት ነው:: ሁለተኛው ክፍል ቅድስት ይባላል:: የኤጲስ ቆጶሱ መንበር በዚህ ውስጥ ነው:: ለቁርባን የተዘጋጁ ምእመናንም ቁመው የሚያስቀድሱበት ነው:: ሦስተኛው ክፍል መቅደስ ሲባል ይኸውም ሥጋውና ደሙ የሚፈተትበት መንበረ ታቦቱና ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት የሚገኙበት ክፍል ነው:: ስያሜው ከግብሩ የተወረሰ ነው

ሦስተኛው ቅርፅ ዋሻ ነው:: የዋሻ ቤተክርስቲያን በሩ አንድ ብቻ ነው:: ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስቱና መቅደሱም የሚለየው በመጋረጃ ብቻ ነው:: ቅዱስ ላሊበላ ያሠራቸው አብያተ ክርስቲያናት አንዳንዶቹ ዋሻዎች ናቸው:: የዋሻ ቤተክርስቲያን ጉልላት የለውም የመቅደሱም በር አንድ ነው::

አሁን ደግሞ ለቤተክርስቲያን ሥራ ምሳሌዎች የሆኑትንና ትርጉም የሚሰጡትን እንመልከት::

የቤተክርስቲያን ሦስት በሮች የሥላሴ፣ ሦስት ክፍሎች የሦስቱ ሰማያት/ ዓለማተ መላእክት/ ምሳሌዎች ናቸው፤ ዓለማተ መላእክት የሚባሉት ሦስቱ ሰማያትም ኢዮር፣ ራማ፣ ኤረር ናቸው:: ሁለተኛዋ የሦስቱ ማዕርጋተ ክህነት ምሳሌዎች ናቸው፣ ሦስቱ ማዕረጋት ክህነትም ዲቁና፣ቅስና፣ ኤጲስ ቆጶስነት ናቸው:: ሦስተኛም የሦስቱ ጸታ ምእመናን ምሳሌ ነው፤ ሦስቱ ፆታ ምእመናን ካህናት፣ ወንዶች ሴቶች ናቸው::

ቤተክርስቲያን ስትሠራ ብዙ አዕማድ /ወጋግራዎች/ ያሉዋት ሆና ትሠራለች:: ቤተክርስቲያን በውስጥና በአፍአ የሚቆሙት አዕማድ /ምሰሶዎች/ የሠራዊተ መላእክት ምሳሌዎች ናቸው:: ቤተክርስቲያን ካህናት አሉዋት፤ ካህናት የመላእክት ምሳሌዎች ናቸው:: ቤተክርስቲያን መስቀል አላት፣ መስቀል ውሃ ሳያጠጧት የለመለመች ያበበችና ያፈራች የበትረ አሮን ምሳሌ ነው:: /ዘኁ.17÷5–8 ፣ ዕብ.9÷4/

## 3. ቅዳሴ ቤተክርስቲያን

ኤጲስ ቆጶስ ቅዳሴ ቤተክርስቲያን በሚያደርግበት ጊዜ ከርሱ ጋር ለተራድኦ ቀሳውስት እንዲገኙ ታዘዋል::

ኤጲስ ቆጶሱ ቤተክርስቲያንን ታቦትን ሲባርክ የእግዚአብሔር ማኅተም የሆነውን ቅብዐ ሜሮን ይቀባዋል::

ቤተክርስቲያኑ በተባረከ ዕለት በውስጡ ይቀደስበታል:: ቤተክርስቲያኑ ሲባረክ ወንጌለ ዮሐንስ በታቦቱ ላይ ወይም በጉኑ ሆኖ ይነበባል::

ኤጲስ ቆጶሱ ሳይመጣ ቀሳውስትና ዲያቆናት ሳይሰበሰበ ቅዳሴ ቤተክርስቲያን አይደረግም:: /ፍት.መን.አንቀጽ1/

## 4. የጽላት አቀራረጽ

በአሪት ታቦት የሚባለው ጽላት የሚቀመጥበት ማደሪያው ነው:: /ዘጸ.40÷20-21 ፣ 25÷20-22 ፣ መዝ.131÷8 ፣ 2ቆሮ.6÷16 ፣ ዕብ.9÷4 ፣ ራእ.11÷19/

ጽላት የሚባለው ደግሞ እግዚአብሔር ለሙሴ አስቀድሞ አሠርቱ ቃላተ ኦሪትን በእጁ የሰጠው ቃሉ ተጽፎ የሚገኝበት ከዕብነ በረድ የተቀረጸው ነው:: /ዘጸ.31÷18 ፣ 24÷12-25 ፣ 10÷22 ፣ 34÷1-29/ ይህ በብሉይ ኪዳን የነበረው ሥርዓት ነው::

በሐዲስ ኪዳን ግን ጽላትም ታቦትም የሚባለው ያው አንዱ መሠዊያ ነው፤ ጽላት ሲቀረጽ ጻሕል ጽዋዕ እንዲይዝ ከቦታ ወደ ቦታ ለማዛወር እንዲቻል ሆኖ ይቀረጻል:: ፍት.መን.አንቀጽ 1/

ከዚህ በኋላ በጽላቱ ላይ «አልፋ ወኦ፣ ቤጣ የውጣ» የሚለው የጌታ ስም ይቀረጽበታል፤ ከላይ ሥዕለ ሥላሴ፣ ቀጥሎ ምስለ ፍቁር ወልዳ፣ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ እንዲሁም መቅደሱ የተሠራለት ጻድቅም ሆነ ሰማዕት ሥዕሉ ይቀረጻል:: ስሙ ይጻፋል::

ጽላተ ኪዳኑም ማኅደረ እግዚአብሔር ነው፣ ያለ ታቦትም መሥዋዕት አይሠዋም::

## 5. ማኅቶተ ቤተክርስቲያን /የቤተክርስቲያን መብራት/

በቤተክርስቲያን የሚበራው መብራት ሻፍና ዘይት ነው:: /ፍት.መን.አንቀጽ1/

በቤተክርስቲያን ብዙ መብራት ማብራት ታዟል:: በተለይ ቅዱሳት መጻሕፍት ማለት መልእክተ ጳውሎስ፣ መልእክታተ ሐዋርያት፣ ግብረ ሐዋርያት ሲነበቡ መብራት እንዲበራ ታዟል:: ይልቁንም ወንጌል ሲነበብ እጅግ በጣም መብራት ማብዛት እንደሚገባ ተሠርቷል:: /ፍት.መን.አን.1/

## 1. ሥርዓተ መቅደስ ወዐውደ ምሕረት

በታቦት ፊት ለመስገድ፣ ለመጸለይ ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ወደ መቅደስ ገብቶ እንዲቀመጥ አልተፈቀደለትም::

ካህን ካልሆነ በስተቀር ከምእመናን ወገን ማንኛውም ሰው ወደ መቅደስ ገብቶ ሥጋ ወደሙን አይቀበልም:: ወደ ታቦትም አይጠጋም:: /ፍት.ነገ.አን.1:: በደስ19/

ሴቶች ወደ መቅደስ እንዲገቡና በመቅደስ ውስጥ እንዲጸልዩ አልተፈቀደም:: /ፍት.መን.አን.1 ሎዶቅ44/

በቤተክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢና የውጭ አደባባይ ገበያ ክልክል ነው:: /ኤር.7÷11 ማቴ.21÷12-13 ፣ ማር.11÷15-17 ፣ ሉቃ.19÷45-46 ፣ ዮሐ.2÷13-18 ፍት.አን.1/

በቤተክርስቲያኑ ውስጥ በቅጽረ ግቢም ቢሆን ግብዣ ማድረግ መብላት መጠጣት ክልክል ነው:: /ፍት.መን.አንቀጽ 1 ለዶቅ 28/

ከቤተክርስቲያን የገባውንና የተቀደሰውን ንዋያተ ቅድሳት እንደገና ወደ ውጭ አውጥቶ ለሥጋዊ አገልግሎት ማዋል አይገባም /ፍት.መን.አን1፣ ረስጣ28/

ያላመኑ ያልተጠመቁ ተወግዘው የተለዩ ወደ ቤተክርስቲያን እንዳይገቡ ምሥጢረ ቤተክርስቲያንን እንዳይሳተፉ ተከልክሏል:: የቤተክርስቲያኑ በሮችም በአጋፋሪዎች እንዲጠበቁ ታዝዘዋል /ፍት.መን.አን 12/

## 2. ወደ ቤተክርስቲያን ስመሄድ የሚደረግ ጥንቃቄ

ለጸሎትና ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል ወደ ቤተክርስቲያን በሚኬድባቸው ዕለታት እንዲሁም በጾምና በሰንበት በበዓላት ቀኖችም ወንድና ሴት መገናኘት ክልክል ነው:: በመኝታ የተገናኘ ወደ

ቤተክርስቲያን በዕለቱ አይገባም:: ወደ ቤተክርስቲያን ባይሄዱም በዓላትንና አጽዋማትን ሊጠብቁ ይገባል:: /ዘጸ.19÷15፣ 1ቆሮ.7÷5-7፣ ኩ.4÷34÷12/

ሴት በወር አበባዋ ጊዜ እስከ ሰባት ቀን ድረስ፣ ስትወልድ ወንድ ከወለደች አርባ ቀን ሴት ከወለደች እስከ ሰማንያ ቀን ድረስ ወደ ቤተክርስቲያን እንዳትገባ ታዟል:: ከዚህ በኋላ ግን ገላዋን ታጥባ ትገባለች:: /ዘሌዋ.12-15- 19÷28:: ፍት.መን.አን.6 ዘኒቅያ 29/

ወንድ ሕልመ ሌሊት /ዝንየት/ ከመታው በዕለቱ ወደ ቤተክርስቲያን አይገባም:: በማግሥቱ ገላውን ታጥቦ ይገባል:: /ዘሌዋ.15÷2-18/

# ክፍል 2

## ሰ. ሥርዓተ ጥምቀት

### 1 የጥምቀት አመሠራረት

ጥምቀት ማለት «አጥመቀ» አጠመቀ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የሚወጣ ማጥመቅ መጠመቅ የሚል ትርጉም የሚሰጥ ሳቢ ዘር ነው::

ጥምቀት ሌሎችን ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ለመሳተፍ የቤተክርስቲያን አባል ለመሆን የመጀመሪያው መግቢያ በር ነው::

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ በሰላሳ ዓመቱ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጥምቆ ጥምቀትን መሠረተ::

ስለ ጥምቀቱም ቀደም ብሎ በብሉይ ኪዳን የተነገረ ትንቢትና የተመሰለ ምሳሌ አለ:: /መዝ.28÷3 ፣ 113÷5-7 ፣ 1ኛ ቆሮ.10÷2 ፣ የሐ.ሥ1÷5/

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ተጠምቆ ከውኃው ከወጣ በኋላ አብ «ዝንቱ ውእቱ ወልድየ» ብሎ የባሕርይ ልጅነቱን መስክሮለታል:: መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጧል:: /ማቴ.3÷16-17/

በትምህርቱ መጨረሻ «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ» በማለት ጥምቀትን አዟል:: /ማቴ28÷19/

### 2 ከመጠመቅ በፊት የሚያስፈልጉ ነገሮች

ከጥምቀት በፊት:- 1ኛ. ትምህርት

2ኛ. እምነት ያስፈልጋል

ተጠማቂው በዕድሜ ከፍ ያለ ከሆነ የክርስትናን ትምህርት የተማረ በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነትና መድኃኒትነት ያመነ መሆን አለበት:: ጌታችን «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ብሎዋል /ማር.16÷16/

እምነት መሠረት ነው:: ሌሎች ተግባራት ግን ሕንጻዎች ናቸው:: እምነቱን ለመግለጥ የማይችል ሕጻን ከሆነ ግን በወላጆቹና በክርስትና

አባቱ ወይም እናትዋ ኃላፊነት ይጠመ ቃል:: ከአደገ በኋላ በኃላፊነታቸው ይመክሩታል:: ያስተምሩታል::

ንዑስ ክርስቲያን ከመጠመቁ በፊት ሥራው ይመረመራል:: ተመርምሮ እምነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ይጠመ ቃል:: /ፍት.መን.አን 3፣ ሥርዋጽ 2/

ንዑስ ክርስቲያን ከመጠመቁ በፊት በመጽሐፈ ኪዳን እግዚአብሔር ዘብርሃናትን እየደገሙ ያጠምቁታል:: ዘይት ይቀባል:: /ፍት.መን.አንቀጽ3/

## 3 ለጥምቀት የተወሰነ ዕድሜ

ለጥምቀት የተወሰነ ዕድሜ ለወንዶች አርባ ቀን ለሴቶች ሰማንያ ቀን ነው:: /ኩፋ.4÷12፣ ዘሌዋ.12÷1/ ሕጻኑ ሞት የሚያሰጋው ሆኖ ከተገኘ ግን ከአርባናና ከሰማንያ ቀንም በፊት በሞግዚት ታዝሎ ሄዶ ይጠመቃል:: /ፍት.መን.አን.3 ሥርዋጽ 2/ ለመጠመቅ ቀኑ የደረሰውን ሰው ለነገ ብሎ ቀጠሮ መስጠትና በልዩ ልዩ ምክንያት ማሳደር አይገባም /ፍት.መን.አንቀጽ3፣ ስርዋጽ.2/

ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ጥቅስ ያመነ የተጠመቀ ይድናል የተባለው ዐዋቂ ሰው ካልሆነ በቀር ከመጠመቁ በፊት እምነት መቅደም አለበት ለማለት አይደለም::

በመጀመሪያ ቤተክርስቲያን ስትመሠረት፣ የሕጻናት ጥምቀት አከራካሪ አልነበረም:: ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 10÷48 ላይ ቆርኔሌዎስ ከነቤተሰቡ መጠመቁ፣ በሐዋርያት ሥራ 16÷15 ላይ ሊድያ ከነቤተሰብዋ መጠመቋዋ፣ በ1ቆሮ.1÷16 ላይ የእስጢፋኖስ ቤተሰብ የተጠመቁ መሆኑ ስለተገለጸ ሐዋርያት ያጠምቁ የነበሩት ቤተሰብን በሙሉ እንጂ ሕፃናትን አስቀርተው እንዳልነበረ ያመለክቱናል:: ይህን የመሰለ በቂ ማስረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እያለ የሕፃናት ጥምቀት ሊያጠያይቀን ሊያከራክረን አይችልም::

## 4 የጥምቀት ሥርዓት

1. ጥምቀት የሚደረገው በሥላሴ ስም ነው:: የሥላሴን ስም ሳይጠሩ የተጠመቁት ጥምቀት በባዶ ውኃ ተነክሮ እንደመውጣት የሚቆጠር እንጂ የሚሰጠው ዋጋ ወይም ጥቅም የለውም:: /ማቴ.28÷19/
2. ጥምቀት የሚፈጸመው በፈሳሽ ወይም በጥልቅ ውኃ ነው:: የሥላሴን ስም እየጠሩ «አጠምቀከ በስመ አብ አጠምቀከ በስመ ወልድ አጠምቀከ በስመ መንፈስ ቅዱስ» እያሉ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያደረጉ ማጥመቅ ነው:: ጥልቅ ውኃ በማይገኝበት ጊዜ ግን ውኃ ቀድተው ወይም በእጅ እየታፈኑ ያጠምቁታል::

«ወይኩን ጥምቀት ውስጠ ማይ ውኁዝ ወለእመ ኮነ ህየ
ወጸባክዐው ማየ ዘረከቡ ቀዲሆሙ እምኅበ ምጥማቅ» /ፍት.መን.አን3

ረስጠ.34/

«ወለእመ ኢተረክበ ማይ ዘይውኅዝ ርእሰ ለዘይጠመቅ ይንግዕ መጠነ ሠለስቱ ሕፍን እምነ ማይ ወይሕፀብ ርእሰ በስመ ሥላሴ»

3. አጥማቂው ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ ነው:: ሥልጣነ ክህነት የሌለው ሊያጠምቅ አይችልም::

«ኢያጥምቅ ዘእንበለ ኤጲስ ቆጶስ አው ቀሲስ» /ፍት.መን.አን 3 ድ 21/

ሀ. ሴቶች አያጠምቁም /ፍት.መን.አን.3፣ ድስቅ 20/

ለ. ኤጲስ ቆጶስም ሆነ ቄስ ዋጋ ተቀብሎ ማጥመቅ አይገባውም:: «ወኢይከውኖ ለአሐዱ ከመ ያጥምቅ በህልያን» /ፍት.ነገ.አን.3፣ ፅጥ.4/

ሐ. ማንኛውም ተጠማቂ በሃይማኖት ከተለዩ ሰዎች ቢጠመቅ ክርስቲያን አይባልም:: «እመቦ ብእሲ ዘተጠምቀ ጥምቀተ እምዐላውያን ኢኮነ ውእቱ ምእመነ» /ፍት.መን.3::2÷4/

በማጥመቅ ጊዜ የሚፈጸመው ሥርዓት የሚከተለው ነው::

1. ንዑስ ክርስቲያን የሚጠመቀበት የትንሣኤ ዕለት የሆነ እንደሆነ በስሙነ ሕማማት በሱባኤው ውስጥ ሐሙስ ሰውነታቸውን ይታጠባሉ ዐርብ ይጾሙና እሑድ ይጠመ ቃሉ /ፍት.መን.አን.3፣ በደስ19/

2. ተጠማቂዎች እሑድ ሌሊት በሚጠመቁበት ቦታ ይቆማሉ::

3. ኤጲስ ቆጶሱ ወይም ቄስ የሚጠመቁትን ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አዙሮ እጁን ዘርግቶ ይጸልይላቸዋል::

4. ኤጲስ ቆጶሱ ወይም ቄሱ ከቁራኝነት በሚለዩበት በቅብዐ ቅዱሱ ላይ ይጸልይበታል::

5. ኤጲስ ቆጶሱ ለቄሱ ቅብዐ ቅዱሱን ይሰጠውና በተጠማቂዎች ግራ ያቆመዋል::

6. ቀጥሎ ልጅነት በሚያስጠው መንፈስ ቅዱሰን በሚያሳድረው በሜሮን ይጸለይበታል::

7. ከጸለየበት በኋላ ለሌላ ቄስ ይሰጠውና በተጠማቂዎች ቀኝ ያቆመዋል::

8. ተጠማቂዎች በውኃው አንጻር ሆነው ወደ ሰማይ እየተመለከቱ ፊታቸውን ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ይመልሳሉ::

9. ኤጲስ ቆጶሱ ወይም ቄሱ «ዲያብሎስን ትክደዋለህን» እያለ እያንዳንዳቸውን ተጠማቂዎች ሲጠይ ቃቸው አዎን እንክደዋለን እያሉ እያንዳንዳቸው ይክዱታል::

10. ከዚያ በኋላ አንዱ ቄስ የየአንዳንዱን ተጠማቂ ቀኝ እጅ ይዞ በውኃው አንጻር ፊቱን ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ይመልሰዋል::

11. ወደ መጠመቂያው ከመግባታቸው አስቀድሞ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ እንደአመኑ ይናገራሉ:: ማለት «በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ

ታምናለህን» እያለ እያንዳንዳቸውን ይጠይቃቸዋል:: «አዎን አምናለሁ» እያሉ እያንዳንዳቸው ይመልሳሉ::

12. ከዚህ በኋላ ቅብዐ ቅዱስ ይቀባቸዋል:: ያጠምቃቸዋል በንፍሐት ልጅነትን ያሳድርባቸዋል:: ሲጠመቁ ልብሳቸውን አውልቀው ነው:: ሴቶችም ሲጠመቁ የጠጉራቸውን ሹሩባ የአንገታቸውን የጆሮዋቸውንና የጣታቸውን የእግራቸውን ጌጥ ፈትተው ነው:: /ፍት.መን.አን.3:: ረስጠብ 34/ ሴት በምትጠመቅበት ቀን ግዳጅ ከመጣባት እስክትነጻ ድረስ ትቆያለች::

13. ተጠማቂዎች መናገር የሚችሉ ከሆኑ ራሳቸው እምነታቸውን በመመስከር ጸሎተ ሃይማኖትን ያነባሉ:: መናገር የማይቻላቸው ከሆኑ የክርስትና አባት እናት ስለእነሱ ሃይማኖታቸውን ይመሰክራሉ:: ጸሎተ ሃይማኖት ያነባሉ::

14. ወንዶች ሴቶችን ሴቶች ወንዶችን ክርስትና አያነሡም:: /ፍት.መን.አንቀጽ 3፣ ረስጠብ 34፣ ዘኒ.ቅያ 24/

15. የተጠማቂዎች ቅደም ተከተል ተራ በመጀመሪያ የ40ና የ80 ቀን ሕፃናት ይጠመቃሉ፣ በኋላ ንዑስ ክርስቲያን ወንዶች ይጠመቃሉ:: በመጨረሻ ንዑስ ክርስቲያን ሴቶች ይጠመቃሉ /ፍት.መን.አን 3፣ ረስጠብ 34/

16. ተጠማቂዎች ከተጠመቁ በኋላ ካህኑ ሜሮን ይቀባቸዋል:: ከዚያ በኋላ ሥጋውን ደሙን ያቀብላቸዋል:: ሥጋውን ደሙን ሳይቀበሉ ምንም አይቀምሱም::

17. የክርስትና አባት እናትም አብረው ጾመው ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ::

18. በዕለቱ ክርስትና የተነሡ ከሌሎች ቀራቢዎች በፊት ሥጋ ወደሙን ይቀበላሉ /«ወይትመጠው ቁርባን እምቅድመ ሕዝብ» /ፍት.መን.አንቀጽ 3፣ በስ.105-/

19. የምትጠመቀዋን ንዑስ ክርስቲያን ሴት ቅብዐ ቅዱሱንና ሜሮኑን ኤጲስ ቆጶሱ ከአንገትዋ በላይ ከቀባት በኋላ ሌላውን ሰውነትዋን የምትቀባት ዲያቆናዊት ሴት ናት:: /ፍት.መን.አንቀጽ3:: ረስ. 34/

## 5 በጥምቀት የሚገኝ ክብር

1. ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ ልደት መወለድ /ልጅነት ማግኘት/
2. ከኃጢአት መንጻት ነው::

ሰው በጥምቀት ከኃጢአት በመለየቱ ከእግዚአብሔር በጸጋ በመወለዱ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ይበቃል:: /ሕዝ.36÷25፣ የሐዋ.2÷38፣ 1ቆሮ.6÷11/

«ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት» /ጸሎተ ሃይማኖት/

የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰው ልጅ የሚሰጠው በጥምቀት ከሥላሴ ሲወለድ መሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት ተነግሮዋል።

## 6 የ ሥርዓተ ጥምቀት ትርጉም

ሀ. በውኃ የምናጠምቅበት ምክንያት ራሱ ክርስቶስ በውኃ ተጠምቋል። ሐዋርያትም በውኃ እንዲያጠምቁ አዟል /ማቴ.3÷13-16፣ ማር.1÷9፣ ዮሐ.3÷5፣ ኤፌ.5÷26፣ ቲቶ.3÷5፣ 1ዮሐ.5÷6-8/

ለ. ከውኃው ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብለን መጠመ ቃችን ክርስቶስ በከርሠ መ ቃብር ሦስት መዐልት ሦስት ሌሊት አድሮ የመነሣቱ ምሳሌ ነው። /ፍት.መን.አን. 3፣ ድ.34/

ሐ. ተጠማቂው በሚጠመቅበት ጊዜ ዲያብሎስን ሲክደው ፊቱን ወደ ምዕራብ ማዞሩ የዲያብሎስ ቦታው ምዕራብ ስለሆነ ነው።

መ. ተጠማቂው ፊቱን ወደ ምሥራቅ የሚመልሰው አዳም ከገነት ሰባት ዓመት መኖሩን ለማስታወስ ነው። ገነት ምሥራቅ ናትና።

ሠ. ተጠማቂው ወደ ምዕራብ የሚመለስበት ምክንያት አዳም ሲያል መውረዱን ለማዘከር ነው /ሲያል ምዕራብ ናትና/

ረ. ተጠማቂው በውኃ አንጻር መቆሙ የድኅነት ተስፋ መስማቱን ለማዘከር ነው። ምክንያቱም ድኅነት በጥምቀት ነውና «<u>እድ ዘመኑ መጠውክዎሙ ወኮነቶሙ ጥምቀት</u>» /መጽሐፈ ኪዳን 25 ክፍል/

ሰ. ካህኑ የተጠማቂውን እጁን ይዞ ወደ ምሥራቅ ፊቱን የሚመልስበት ምክንያት ጌታ በጥምቀት ወደ ምሥራ ቃዊት ገነት እንደ መለሰን ለማጠየቅ ነው።

ሸ. የ40፣ የ80 ቀን ሕፃናት በፊት፣ በኋላ ንዑስ ክርስቲያን የሚጠመቁበት ምክንያት ሕፃናት የኖሎት፣ የቅዱሳት አንስት፣ ንዑስ ክርስቲያን የሰብአ ሰገል፣ የሐዋርያት ምሳሌዎች ስለሆኑ ነው።

ቀ. ወንዶች ሴቶችን ሴቶች ወንዶችን ክርስትና እንዳያነሡ የተከለከለበት ምክንያት በፆታቸው ለማስተማር እንዲመች ነው።

## 7 <u>ለንዑስ ክርስቲያን የሚደረግ የቅብዐ ቅዱስ ሥርዓት</u>

ሀ. ዳዊት ይደገማል። ጸሎተ አኰቴት ይደርሳል። ንዑስ ክርስቲያኑ ይታጠባል።

ለ. ዲያቆኑ ጸሎት እያዘዘ ሕዝቡ ይጸልያሉ።

ሐ. ካህኑ ቀርነ ቅብዑን በእጁ ይዞ ጸሎተ ዘይት ይጸልያል።

መ. ካህኑ ዘይቱን ከጸለየበት በኋላ ወንዱን ደረቱን፣ ልቡን፣ ትከሻውን፣ የእጁን መዳፍ ውስጡንና ውጭውን፣ ጀርባውን ይቀባል። ሲቀባም «ዕቀብዐከ በስመ አሐቲ ቅድስት ቤተክርስቲያን እንተ እግዚአብሔር አሜን» እያለ ነው።

ሠ. ካህኑ በየተራው የዘይቱን ጸሎትና ቡራኬ ከአደረሰ በኋላ ንዑሰ ክርስቲያኑ በዘይቱ በተቀላቀለ ውኃ /ጠበል ይረጨዋል።/

ረ. በመጨረሻው ሥርዓተ ጥምቀት አድርሶ ቅብዐ ቅዱሱን ቀብቶ ያጠምቀዋል።

# ክፍል 3

## ሐ. ሥርዓተ ሜሮን

### 1. የሜሮን አመሠራረት

ሜሮን ማለት ቅባት ማለት ነው። እርሱም መልካም መዓዛ ከሚሰጡ ዘይትነት ካላቸው ዕፅዋት ተንጥሮ የሚወጣ ቅብዕ ነው። ሲሠራ በፓትርያርኩና በጳጳሳት ጸሎት ይባረካል፣ ይከብራል።

ከብዙ ዕፅዋት እየተቀመመ በማንጠር እስከ አሁን እየተሠራ መጥቷል /1ዮሐ.2÷27/

የሜሮን ምሳሌ የሆነ በኦሪቱ ታቦትና የደብተራ ኦሪት ንዋያተ ቅድሳት የሚከበሩበት፣ ካህናት ሲሾሙ፣ ነገሥታት ሲነግሡ የሚቀቡት ቅብዐ መንግሥትና ቅብዐ ክህነት እንደነበረ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እናገኛለን /ዘጸ.28÷41፣ 29÷7፣21፣ 40÷9-16 ፣ ዘሌዋ.4÷3፣ 5÷16፣ 6÷20-22፣ 7÷36፣ 8÷2-30፣ 21÷10-12፣ 1ሳሙ.9÷16፣ 10÷1፣ 16÷1-13፣ 1ነገ.1÷34-45/

በዘመነ ሐዲስም በጥምቀተ ክርስትና ጊዜ አንብሮተ እድና ቅብዐ ሜሮን እንዲደረግ ሐዋርያት በሲኖዶስ አዝዘዋል።

አዲስ የተሠራ ቤተክርስቲያን አዲስ ንዋያተ ቅድሳት በቅብዐ ሜሮን ይከብራል። ታቦትም የሚከብረው በቅብዐ ሜሮን ነው።

### 2. የሜሮን አቀባብ ሥርዓት

ሀ. ሜሮን ከጥምቀት አይለይም። ተከታትሎ ሁለቱም ምሥጢር ዕለቱን ይፈጸማል።

ለ. ሜሮን በጳጳሳት ከተባረከ በኋላ ቄስ በእጁ ይዞ ይጸልይበታል። መጽሐፈ ክርስትና ያነብባል።

ሐ. የተጠማቂውን ሰውነት ክፍል ክፍሉን እየለየ በትእምርተ መስቀል አምሳል 36 ሕዋሳቱን ይቀባል።

መ. በሥርዓተ ጥምቀት እንደተገለጠው ካህኑ ሴቷን ንዑሰ ክርስቲያን ከአንገትዋ በላይ ያለውን አካሉዋን ከቀባ በኋላ ከዚያ በታች ያለውን ሰውነቱዋን ዲያቆናዊት ሴት የካህኑን እጅ ይዛ ትቀባታለች።

ሠ. ዲያቆን ተጠማቂው ራሱን ዝቅ አድርጎ /አትኑቶ ርእስ/ በእግዚአብሔር ፊት እንዲቆም ያዝዛል።

ረ. ካህኑ ሜሮኑን ይዞ በተጠማቂው ላይ ይጸልያል።

ሰ. ካህኑ ሜሮኑን በመጀመሪያ በትእምርተ መስቀል አምሳያ እያመሳቀለ በገጹ /ግንባር/ ግራና ቀኝ ሁለት ላይ ይቀባል። ግንባሩን ሲቀባ በፊቱ ላይ እፍ ይልበታል።

ሸ. ቀጥሎም «ቅብዐ ቅዱስ እቀብዐከ ለሱታፌ ሕይወት ዘለዓለም» እያለ ሁለቱን የአፍንጫውን በር ሁለት፣ ሁለቱን ከናፍር ሁለት፣ የቀኝ ጆሮ አንድ፣ የግራ ጆሮ አንድ፣ የቀኝ ዓይን አንድ፣ የግራ ዓይን አንድ፣ ደረት አንድ፣ ልብ አንድ፣ ከማሕል ራስ እስከ ወገብ አንድ፣ መሐል ጀርባ አንድ፣ እንብርት አንድ ይቀባል።

ቀ. ከዚያም «እቀብዐከ ለአምላከ መሢሕ በማኅተሙ ዘኢይትፌታሕ» እያለ ቀኝ እጅ አንድ፣ ግራ እጅ አንድ፣ የእጆች መገናኛዎች ሁለት፣ የቀኝ ትከሻ አንድ፣ የግራ ትከሻ አንድ፣ ማጅራት አንድ፣ አንገት አንድ፣ የቀኝ ክርን አንድ፣ የግራ ክርን አንድ፣ የሁለት እጅ መዳፍ የውጭው ሁለት፣ የውስጡ ሁለት ይቀባል።

በ. እንደዚሁም «እቀብዐከ ቅብዐተ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ...» እያለ የእግር መገናኛዎችን /ዳሌ፣ ሙላ፣ ታፋ/ ሁለት፣ የሁለት እግር ጉልበት ሁለት፣ የሁለት እግር ጣቶች የውጭው ሁለት፣ የውስጡ ሁለት ይቀባል።

ተ. ካህኑ ሜሮን ቀብቶ ከፈጸመ በኋላ በተጠማቂው ላይ እጁን ጭኖ /በአንብሮተ እድ/ «ቡሩክ ኩን በበረከተ መላእክት ሰማያውያን...» እያለ ይባርከዋል።

ቸ. ከዚያ በኋላ ተጠማቂው ነጭ ልብስ ይለብስና በራሱ ላይ አክሊል ይቀዳጃል።

## 3. <u>በሜሮን የሚገኝ ጸጋ</u>

ሜሮን የእግዚአብሔር ጸጋ ለምእመናን የሚሰጥበት መንፈስ ቅዱስ የሚያድርበት ምሥጢር ነው።

በጥምቀት የሚሰጠውን ሀብተ ጸጋ የሚያረጋግጥ የሚያጸና ማኅተም ሜሮን ነው። በጠቅላላው መንፈሳዊ ሕይወት በጥምቀት ይጀመራል ማለት ዳግም ልደት ይወለዳል፣ በሜሮን ይታተማል /የሐዋ.8÷14-17/

## 4. <u>የሥርዓተ ሜሮን ትርጉም</u>

ሀ. ሜሮን ከብዙ ዓይነት ዕፀዋት ተደባልቆ ተሠርቶ አንድ መሆኑ መንፈስ ቅዱስ አንድ ሲሆን ሀብቱ ብዙ የመሆኑ ምሳሌ ነው /1ቆሮ.12÷4-13/

ለ. አክሊል የሚቀዳጀው አይሁድ በዕለተ ዓርብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያቀዳጁት አክሊለ ሦክ ምሳሌ ነው።

# ክፍል 4

## መ. ሥርዓተ ቁርባን

### 1. የመሥዋዕትና የቁርባን አመሠራረት

ሀ መሥዋዕተ አበው፡- መሥዋዕተ ቁርባን ማቅረብ የተጀመረው በአዳም ጊዜ ነው:: ከአዳም እስከ ሙሴ የተነሡ አበው ሁሉ በሕገ ልቡና ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ይሠዉ፣ ቁርባን ያቀርቡ ነበር:: መሥዋዕታቸውም ከእንስሳ ሲሆን ቁርባናቸው ከእህልና ከአትክልት ማለት ከስንዴ እህል፣ ከወይን ፍሬ የሚቀርብ ነበር::

ለ. መሥዋዕተ ኦሪት፡- በዘመነ አበው ይደረግ የነበረው የመሥዋዕት አቀራረብ በኦሪትም በሁለት ዓይነት ይሠራ ነበር:: ይኸውም ከሥጋ ከደም ወገን የሆነው መሥዋዕት፣ ከእህል ወገን የሆነው ቁርባን ይባል ነበር::

መሥዋዕቱና ቁርባኑ የሚቀርበው የሠርቀ ወርኅ /መባቻ/ የሰንበትና /ቀዳሚት/ የታላላቅ በዓላት ዕለት ሲሆን የፈ ቋድ፣ የምስጋና፣ የበዓል፣ የመድኃኒት፣ የንስሐ፣ የብፅዓት፣ የቅንዓት እየተባለ ይጠራ ነበር::

መሥዋዕት አቅራቢዎችና ቦታው ልዩነት ነበራቸው:: ይኸውም ከመጋረጃ ውጪ ቦታው በቅድስት መሥዋዕት አቅራቢዎች ካህናት፤ ከመጋረጃ ውስጥ ቦታው ቅድስተ ቅዱሳን መሥዋዕት አቅራቢው ሊቀካህናት ይባል ነበር::

ጊዜውም እንደዚሁ ልዩነት ስለነበረው ካህናት ዘወትር ሲሠዉ የካህናቱ አለ ቃ በዓመት አንድ ቀን ይሠዋ ነበር/ዕብ.9-6-7/

ካህናቱም ሆኑ ሊቀ ካህናቱ አስቀድሞ ስለራሳቸው በደል መሥዋዕት ከሠዉ በኋላ ነበር ስለሕዝቡ ኃጢአት መሥዋዕት የሚያቀርቡት /ዕብ.10-14/

አይሁድ ስለኃላፊው መብል ብቻ አጥብቀው ሲፈልጉት፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ኃላፊው መብል ሳይሆን ዘለዓለም ለሚኖረው ምግብ አስቡ» ቢላቸው አባቶቻችን ከሰማይ እንጀራ በሉ አንተስ ከዚህ የተሻለ ምን ተአምራት ታደርጋለህ» አሉት:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን «ይህ ሙሴ የሰጣችሁ እንጀራ አይደለም ይህ ከሰማይ የወረደ ኅብስት ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው:: እኔም የምሰጣችሁ ኅብስት ሥጋዬ ነው፤ በእኔ የሚያምን አይራብም፣ አይጠማም፤ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ እንጀራ በሉና ሞቱ፤ ከዚህ ኅብስት የሚበላ ግን ለዘለዓለም ይኖራል እንጂ አይሞትም፤ ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ» ብሎ አስተምሮአቸዋል /ዮሐ.6./

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐሙስ ማታ አይሁድ በብሉይ ኪዳን ሥርዓት በጉን በመቅደስ አርደው፣ ሲመሽ ወስደው፣ በቤታቸው

ከተካፈሉት በኋላ ምሳሌ የነበረው በግዐ ፋሲካ አልፎ «ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም» የተባለው አማናዊ መሥዋዕት ተተካ ::

በብሉይ ኪዳን ስለ ፋሲካ በዓል አከባበር በሚደረገው ማዕድ ላይ ተቀምጦ ሳለ አምላካችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፋሲካው ራት ከቀረበው ኅብስት አንሥቶ አመስግኖ ባርኮ ቆርሶ ስለ እናንተና ስለ ብዙዎች ቤዛ የሚፈተትና የሚሰጥ ሥጋዬ ይህ ነው:: እንኩ ብሉ ብሎ ሰጣቸው:: እንዲሁም ጽዋውን አንሥቶ÷ አመስግኖ÷ አክብሮ «ስለ እናንተ ስለ ዓለም ሕይወት የሚፈሰው አዲስ ሥርዓት ሆኖ የሚሰጠው ደሜ ይህ ነው:: እንኩ ጠጡ» ብሎ ሰጣቸው

እነሱም አምነው ተቀብለው ሥጋውን በሉ ደሙን ጠጡ ፈጣሪያችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥርዓተ ምሥጢርን ሠርቶ አሳይቶ «መታሰቢያዬን እንደዚህ አድርጉ» ብሎ ስለአዘዛቸው ሐዋርያት ከክርስቶስ የተቀበሉትን ትእዛዝ ለቤተክርስቲያን በመስጠታቸው ቤተክርስቲያን የክርስቶስን ሕማሙን፣ ሞቱን ትንሣኤውን ዕርገቱን፣ ዳግም ምጽአቱን በልብ እያሰበች፣ በአፍዋ እየመሰከረች በሐዲስ ኪዳን ለሐዲስ ሥርዓት የተሰጠውን የዓለሙን ኃጢአት የሚያስተሠርየውን ሥጋ ወልደ እግዚአብሔርን ደመ ወልደ እግዚአብሔርን ስትቀበል ስታቀብል ኖራለች:: ትኖራለች::

## 4.ስቁርባን የሚደረግ ጥንቃቄ

ሀ. የሚቀድሱና የሚቆርቡ ሰዎች በጋብቻ ሥርዓት የሚኖሩ ከሆኑ ከመቀደሳቸውና ከመቀረባቸው በፊት ሦስት ቀን ከቁርባን በኋላ ሁለት ቀን ከሩካቤ ሥጋ መከልከል ይገባቸዋል::

ለ. ቁርባን መቀበል ንስሐ ገብቶ ከኃጢአት ነጽቶ ነው:: ከክርስቲያን ወገን ማንም ሰው የክርስቶስን ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ትንሣኤ ዘለሕይወትን ሊወርስ ቢወድ ልቡን ከቂም ከበቀል ሰውነቱን ከበደል ንጹሕ አድርጎ መቀበል አለበት:: ይህም ማለት ሰው ስለሚያውቀው ኃጢአት ተናዝዞ ስለማያውቀው ይቅር በለኝ እያለ በንጹሕ ይቁረብ ማለት ነው:: ከኃጢአት ሳይነጻ ቢቀበል ግን የጌታ ሥጋ እንደሆነ አላወቀምና እንደ ምድራዊ ምግብ አቃልሎታል በኃጢአት ሳለ ያለ ኃፍረት ሥጋውን ደሙን በመቀበሉ ሥላሴ ይፈርዱበታል:: /1ቆሮ.11÷23-29/

ሐ. ሥጋ ወደሙ ለመቀበል 18 ሰዓት ከእህል ከውኃ ተከልክሎ መፆም ይገባል /ኢይንሣዕ መኑሂ ቁርባነ ዘእንበለ ይጹም በንጹሕ/ ፍት.መን.13:: ረስጠብ 46/

መ. ሰው ዝንየት /ርስሐት/ ከአገኘው በዚያን ቀን አይቆርብም::

ሠ. ካህን በሚቀድስበት ቀን ዕንቅፋት ቢያገኘው ማለት ነስር÷ ትውኪያ /አንቋር/÷ ብስና÷ ማንኛውም የአካል መድማት መቁሰል÷ ወደ አፍ

የሚገባ እንደ ትንኝ ዝምብ ይህን የመሰለ ሁሉ ቢያጋጥመው በዚያው ዕለት መቀደስ መቀረብ አይገባውም።

ይህም ለካህን ብቻ ሳይሆን ምእመናንንም የሚመለከት ነው። ከቁርባን በኋላ ከአለመጠንቀቅ የተነሣ እንዲህ ያለ ነገር ቢያጋጥመው ንስሐ ሊሰጠው ይገባል። ንስሐውን ሳይፈጽም እንደ ገና መቁረብ አይችልም። /ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ/

## 5. ስመሥዋዕት የሚገባ ስንዴ

ሀ. መሥዋዕት የሚሆነው በወራቱ የደረሰ ዋግ ያልመታው እንክርዳድ የሌለበት ንጹሕ ስንዴ ነው። /ፍት.መን.13 ረስጣ.3/

ለ. ለመሥዋዕት የሚቀርበው ኅብስት ዕለቱን የተሠራ እንዲሆን ታዟል። ከተሠዋም በኋላ ለማግሥቱ አያድርም /ፍት.መን.አንቀጽ13 ረስጠ.30/

ሐ. ኅብስቱም ነቅዕ ያለበት አይሆንም፣ ነቅዕ የሌለበት ያላረረ ያልጠቆረ እንዲሆን ታዟል /ፍት.መን 13/።

መ. ኅብስተ አኰቴቱ ሲሠራ አሥራ ሦስት መስቀል ባለው ማኅተም ታትሞ ይሠራል።

## 6. ስመሥዋዕት የሚገባ ወይን

ሀ. ወፍ ያልመጠጠው አይጥ ያልቀረጠመው መጀመሪያ የደረሰው ወይን ሊሆን ይገባል።

ለ. ለመሥዋዕቱ የሚቀርበው ወይን በእሳት ከሚበስሉ ከጠጅ ከአረቄ ወገን በማንኛውም አይሠራም /ፍት.ነገ.13። ረስጣ 3/

ሐ. ወይኑንም ሲሠሩ ጥሩ መሆኑን ተመልክቶ መሥራት ይገባል። ንጹሕ ጽሩይ ካልሆነ ለመሥዋዕት አይገባም። ከሚሶ የበለጠ ውኃም አይጨመርበትም /ፍት.መን./

መ. ዓመት ያለፈውና መዓዛው የለወጠ ወይን ለመሥዋዕት ሊቀርብ አይገባም /ፍት.መን.አንቀጽ 13፣ በስ.102/

## 7. መቀደሻ አልባሳት

ሀ. የሚቀደስባቸው አልባሳት በቤተክርስቲያን ዕቃ ቤት ሊቀመጡና በንጽሕና ሊጠበቁ ይገባል። ከዚህ ውጪ በሌላ ቦታ እንዲቀመጡ አልተፈቀደም።

ለ. ካህናት የሚደርቡት ካባ ላንቃ አምስት መንዲል /ከልጅ/ ያለው እንዲሆን ታዟል። መንዲል ወይም ከልጅ ማለት ለምድ ነው።

ሐ. ካህናት በቀደሱ ጊዜ የሚለብሱት እስከ ተረከዛቸው የሚደርስ መሆን አለበት። /ፍት.መን.አንቀጽ 12/

መ. ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት ልኩ የሚሆነውን መርጦ ይለብሳል። ልብሰ ተክህኖ ከለበሰ በኋላ ማውለቅ አይገባውም። ቀሚሱ ከረዘመበት በዝናር ይታጠቀዋል። /ፍት.መን.አንቀጽ 12/

ሠ. የሚቀድሱ ካህናት ሲቀድሱ ነጭ ልብስ እንዲለብሱ ታዟል። የሚቆርቡ ምእመናንም ንጹሕ ነጭ ልብስ ለብሰው መቁረብ ይገባቸዋል። «ወአልባሰ ቅዳሴ እለ ይቄድሱ ቦቶን ይኩና ጸዐድወ በከመ ይደሉ ለካህናት ወአኮ ኅቡራት» /ፍት.መን. 12/ ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት ጳጳስ ካለ ጳጳሱን አስባርኮ ይለብሳል ከሌለ ራሱ ባርኮ ይለብሳል።

8. <u>ሥርዓተ ቅዳሴ</u>

ሀ. ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት አብሮት የሚቀድስ ዲያቆን መኖሩን ማረጋገጥ አለበት።

ለ. ካህን ወደ ቤተመቅደስ ሲገባ በታቦቱ ፊት ከመጋረጃ ውጭ አንድ ጊዜ በመጋረጃ ውስጥ በመሠዊያው ፊት ሦስት ጊዜ ይሰግዳል /ሕዝ.46÷3/

ሐ. ካህን በክብር በፍርሃት ሆኖ «ተንሥኡ ጸልዩ» እያለ ሕዝቡን የሚሰብክለት ዐዋጅ የሚናገርለት ዲያቆን ሳይዝ እንዳይቀድስ ተከልክሏል። ዲያቆኑም አሰምቶ የሚያነብና የሚያዜም ሊሆን ይገባል።

መ. ሕዝቡ እንዳይፈዝ እንዳያንቀላፋ ዲያቆኑ ያነቃቸዋል። /ፍት.መን.12፣ ድስቅ12/።

ሠ. ካህኑ ቅዳሴ ሲገባ ከሁሉ በፊት አንድ ጊዜ በታቦቱ ፊት ሰግዶ አንድ ጊዜ ቀሳውስቱን አንድ ጊዜ ዲያቆናቱን እጅ ይነሣል።

ረ. የሚለብሰውን ልብሰ ተክህኖ ይዞ ፊቱን ወደ ምሥራቅ መልሶ ሦስት ጊዜ ሰግዶ አቡነ ዘበሰማያትን ይጸልያል።

ሰ. ዲያቆን በቤተልሔም ኅብስቱንና ወይኑን ለመሥዋዕት ከሠራና ካዘጋጀ በኋላ ንፍቁ ዲያቆን ኅብስቱን በመሶበ ወርቅ በራሱ ላይ አድርጎ ወይኑን ሠራዒው ዲያቆን በጽዋዕ ይዞ ቃጭል እያቃጨለ በፊት በፊቱ ንፍቁ ቄስ መስቀልና ማዕጠንት ይዞ እያጠነ በኋላ በኋላ ሆነው ከቤተልሔም ወደ ቤተመቅደስ ይገባሉ /ፍት.መን. 12፣ ረስጠብ.92/።

ቀ. ቅዳሴ ሲገቡ ቀዳስያን መንበሩን ከበው ይቆማሉ። ሠራዒ ካህን ፊቱን ወደ ምሥራቅ አድርጎ በምዕራብ ይቆማል። ሠራዒ ዲያቆን ፊቱን ወደ ምዕራብ አድርጎ በምሥራቅ ይቆማል። ንፍቅ ካህን ፊቱን ወደ ሰሜን አድርጎ በደቡብ ይቆማል፤ ንፍቅ ዲያቆን ፊቱን ወደ ደቡብ አድርጎ በሰሜን ይቆማል። ሦስተኛው ቄስ በስተግራ ቆሞ ለሠራዒው ካህን መብራት ያበራለታል። መጽሐፍ ይገልጥለታል።

በ. ዲያቆናት በዐውደ መንበሩ ቆመው ተሰጥዖውን ይቀበላሉ፤ በተለይ ሁለት ዲያቆናት ከልዝብ ሐር የተሠራ መነሳንስ ይዘው አንዱ በቀኝ አንዱ በግራ ቆመው ወደ ጽዋው ምንም ምን እንዳይገባ ተሐዋስያንን ይከለክላሉ /ፍት.መን.አንቀጽ 12፤ረስጣ.52/።

ተ. ወንጌል ሲነበብ መቆም ነው እንጂ መቀመጥ ክልክል ነው።

ቸ. ወንጌል ሲሳለሙም «ነአምን በ ቃለ ወንጌል ቅዱስ» እያሉ ነው።

ኀ. ወንጌል ከተነበበ በኋላ ኤጲስ ቆጶስ ከአለ ወንጌሉን በእጁ ይዞ በክፍሎቹ የተነበበውን ለሕዝቡ ተርጉሞ መንገር ይገባዋል፤ ኤጲስ ቆጶሱ ከሌለ ትርጓሜውን የሚችል ካህን እንዲያስተምር ታዟዋል።

ነ. ኤጲስ ቆጶሱ፣ ወይም ቄሱ፣ ወንጌልን ካነበበ በኋላ ንፍቅ ቄስ «ርኁቀ መዓት» የሚለውን ጸሎት ይጸልያል።

ኘ. ካህን በሥርዓተ ቅዳሴ መጀመሪያና በፍሬ ቅዳሴ መጀምሪያ ሁለት ጊዜ እጁን ይታጠባል። እንዲሁም ሌሎች ካህናትና ዲያቆናት ከቁርባን አስቀድሞ እጃቸውን ይታጠባሉ።

አ. በቅዳሴ ጊዜ በሁለት ጧፍ እንጂ በአንድ ጧፍ አይቀደስም።

ከ. በቅዳሴ ጊዜ ዕርገተ ዕጣን አይቀርም። የሚደረገውም ዕርገተ ዕጣን አምስት ጊዜ ነው /አብጥሊስ3/

ኸ. ማዕጠንት /ጥና/ የሚይዝና የሚያጥን ቄስ ነው እንጂ ዲያቆን በእጁ ይዞ አያጥንም። ኤጲስ ቆጶስ፣ መሥዋዕቱን ከአጠነ በኋላ ሕዝቡንና ካህናቱን፣ ቤተክርስቲያኑን እየዞረ እንዲያጥን ጥናውን ለቄስ ይሰጣል /ድስቅ.12።/

ወ. በቅዳሴ ጊዜ የሠራዒው ካህን ዑደት ሰባት ነው፤ ይኸውም በመጀመሪያው ጸሎተ ዕጣን በመቅደሱ ውስጥ3፣ በአንቀጸ ምዕራብ ሦስት «ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ» እያለ አጥኖ ከፈጸመ በኋላ «እግዚአብሔር አምላክነ በከመ እንሀልክ ቅድመ ጥቅማ ለኢያሪኮ» እያለ ሲዞር አንድ በሁለተኛው ጸሎተ ዕጣን ሦስት በድምሩ ሰባት ዑደት ይሆናል።

ዐ. የንፍቅ ካህን ዑደት ሦስት ነው። ግብረ ሐዋርያት አንብቦ ሲገባ አንድ ወንጌል ተነቦ ሲገባ አንድ ጊዜ፣ «ሠራዊተ መላእክቲሁ» ተብሎ ሲገባ አንድ ጊዜ ይዞራል። በድምሩ ሦስት ይሆናል።

ዘ. ጸሎተ ቅዳሴ ከተጀመረ በኋላ ዲያቆን «እትዉ በሰላም» ብሎ ሳያሰናብት በከባድ ችግርና በሕመም ካልሆነ በቀር ከቤተክርስቲያን መውጣት ክልክል ነው /ፍት.መን.12፣ በስ.92/።

የ. ዲያቆን «ጸልዩ በእንተ ሰላም» ብሎ ስለ ሰላም እንዲጸለይ በቅዳሴ ላይ ትእዛዝ ሲሰጥ ወንዶች ወንዶችን ሴቶች ሴቶችን ሁሉም በየጾታቸው እጅ ይነሣሣሉ፤ ወንዶች ሴቶችን ሴቶች ወንዶችን እጅ አይነሡም /ፍት.መን.12፣ ረስጣ. 103÷32÷53/።

## 10 ስለመቁረብ የሚያበቃና የማያበቃ ሁኔታ

ሀ. ቅዳሴ ሲጀመር ያልነበረ ሰው አይቆርብም፤ ቅዳሴ ሲጀመር ያልነበረ ካህንም እንደዚሁ ሥጋ ወደሙ ሊቀበል ሊያቀብል አልተፈቀደለትም:: /ፍት.መን.12፣ በስ.97/::

ለ. ከምእመናን በስተቀር ያላመኑ ሰዎች ሥጋ ወደሙን እንዳይቀበሉ መጠበቅና መቆጣጠር ያስፈልጋል /ፍት.መን.13፣ ረስጠብ. 44/::

ሐ. በንስሐ የተለየ ሰው የንስሐ ጊዜውን ሳይፈጽም ለሞት የሚያበ ቃ ደዌ ቢታመም ሥጋ ወደሙን ከመቀበል አይከለከልም:: ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ ከዳነም ከምእመናን ጋር በጸሎት ይሳተፋል፤ በቀኖና ወደ ተለዩ ሰዎች አይመለስም /ፍት.መን.13፣ ዕንቁራ 15/

## 11 የቁርባን ሥርዓት

ሀ. የቅዱስ ቁርባን አቀራረብ ተራ ቀጥሎ እንደተዘረዘረው ነው::

1. ሊ.ቃ ጳጳሳት
2. ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት
3. ቆሞሳት
4. ቀሳውስት እነዚህ ሥጋወደሙን በቅድሚያ በየማዕረጋቸው ይቀበላሉ::
5. ዲያቆናት በመቅደስ ይቆርባሉ::
6. ከንፍቀ ዲያቆናት ጀምሮ ሁሉም በየማዕረጉ በቆሙበት ቦታ በቅድስት ይቀበላሉ::
7. ከበር ከፋቾች /ከዐጸውተ ኆዋኀው/ በኋላ በዕለቱ ክርስትና የተነሡ ይቀበላሉ:: ከእነሱም በኋላ ለ40ና ለ80 ቀን ሕፃናተ ቅድሚያ ይሰጣል::
8. ከሕፃናት ቀጥሎ ደናግል
9. የቀሳውስት ሚስቶች
10. የዲያቆናት ሚስቶች
11. መነኰሳት ምእመናን
12. መነኰሳይያት
13. ምእመናን ወንዶችና ሴቶች ተራቸውን ጠብቀው በየማዕረጋቸው ይቆርባሉ::

ለ. ቁርባን ለተቀበሉ ከሐዳፌ ነፍስ በኋላ ማየ መቁረር /የቅዳሴ ጠበል/ ይሰጣል /ፍት.መን.13፣ ረስጣ65/::

ቀዳሾችና ቆራቢዎች ከመቀደሳቸውና ሥጋ ወደሙ ከመቀበላቸው በፊት ሦስት ቀን ከሴት ተከልክለውና ተጠብቀው እንዲቆዩ የተደረገበት ምክንያት በኦሪቱ ዳዊትና ክርሱ ጋር የነበሩት ወደ ካህኑ ወደ አብያታር /አቤሜሌክ/ በመጡና የሚበሉት የቁርባን ኅብስት እንዲሰጣቸው ካህኑን

በጠየቁት ጊዜ ከሴት ከራ ቓችሁ ሦስት ቀን ሞልቷች ኋል ወይ? ብሎ ጠ ይቋቸው ነበር። እነሱም ከቤታችን ከወጣንና መንገድ ከጀመርን ሦስት ቀን ሆኖናል ብለው ሲመልሱለት ኅብስተ ቁርባኑን ሰጥቶዋቸው ዳዊትና ሠራዊቱ ስለበሉ የዚያ ምሳሌ ነው /ዘጽ.19÷15፣ 1ሳሙ.21÷1-6/። ከዚያም ቀደም ብሎ እሥራኤል ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በተጠሩ ጊዜ ሦስት ቀን ከሴት እንዳይገናኙ ሙሴ ያዘዘ ስለሆነ የዚያ ምሳሌ ነው።

* ታቦት የእመቤታችን፣ ጽላት ከእመቤታችን የነሣው ሥጋና ነፍስ፣ በጽላት ላይ ቃል ከድንግል ማርያም የነሳውን ሥጋና ነፍስ የተዋሐደው አካላዊ ቃል ምሳሌ ነው።
* ምሥዋዑ /መሠዊያው/ ጻሕሉ፣ ጽዋው፣ የመንበረ ጸባዖት፣ የጎል፣ የመ ቃብር ምሳሌ ነው።
* መሶበ ወርቅ፣ ማዕጠንቱ፣ የእመቤታችን ምሳሌ ነው። ፍሕም የመለኮት፣ ዕጣን የትስብእት፣ መዓዛው የመዓዛ መሥዋዕት ምሳሌ ነው።
* ኅብስተ ቁርባን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጻሕል የሚለብሰው ማኅፊድ ጌታ ሲወለድ የተጠቀለለበት ጨርቅ፣ ሲሞት የተገነዘበት መግነዝ ምሳሌ ነው። ይኸውም ኅብስቱ የሚጠቀለልበት ማኅፊድ ነው።

6. ዕርፈ መስቀል /ማንካ/ የሱራፌ ጉጠት ምሳሌ ነው /ኢሳ.6-5-7/ ዲያቆን ደም ያቀብልበታል። ሱራፌ ለነቢዩ ለኢሳይያስ ፍሕመ እሳት በጉጠ ት ሰጥቶት ኢሳይያስ ከለምፁ የመንጻቱ ምሳሌ ነው። ፍህሙ የሥጋው የደሙ ምሳሌ ነው። ለምፁ የኃጢአት ምሳሌ ነው። ሱራፊ የዲያቆኑ ምሳሌ ነው። ፍሕሙን ሱራፌ በእጁ አለመያዙ በጉጠት መያዙ ሥጋውን ደሙን በእጅ ለመንካት ያልበ ቃ በዕርፈ መስቀል መስጠት ያለበት መሆኑን ያመለክታል። ኢሳይያስ የምእመናን ምሳሌ ነው። ኢሳይያስ በሱራፌ ጉጠት ፍሕም ከለምፁ መዳኑ ምእመናን ሥጋውን ደሙን ሲቀበሉ ከኃጢአት የመዳናቸው ምሳሌ ነው።

- ቁርባን በአንድ ኅብስት የሚቀርብበት ምክንያት መሥዋዕት ሆኖ የቀረበውና የተሠዋው አንድ አካል ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ ነው።

- ዲያቆኑ «እግዚአብሔር ይሬእየኒ»ን እያነበበ ጽዋውን ይዞ ሦስት ጊዜ ይዞራል። ይህም ጌታ በምድረ ፍልስጥኤም እየተመላለሰ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ወንጌልን የማስተማ ሩ ምሳሌ ነው።

- ቁርባን በጻሕሉ ላይ መቀመጡ ጌታ በመ ቃብር የመቀበሩ ምሳሌ ነው።

- ዕርገተ ዕጣን የደመ አቤል፣ የቁርባነ ኖኅ፣ የሂሩተ አብርሃም፣ የመባዕ ይስሐቅ፣ የመልእክተ ሙሴ ምሳሌ ነው። /ዘፍ.4÷9-12፣ 8÷20፣ 12÷1-3፣ 29÷2-18፣ ዘጸ.3÷10-22፣ 4÷1-3/

- ካህኑ ዑደት በሚያደርግበት ጊዜ መብራት የያዘው ንፍቅ ዲያቆን ከካህኑ ፊት ቀድሞ የሚሄደው የመጥምቁ ዮሐንስ ምሳሌ ነው:: ካህኑ ከንፍቅ ዲያቆን ቀጥሎ ተከትሎ የሚዞረው የጌታ ምሳሌ ስለሆነ ነው:: ምክንያቱም መጥምቁ ዮሐንስ ከጌታ መንፈቅ ቀድሞ ወንጌል አስተምሯልና:: ከካህኑ ቀጥሎ በኋላው ሆኖ ሠራኢው ዲያቆን መስቀል ይዞ የሚዞረው የቅዱስ እስጢፋኖስ ምሳሌ ነው:: ከጌታ ቀጥሎ መከራ የተቀበለ ቅዱስ እስጢፋኖስ ነውና:: /የሐ.ሥራ 7÷58/

በወንጌል ዑደት ጊዜ መብራት የያዘው ንፍቁ ዲያቆን መቅደሙ የነቢያት፣ ንፍቅ ካህን ወንጌል ተሸክሞ መከተሉ የመጥምቁ ዮሐንስ፣ ሠራዒ ካህን እያጠነ ንፍቁን ቄስ ተከትሎ መዞሩ የጌታ፣ ሠራዒ ዲያቆን በኋላ ሆኖ መዞሩ የእስጢፋኖስ ምሳሌዎች ስለሆኑ ነው::

ንፍቅ ካህን ወንጌሉን ተሸክሞ ከካህኑ ፊት ከዞረ በኋላ ለካህኑ የሚሰጠው መጥምቁ ዮሐንስ መንፈቅ ከጌታ ቀድሞ ከአስተማረ በኋላ ጌታ ወንጌሉን የማስተማሩ ምሳሌ ነው:: /ማቴ.4÷12-18/ የንፍቅ ካህን ዑደት ሦስት ጊዜ መሆኑ የሥላሴ አምሳል ነው:: /ማቴ.28÷19/ የጳውሎስ መልእክት ወደ ምዕራብ የሚነበበው የጳውሎስ መልእክትና ትምህርት የተሰጠው ማለት ጳውሎስ ያስተማረው በምዕራብ ሀገሮች ስለሆነ ነው::

የሐዋርያት ሥራና የሐዋርያት መልእክታት በሰሜንና በደቡብ የሚነበበው ሐዋርያት በሰሜኑም በደቡብም ክፍላተ ዓለማት እየተዘዋወሩ ወንጌልን ስለ ሰበኩ ነው:: /ማቴ.28÷19፤/

ወንጌል ወደ ምሥራቅ የሚነበበው «ውእተ አሚረ ይሠርቅ ለክሙ ፀሐየ ጽድቅ ለሕይወት ታንኅ ክንፊሁ» የተባለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የምትሰብክ ስለሆነ ነው:: /ሚክ.4÷2/ የአረገውም በምሥራቅ ነው የሚመጣውም ከምሥራቅ ስለሆነ ነው መዝ.67÷33፤ ማቴ.24÷27/

* ሠራዊት ሦስት ጊዜ መባሉ የሦስትነት፣ ቃሉ አለመለወጡ የአንድነት ምሳሌ ነው::

* ከመጋረጃ በአፍአ ሠራዊት የሚሉት ንፍቁ ቄስና ንፍቁ ዲያቆን ሕዝቡ የነቢያት፣ ከመጋረጃ ውስጥ ሠራዊት የሚሉት ሠራዒ ካህን፣ ዲያቆን አብሪ ካህን የሐዋርያት ምሳሌዎች ናቸው::

* «አርኅዉ» ሲል በር ወይም መጋረጃ መከፈቱ ጌታ በገበያ ቀን በአደባባይ የመሰቀሉ ምሳሌ ነው::

* ካህኑና ሕዝቡ እየተቀባበሉ 40 እግዚኦታ ማድረሳቸው የጌታ የግርፋቱ ካህኑ 41ኛውን ብቻውን የሚለው የአዳም ቀኖና ምሳሌ ነው::

* ደሙን ሲቀበል ሁለት ጊዜ «አሜን ወአሜን» መባሉ ደሙ ሁለት ጊዜ ማለትም ከሞት በፊትና ከሞት በኋላ የመፍሰሱ ምሳሌ፣ ከሥጋው ጋር ሦስት ጊዜ መባሉ ለቀድሶ ሥጋ ወነፍስ ወመንፈስ ሥጋውን መቀረሱን ይተረጉማል::

* ድርገት ሲወርድ ከመሬት የሚወደቀው ጌታ ከሙታን ከተነሣ በኋላ በመንገድ ቅዱሳት አንስትን አግኝቷቸው «በሀክን» ሲላቸው ድምፁን ሰምተው ከመሬት የመውደቃቸው ምሳሌ ነው::

* ድርገት ወደ ምዕራብ መውረዱ ጌታ ፊቱን ወደ ምዕራብ መልሶ ለመሰቀሉ ምሳሌ ነው «እስመ ገጹ ለእግዚአብሔር መንገለ ምዕራብ ከመ ይነጽር ኩሉ ሕዝበ፣ መንገለ ብርሃኑ ዘይሠርቅ» እንዳለ ወደ ምሥራቅ መመለሱ የዕርገት ምሳሌ ነው፤ ያረገው ወደ ምሥራቅ ነውና::

* ዲያቆን ከድርገት በኋላ «ነአኩቶ» እያለ በቅድስት መዞሩ ከጌታ ዕርገት በኋላ እስጢፋኖስ በቅድሚያ አስተምሮ ሰማዕትነት የመቀበሉ ምሳሌ ነው::

* በቅዳሴ ማብቂያ ላይ የሚደረገው አንብሮተ እድ /የካህኑ ሕዝቡን በእጁ መባረክ/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዐረገ ጊዜ ሐዋርያትን በአንብሮተ እድ ባርኮ የማረጉ ምሳሌ ነው::

* ከካህናት ቀጥሎ አዲስ የተጠመቀ ሕፃናት እንዲቀርቡ የተደረገበት ምክንያት ጌታ የተወለደ ዕለት በመጀመሪያ ያመሰገኑ መላእክት ናቸው:: ከዚያ በኋላ የእነሱን ዜና አሰምተው ኖሎት /እረኞች/ ናቸው:: ከዚያ በኋላ የነሱን የሐዳፌ ነፍስ ጸሎት «ጸልዩ» እስከሚለው ያለውን ወደ ምዕራብ ካለ በኋላ ወደ ምሥራቅ የሚጸለየው አዳምና ልጆቹ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በሲዖል ከኖሩ በኋላ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከሲዖል ወደ ገነት መመለሳቸውን ለማዘከር ነው:: /1 ጴጥ.3÷18-22/

* ሥጋ ወደሙ ከተቀበሉ በኋላ መስገድ የተከለከለበት ምክንያት

  1ኛ. ወዙ እንዳይንጠፈጠፍ ነው
  2ኛ. ድኅነት በሥጋው በደሙ ሳይሆን በትሩፋት ዳንን እንዳያሰኝ ነው::

# ሠ. ሥርዓተ ንስሐ

## 1. የንስሐ አመሠራረት

ንስሐ የግእዝ ቋል ነው፤ ትርጉሙ በሠሩት ኃጢአት መጸጸት፣ ወደ ገቢረ ኃጢአት አለመመለስ ነው:: ስለዚህ «ከልብ መመለስ በኃጢአት መጸጸትና ከኃጢአት ለመጠበቅ ቁርጥ አሳብ ማድረግ» ንስሐ ይባላል::

ንስሐ ከጥንት የመጣ ምሥጢርና ሥርዓት ነው:: አዳም በድሎ ንስሐ ቢገባ ተስፋ ድኅነት አግኝቷል:: የነነዌ ሰዎች በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተው ድነዋል/ ትንቢተ ዮናስን በሙሉ አንብብ/

ከሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ምሳሌ ይሆናል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተያዘበት ዕለት ጌታውን አላውቅም ብሎ ሦስት ጊዜ ከካደ በኋላ «ዶሮ ሳይጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ» ያለውን የአምላኩን ቋል አስቦ በኀሊናው ተወቅሶ መራራ ለቅሶ አለቀሰ:: እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስም ንስሐውን አይቶ ኃጢአቱን ይቅር ብሎ «በጎቼን ጠብቅ» ሲል የሐዋርያነትን ሹመት ሰጠው፤ የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጥሃለሁ ሲል በቂሣርያ የሰጠውን ተስፋም ፈጸመለት /ማቴ.26÷69-75፣ ማቴ.16÷19:: ዮሐ.20÷22-23::/

ንስሐ ከእግዚአብሔር የታዘዘ ነው:: እግዚአብሔር ሰውን ከመውደዱ የተነሣ አንዱ እንኳ እንዳይጠፋ የበደለውን ሁሉ ይቅር በማለት ታላቁን የምሕረት በር ንስሐን ከፈተ:: ይህም ምሥጢር ያለማቋረጥ እንዲሠራ ሥልጣኑን ለሐዋርያት ሰጠ::

«የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጥሃለሁ በምድር ያሠርኸው በሰማይ የታሠረ ይሆናል፤ በምድርም የፈታኸው በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ማቴ.16÷19፣ 18÷18::

ካህናት የሕይወት መሰላል ወይም ድልድይ ሆነው የሕዝቡን ንስሐና ልመና ወደ እግዚአብሔር፤ የእግዚአብሔርን ምሕረት ወደ ሕዝብ የሚያደርሱ ናቸው:: በኃጢአት የሚሰናከል ሁሉ ንስሐ ያስፈልገዋል::

## 2. የንስሐ ኑዛዜ አፈጻጸም

በንስሐ የሚሰጠው ቀኖና በሥርዓተ ቤተክርስቲያን መሠረት ይፈጸማል:: ተነሣሒው ኃጢአቱን ለመምህረ ንስሐው ይነግረዋል፤ መምህረ ንስሐው የተነሣሒውን ዐቅም መዝኖ የጾም፣ የጸሎት፣ የስግደት፣ የምጽዋት፣ ቅጣት ይሰጠዋል:: ለዚህም ጊዜ ይወሰንለታል:: የቀኖናውን ጊዜ ከጨረሰ በኋላ ተነሳሒው ወደ መምህረ ንስሐው ተመልሶ እንደ ትእዛዙ መፈጸሙን ይነግረዋል:: ፍትሐት ሰጥቶ /አናዝዞ/ ሥጋውን ደሙን አቀብሎ ከምእመናን ጋር እንዲቀላቀል ይፈቅድለታል::

### 3. በንስሐና ኑዛዜ የሚገኝ ጸጋ

ንስሐ ዘማዊውን እንደ ድንግል ኃጢአተኛውን እንደ ጻድቅ በአጠቃላይ የበደለውን እንደ አልበደለ ያደርገዋል።

በአንብዐ ንስሐ መታጠብ ፍጹም ንጹሕ ያደርጋል። የንስሐ ጥምቀት በዕንባ መታጠብ ነውና። ይህም ነቢዩ ዳዊት «ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን በዕንባዬ አብሳለሁ፤ ምንጣፌንም በዕንባ አርሳለሁ» እንዳለው ነው /መዝ.6÷6/

# ረ. ሥርዓተ ክህነት

## የክህነት አመሠራረት

ክህነት የተጀመረው በመጀመሪያው ሰው በአዳም ነው። እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ፈጥሮ በልጅነት አክብሮ ነቢይ ወካህን አድርጎ ሾመው። በኦሪት በወንጌል ሥርዓት እስኪወሰን ድረስ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ የነበሩ አበው በበረከተ አበው ከእግዚአብሔር እየተሾሙ ትንቢትን፣ ክህነትን ከቅዱስ መንፈስ እየተቀበሉ /እየተሾሙ/ በነቢይነታቸው ያለፈውን የሚመጣውን ሲገልጡ፣ ሲያስተምሩ፣ በክህነታቸው መሥዋዕት ሲያቀርቡ ነበር ።

## ሀ. የፓትርያርክ /ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት/ ወይም የሊቀ ጳጳሳት አሿሿም

ክህነት በዘመነ ኦሪት ለሌዊ ነገድ ከተሰጠ በኋላ ሲወርድ ሲዋረድ እስከ ክርስቶስ ደርሷል። ታላቁ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ብሉይ ኪዳን ካህናት መሥዋዕት እንስሳን ሳይሆን መሥዋዕተ ደሙን ይዞ ራሱ መሥዋዕት ራሱ ሠዋዒ ሆኖ ወደ መቅደስ ገብቶዋል «ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ ዕጣነ»

ሥርዓት

ሀ. ሊቃ ጳጳሳት ቤተክርስቲያንን ለመጠበቅ ክርስቶስ የሾማቸው የሐዋርያት ተከታዮች ናቸው /የሐ.20-28/

ለ. በአንድ ዘመን በአንድ ወምበር ሁለት ሰዎች አይሾሙም

ሐ. ርዕሰ ሊቃ ጳጳሳት ሲሾም ሊቃ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት ይገኛሉ። ይህ ሹመት ያለ ኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ አይደረግም።

«የሀልወ ኤጲስ ቆጶሳት በሢመተ ሊቀ ጳጳሳት እስመ ኢይትፌጸም ዝንቱ ዘእንበለ በሕላዌ ጉባኤሆሙ ለኤጲስ ቆጶሳት ወህላዌ ሚጥሮጶሊስ ዘውእቱ ጳጳስ» ፍት.መን አን 4 ረስ.1-1።

መ. ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ጳጳስ፣ ጳጳስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ፣ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ቄስ፣ ሳለም ከሞተም በኋላ አይፈታውም:: ቄስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ፣ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ጳጳስ፣ ጳጳስ ያወገዘውን ሊቀ ጳጳስ፣ ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ፓትርያርክ /ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት/ ሳለም ከሞተም በኋላ ይፈታዋል:: ሊቀ ጳጳሳት ያወገዘውን ሊቀጳጳሳት፣ ጳጳስ ያወገዘውን ጳጳስ፣ ኤጲስ ቆጶስ ያወገዘውን ኤጲስ ቆጶስ፣ ቄስ ያወገዘውን ቄስ ሳለ አይፈታውም፤ ከሞተ በኋላ ግን ይፈታዋል:: «ወኢይደሉ እም ሊቃነ ጳጳሳት፤ ወጳጳሳት፤ ወኤጲስ ቆጶሳት ከመ ይፍታህ ዘአሠሮ ካልኡ ዘእንበለ እምድኅረ ሞቱ፣ ወሊቀ ጳጳሳት ብውህ ውእቱ እምድኅረ ተከሥተ ከመ ይፍታህ ማአሠሮሙ ለእለ ኩሎሙ ሶበ ርእየ ዝክተ» /ሲኖዶስ 51/

ሠ. ሊቀ ጳጳሳት ወይም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ የታመመ እንደሆነ እስከሚድን፣ የታሠረ እንደሆነ እስከሚፈታ ይጠበቃል፤ ሹመቱ ለሌላ አይሰጥም፤ የማይድን ደዌ ከያዘውና ሊፈታ የማይችልበት እሥራት ከሆነ በላዩ ይሾማል፤ አይጠበቅም /ፍት.መን.4/

## ለ የኤጲስ ቆጶሳት ሢመተ ክህነት ሥርዓት

ሀ. ኤጲስ ቆጶሳት ኖላዊ /ጠባቂ/ ናቸው፣ /ፍት.መን.አን.5፣ ሕዝ.34÷1-10፣ ዮሐ.10÷2-16፣ 21÷15-17/

ለ. ኤጲስ ቆጶስነት የሚሾም ነውር የሌለበት፣ በልቡናው ከሐኬት የነቃ የሚያረጋጋ እንግዳ መቀበልን የሚወድ፣ የተማረ፣ አብዝቶ የማይጠጣ፣ ፈጥኖ የማይማታ፣ ብልህና ዐዋቂ ነው:: «ወነዋ ይደሉ ከመይኩን ኤጲስ ቆጶስ ዘኢተረከበ ውስቴቱ ነውር ወዘአውሰበ አሐተ ብእሲተ ዘንቁህ በህሊናሁ ውእቱ ጠቢብ ወመናዝዝ ወመፍቅሬ ነግድ መምህር ዘኢያበዝህ ስትየ ወይን ወዘኢያፈጥን እዴሁ ለዘፍጥ» /ፍት.መን.አን.5፡ 1ጢሞ.3÷1-3፣ ጢሞ.7÷4

ሐ. ኤጲስ ቆጶስ በጠባዩ ትሑት፣ የማይጣላ፣ ትዕግሥተኛ፣ ሰውን የሚያስታርቅ፣ ገንዘብ የማይወድ፣ ለሰው የሚያዝንና የሚራራ፣ ሰካራምና ቀጡ ያልሆነ፣ ከቂም በቀል ከዓመፅ የተለየ፣ ሐዲስ አማኒ ያልሆነ እንዲሆን ታዟል /1ጢሞ.3÷3-7፣ ፍት.ነገ. አን 5/::

መ. ኤጲስ ቆጶስ ከ50 ዓመት በታች እንዳይሾም ተከልክሏል:: «ወዘኢኮነ ሕይወቱ ሕፁፅ እም 50 ዓመት» /ፍት ነገ.5 ድቅስ 4/::

ሠ. ኤጲስ ቆጶስ ብሉይና ሐዲስ የተማረ እንዲሆን ታዟል

ረ. አ ጰስ ቆጰሱን የሚመርጡት 30 ዘመን የሆናቸው ናቸው /ፍት.ነገ.አንቀጽ 5፣ ጠሰ.28/::

ሰ. ኤ ጰስ ቆጰስ የሚሾም በሚሾምበት ሀገር ምእመናን ምርጫና በርዕሰ ሊ ቃ ጳጳሳት ፈ ቃድ ነው:: /ፍት.ነገ.አንቀጽ 5/ «ይሠየም ኤ ጰስ ቆጰስ በኀርየተ ኲሎሙ ሕዝበ ዚአሁ በሥምረተ መንፈስ ቅዱስ» /ፍት.ነገ አንቀጽ 5 ድስቅ 36/ «እመሰ ብእሲ ዘአምጽዕዎ ከመ ይሰየም ኤ ጰስ ቆጰስ ወይኩን ዝንቱ በሥምረተ ሰብአ ብሔሩ ኵሎሙ ወይኩን ዝንቱ ጳጳስ ርዕሰ ሊቀጳጳሳት ዘይሰየም ...» /ፍት.ነገ.አንቀጽ 5 ረስጣ/ አብጥሊስ/2/::

ሸ. ካህናትና ሕዝቡ እንዲሾምላቸው ኤ ጰስ ቆጰስ የሚሆነውን ቆሞስ መርጠው ሲያቀርቡ ስለደግነቱና ት ሩፋቱ ስለንጽሕናውና ከነውር የራቀ ስለመሆኑ ርዕሰ ሊ ቃ ጳጳሳቱ ሦስት ጊዜ እየመላለሰ ማረጋገጫ ይጠይ ቃቸዋል:: ሕዝቡም አረጋግጠው «የሚባለው ነው» ብለው ሦስት ጊዜ መልስ ይሰጣሉ:: በሦስተኛው ሕዝቡ መልስ ሲሰጡ እጃቸውን አንሥተው «ይገባዋል» እያሉ ያጨበጭባሉ:: ወይም አመልጥ ነው «አማን በአማን» እያሉ ያሸበሽባሉ:: ካጨበጨቡ በ ኋ ተ ቋሞ ቢነሣ ያስታር ቋሉ እንጂ ተቀባይነት የለውም:: /ፍት.ነገ.አንቀጽ 5 ረስጠብ 52/

ቀ. በሹመቱ ጊዜ ሦስት ወይም ሁለት ኤ ጰስ ቆጳሳት ከርዕሰ ሊ ቃ ጳጳሳት ጋር አብረው ይሾማሉ:: አንብሮተ እድ ያደርጋሉ:: «ወየሃልዉ ለሢመተ ኤ ጰስ ቆጳሳት ክልኤቱ አው ሠለስቱ እስመ ዝንቱ ውእቱ ዘይዌስክ ሞገሰ» /ፍት.ነገ.አንቀጽ 5 ረስጣ/ አብጥሊስ 2/

«ወየሀለዉ ከመ ይሢምዎ ክልኤቱ ኤ ጰስ ቆጳሳት እው ሠለስቱ» /ፍት.ነገ.5 ረስጣ 3/

በ. ጋኔን ያደረበት ሰው ኤ ጰስ ቆጰስነት አይሾምም:: «ኢይደሉ ከመ ይኩን ኤ ጰስ ቆጰስ ዘጋኔን» /3 ቀሌ 2/

ተ. ዕውር፣ ደንቆሮ፣ ሰነፍ ዝንጉ ኤ ጰስ ቆጰስ አይሆንም «ወኢይደሉ ከመ ይኩን ዕውር ወኢጽሙም ወኢዝንጉዕ «3 ቀሌ 52፣ ፍት፣ መን፣5/

ቸ. ደግነቱ ያልታወቀ፣ በራሱ ፈ ቃድ አባለዘሩን የሰለበ፣ ቀድሞ ሳያምን ኖሮ በ ኋ የተጠመቀ፣ ኃጢአተኛ ሁኖ በ ኋ ያገባ፣ ኤ ጰስ ቆጰስነት አይሾምም:: /ፍት.መን.5፣ ረስጠጅ /3፣ ቀሌ 75/

ኀ. ኤ ጰስ ቆጰስ ከአንድ ኤ ጰስ ቆጰስ አይሾምም:: «ወኢይደሉ ከመ ይሠየም ለክሙ እምአሐዱ ኤ ጰስ ቆጰስ አሐዱ ዘእንበለ እዴሁ ሳእሌሁ ይትፈለጥ» /ፍት.መን.አን5፣ ረስጣ 58፣ ድስቅ 34/

ነ. አንድ ዓይና እና አንካሳ ኤ ጰስ ቆጰስነት ከመሾም አይከለከልም:: ይኸውም አንካሳው ዞሮ የሚያጥን፣ ዐውድ የማይጥል፣ አንድ ዓይናው ቀለም የማይጥል ፍታቴ

የሚያደላድል ከሆነ ነው። «ወኢይትከላዕ ከመ ይኩን ኤጲስ ቆጶስ ነቋር፣ ወኢሐንካስ፣ ለእመ ኮነ ይሜኒ ዝግብር /ፍት.መን.5፣ ረስጠጅ /3.ቀሌ/አንቀጽ 72/።

ኘ. ኤጲስ ቆጶስ፣ የሚሾመው እሑድ ቀን ነው፤ ተሿሚውን በሚገባ ወንበር ያስቀምጡታል። «ወይሠየም ኤጲስ ቆጶስ በዕለተ እሑድ» /ፍት.መን.ድስቅ37/

አ. ኤጲስ ቆጶስ ሲሾም ካህናቱም ሕዝቡም በሙሉ ተገኝተው እየመሰከሩለት ነው የሚሾመው። «ወኩሉ ሰብአ ይኅበሩ በእንተ ተሰይሞቱ ሕዝበ ወካህናት እንዘ ስምዐ ይከውን ሎቱ» /ፍት.መን.5/

ከ. በአንብሮተ እድ ኤጲስ ቆጶሱን ሲሾሙ የተሰበሰቡ ኤጲስ ቆጶሳት እጃቸውን ይታጠባሉ። ከታጠቡ በኋላ በአንብሮተ እድ ይሾሙታል። «ወኤጲስ ቆጶሳትኒ እለ መጽኡ ከመ ያንብሩ እደዊሆሙ ዲቤሁ ይትሐፀቡ እደዊሆሙ ወእምዝ ይሜምዎ» ፍት.መን.አን.5/

ኸ. ኤጲስ ቆጶሳት በአንብሮተ እድ ሲሾሙት ሕዝቡ በፍርሃት ጸጥ ብለው ይቆማሉ። «ወሕዝብ ቀዊሞሙ በአርምሞ ወበፍርሃት ያንሥኡ ወያነብሩ ኤጲስ ቆጶሳት እደዊሆሙ ዲቤሁ።» /ፍት.መን.5/

ወ. ኤጲስ ቆጶሳት በአንብሮተ እድ ሲሾሙ «ንህነ ናነብር እደዊነ ዲበ ዝንቱ ገብር ኅሩይ ዘእግዚአብሔር በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» እያሉ የቡራኬ ቃላት እየተናገሩ ነው። /ፍት.መን.አን.5/

ዐ. ኤጲስ ቆጶሳቱ የአንብሮተ እዱን ጸሎተ ቡራኬ ከፈጸሙ በኋላ ለተሿሚው መስቀል ይሰጡታል /ፍት.መን.5/

ዘ. ኤጲስ ቆጶሳቱ በአንብሮተ እድ በሚሾሙበት ጊዜ በመጀመሪያ የተሾመው ኤጲስ ቆጶስ ካለ ከርእሰ ሊቃ ጳጳሳቱ ቀጥሎ በቅድሚያ አንብሮተ እድ ያደርጋል፣ እጁን በራሱ ላይ ይጭናል። «ወእምድኅረ ዝንቱ ያንብር ኤጲስ ቆጶስ ቀዳማዊ እምኔሁ እዴሁ ዲቤሁ» /ፍት.መን.አን.5/

ዠ. ከዚህ በኋላ ጸሎተ ሢመቱን ርእሰ ሊቃ ጳጳሳቱ ይጸልያል፣ ሕዝቡ አሜን ይላሉ /ፍት.መን.አን.5/

አ. ጸሎተ ሢመቱም ሲያበቃ ኤጲስ ቆጶሳቱ ተሿሚውን እጅ ይነሡታል፤ ርዕሰ ሊቃ ጳጳሳቱ በአንብሮተ እድ በንፍሐት መንፈስ ቅዱስ ያሳድርበታል። በዚህ ጊዜ ካህናቱና ሕዝቡ «ይደልዎ፣ ይደልዎ፣» ይላሉ። ይህንን ምስክርነት በከፍተኛ ድምፅ እያሰሙ ካህናቱና ሕዝቡ ተሿሚውን እጅ ይነሡታል።

ደ. «በእንተ ሰላምን» ይጸልዩለታል፣ ከዚህ በኋላ ሥጋውን የሚያወሱ መጻሕፍት እየጸለዩ ያነብባሉ፣ ዲያቆናት በሚሾመው ራስ ላይ ወንጌል ዘርግተው ይይዛሉ፣ ጸሎተ ሢመቱ ሲፈጸም ሕዝቡ ሁሉ እጅ እየነሡ መስቀሉን ይሳለማሉ።

ጀ. ከዚህ በኋላ ቅዳሴ ባስልዮስን መቀደስ እንዲገባ ታዟል። ሥጋ ወደሙን መጀመሪያ የሚቀበለው አዲሱ ተሿሚ ነው።

ገ. ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ ሦስት ቀን በዓል ይከበርለታል /ፍት.መን.አን.5/።

ጠ. ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ ሦስት ሱባኤ ይጾማል፣ የተሾመበት ጊዜ በዓለ 50 ከሆነ በዚያ ጊዜ መጾም ስለማይችል አሳልፎ በዚያው ዓመት በየሱባኤው ሦስት ሦስት ቀን ጾሞ ይጨርሳል። /«ወእምከመ ተሠይመ ኤጲስ ቆጶስ ይንበር ሠለስተ ሱባኤያተ በጾም ዝንቱ ለእመ ኮነ በመዋዕለ 50... እምዝነ ይፈጽም ይእተ ዓመተ በጾም በበሠለስቱ» /ፍት.መን.አን.5/።

ጨ. በማስተማር ጊዜ መጻሕፍትን የሚያነብ፣ ኦሪትን፣ ነቢያትን፣ ወንጌልን፣ መጻሕፍተ ሊቃውንትና፣ ምዕራፍን፣ አንቀጹን እየለየ የሚተረጉም፣ ዘወትር የሚያስተምር ንጹሕ ትጉህ እንዲሆን ታዟል /ፍት.መን.አ.5/

ጰ ኤጲስ ቆጶስ በሃይማኖት ወደማይመስሉ ወደ አሕዛብ በዓል እንዳይሄድና እንዳያከብር ተከልክሏል። /«ወኢይሑር ኀበ በዓላተ አሕዛብ» /ፍት.መን.አን.5/

ጸ. ኤጲስ ቆጶስ ሕዝቡን በምሳሌነት ለማስተማር ሁሉንም የሚወድ ፣ ቂም በቀል የማይዝ፣ ኀዳጌ በቀል፣ ልበ ሰፊ፣ ነገር አላፊ መሆን አለበት። ከማንኛውም መንፈሳዊ ሥራ ካልሆነው የሰይጣን ሥራ ከሆነው ነገር ሁሉ መጠበቅ እንዳለበት ታዟል። ኤጲስ ቆጶሱ ደግ ከሆነ ብዙ ሰዎችን ወደሱ መሳብ ይችላል። «ወይኩን ፍቁረ ለኲሉ እስመ ኖላዊ ዘእምርሁቅ እምዓመፃ ይስሕቦሙ ለአርዳኢሁ...» እንዲል /ፍት.ነገ.አን.5/ ድስቅ 8። ሆሴዕ /49/

ፀ. ኤጲስ ቆጶስ ከተሾመ በኋላ ቤተክርስቲያንን ዘወትር ያገለግላል። በመዓልትም በሌሊትም ስለራሱና ስለሕዝቡ ስለ ሀገሩና ስለዓለሙ ይጸልይ ዘንድ ታዟል። በቤተክርስቲያን ብቻውን ይኖራል ማለት ቤቱ ከቤተክርስቲያን አጠገብ ያደርጋል። ካስፈለገው በጸሎተ ማኅበር የሚረዱት አንድ ሰው ሁለት ሰው በቤቱ ለማኖር ይችላል።

«ወለእመ ኮነ ሎቱ ዘያሠምሮ ለነቢር ምስሌሁ አመ አኮ አሐዱ አው ክልኤቱ ወውእቶሙ አሐቲ ነፍስ ምስሌሁ ይግበር በዘይትራድእዎ በእንተ ዘይደሉ» ፍት.ነገ.5

ቀ. ኤጲስ ቆጶስ ቀሳውስትን ይባርካል:: እሱ ግን በቀሳውስት አይባረክም «ኤጲስ ቆጶስ ይባርክ ወኢይባርኩ ኪያሁ» /ፍት.ነገ.5 ረስጣ/ ቀሌ.21

ኀ. ከኤጲስ ቆጶስ ከቀሳውስት እስከ ኀፃዌ ኆኅት ያለውን ሹመት ይሾማል:: ነገር ግን ሳይመረምር ሳይፈትን ማንንም ክህነት እንዳይሾም ተከልክሏል:: «ወኢታፍጥን አንብሮ እዴከ ላዕለ አሐዱሂ ወኢትሳተፍ በዝንቱ ኀጢአተ ካልዕከ» /1ኛጢሞ.5÷22፣ ፍት.ነገ5 ክፍል 4/

ከ. ከኤጲስ ቆጶስ በስተቀር መሻር የሚገባውን ካህን ይሽራል /ፍት.ነገ.አን.5 ክፍል4/ እግዚአብሔር እንደሾመው ኖላዊነት በእሱ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡም ኀጢአት ስለሚጠየቅ ተግቶ ማስተማርና ሕዝቡን ከኃጢአት መጠበቅ እንዳለበት ታዟል::

«አንተሰ ዖርከ ዖረ ክቡደ ጽሑፍ ከመ እግዚአብሔር ይቤሎሙ ለሙሴ አንተ ወአሮን ትፀውሩ አበሳሆሙ ለሕዝብ... ወሰበ መጽአ ኅቤከ ዘሀለወ ቦቱ ዐቢይ አበሳ ኢትትሀይይ ኪያሁ ይቤ ሕዝቅኤል ነቢይ በእንተ ኤጲስ ቆጶስ ዘይትሄየይ እንበይነ ሕዝብ አሌ ሎሙ ለኖሎተ እስራኤል እለ ኀደጉ አባግኢሆሙ ዘይርእዩ ለእለ አሐዱ አኮኑ አንትሙ ኖሎት ዘትርእዩ አባግዐ ወአንትሙ ለሀሊብ ትስትይዎ ወለጸምር ዘትለብስዎ ወመግዝዕኒ ስቡሕ ዘትጠብህዎ ለአባግዕየሰ ኢትርእዩ...» ሕዝ.34-1-19፣ ፍት.ነገ.አን.5/

ኊ ኤጲስ ቆጶስ ስሙ በጸሎት ላይ ይጠራል:: በቅዳሴም ይነሣል /ፍት.ነገ.አን.5/

ኋ. ኤጲስ ቆጶስ ሥጋው ደሙን ከኤጲስ ቆጶሳት እንጂ ከቀሳውስት አይቀበልም:: /ፍት.ነገ.5 ክፍል 4/

ኌ. በካህናት መካከል እኔ በላይ እኔ በላይ ልቀመጥ በማለት ጠብ ክርክር እንዳይሆን ካህናትም በማዕረግ ከሕዝቡ ጋር አንድ እንዳይሆኑ ሊቃ ካህናት ከተራ ካህናት ጋር እኩል እንዳይሆኑ የካህናቱን ማዕረግና መቆሚያቸውን ማወቅ ጽፎ መያዝ እንደሚገባው ታዟል:: «ወይደልዎ ከመ ይጸሐፍ ወያአምር ኵሎ ማዕረጋተ ካህናት ወሥርዓታቲሆሙ ከመ ኢይኩን ማዕከሌሆሙ ጋዕዝ በዝንቱ ግብር ወከመ ኢይደመሩ ስብአ ቤተክርስቲያን እንተ ሐዋርያት ምስለ ሕዝባውያን በማዕረግ ወከመ ኢይኩኑ ምስለ ሊቃ ካህናት በአምሳሊሆሙ» /የኒቅያ ሲኖዶስ/ አን 67/

ኍ. ኤጲስ ቆጶስ የተሾመበትን ሀገር ከተማና ገጠር ትቶ በሌላ ሀገር እንዲቀመጥ አልተፈቀደም «ወኢደልዎ ለኤጲስ ቆጶስ ከመይኅድግ መንበሮ ወሀገሮ ወይሑር ኀበ ካልዕ ሀገር» / ቀሌ.11/

ኗ. ኤጲስ ቆጶስ የተሾመበትን ሀገር ለቆ ወደሌላ ሀገር መዛወር እንደሌለበት ባል ሚስቱን ፈትቶ ሌላ ማግባት የማይገባውን ያህል አይገባውም ተብሎ ታዟል። /ጉባኤ.ኒ.ቂያ77/

ኘ. ኤጲስ ቆጶስ ቢያጠፋ ያላመኑ ሰዎች ምስክርነት ወይም የአንድ አጲስ ቆጶስ ምስክርነት አይሰማበትም። /3 ቀለ.አን.70-2 ጠሌ.12./

## ጉባኤ ኤጲስ ቆጶሳት/ሲኖዶስ/

ሀ. ኤጲስ ቆጶሳት በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባሉ። «ወይኩን ጉባኤ ኤጲስ ቆጶሳት ክልዔተ ጊዜ በበዓመት» /ፍት.መን.አን.5፣ ክፍል 5። ረስጠብ 27። አስጠጅ 28። ዶክ.28

ለ. የመጀመሪያው ጉባኤ በበዓለ ሃምሳ በአራተኛው ሱባኤ በአራተኛው ቀን ይደረጋል፤ ይኸውም ርክበ ካህናት በሚውልበት ዕለት ማለት ነው። ሁለተኛው ጉባኤ ጥቅምት በባተ በ12ኛው ቀን ይደረጋል፤ ይህም ዕለተ ዕረፍቱ ለማቴዎስ ነው። «ወጊዜ ቀዳሚት ጉባኤ በራብዕ ሱባኤ እም ሃምሳ፣ ወዳግሚትኒ አመ አሠርቱ ወክልዔቱ ለጥቅምት»/ፍት.መን.5. ክፍል 5/ «ይትጋብኡ ኤጲስ ቆጶሳት ዘኩሉ መካናት ኀበ ጳጳሰሙ አው ኀበ ሊቃ ጳጳሳቲሆሙ ክልኤተ ጊዜ በኩሉ ዓመታት» /ፍት.መን.አን... 5 ኒቂያ 9። 45/

ሐ. በጉባኤው መካከል አንድ መንበር ተደርጎ በላዩ ላይ ወንጌል ይቀመጣል፤ ርእሰ ሊቃ ጳጳሳቱ በፊት ለፊት ይቀመጣል፤ በር ይዘጋና ኤጲስ ቆጶሳት ተነሥተው የማኅበር ጸሎት ያደርጋሉ፤ ጸሎቱ ሲያልቅ ሂደው ይቀመጣሉ፣ ከዚያ በኋላ ስለ ሃይማኖት መጽናት ስለ በጎ ምግባር መስፋፋት ስለ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን መጽናት፣ በጠቅላላው ስለ መንፈሳዊ ሕግና ፍትሕ ተነጋግረው ውሳኔ ይሰጣሉ። «ወያንብሩ ማዕከለ ምርፋቆሙ አሐደ መንበረ፣ ወያንብርዎ ዲቤሁ ለወንጌል ቅዱስ፣ ወይንበር ሊቀ ጳጳሳት በቅድሜሁ ወይዕፀው አናቅፀ ወይትነሥኡ ኅቡረ ወይጸልዩ ወይገብኡ ኀበ ምርፋቆሙ ወይሐትቱ በእንተ ግብር ዘተጋብኡ በእንቲአሁ በኅቡዕ» /ፍት.አን.5 ክፍል 5/

## ሐ. የሢመተ ቀሳውስት ሥርዓት/ለቅስና ሹመት የሚያበቁ ሁኔታዎች

ሀ. ለቅስና የሚመረጥ ዲያቆን ነውርና ነቀፋ የሌለበት፣ አንዲት ድንግል ሴት ያገባ፣ ደጎች ልጆች ያሉት፣ ቂመኛ ያልሆነ፣ አብዝቶ የማይጠጣ፣ እጁን ለመማታት አንደበቱን ለመገዘት የማያፈጥን፣ ገንዘብ የማይወድ፣ እንግዳ የሚቀበል፣ በጐ ሥራን የሚያፈቅር፣ ከኃጢአት የነጻ፣ ደግና ቸር የሆነ ሰውነቱን ከፍትወት ያራቀ፣ የጌታ ወንጌልን በማስተማር ምእመናንን የሚረዳ እውነተኛ ትምህርት በማስተማር ሰውን ማጽናናት የሚቻለው፣ክደው ሊያስክዱ የሚተናኰሉትን

የሚከራከራቸው መሆን እንዳለበት ተሠርቷል:: /ፍት.መን.አን 5 ክፍል 1 ዘሌ.21-7-16/

ለ. ሠላሳ ዓመት ያልሞላው እንዳይሾም ተከልክሏል:: «ኢይሠየም ቀሲስ ዘእንበለ በሰላሳ ዓመት /ፍት.መን.6 ቀጠግ 11/

ሐ. ብሉያትን ሐዲሳትን ያልተማረ ይልቁኑም አራቱን ወንጌል ያላወቀ ቅስና እንዳይሾም ተከልክሏል:: «ወኢይኩን አሐዱሂ ቀሲስ ዘኢየአምር ነገረ መጻሕፍት እምላካውያት ሠናያት ወፈድፋደሰ አርባዕተ ወንጌላተ»/ፍት.መን.አን.6 በሰ 89/::

## ሢመተ ቅስና

ሀ. ኤጲስ ቆጶስ ቄሱን በአንብሮተ እድ ይሾመዋል፣ ቀሳውስት ቆመው ይዳስሱታል፣ ይጸልዩለታል፣ ቄስ፣ ዲያቆን፣ ንፍቀ ዲያቆንና ከዚያ በታች ያሉት የሚሾሙት በኤጲስ ቆጶስ ብቻ ነው፣ ኤጲስ ቆጶሱ እነዚህን ሲሾም የማዕረጋቸውንና የሥርዓተ ክህነታቸውን ደረጃ ጠብቆ በሕዝብ ፊት ጸሎተ ሲመቱን አድርሶ ይሾማቸዋል:: «ወለእመ ፈቀደ ኤጲስ ቆጶስ ከመ ይሢም ቀሲስ ያንብር እዴሁ ላእለ ርእሱ ወቀሳውስትኒ ኵሎሙ ይግስስዎ ቀዊሞሙ ወይጸልዩ ላእሌሁ» /ፍት.መን.አን.6 ክፍል 9 ረስጣ 22-54/::

ለ. ኤጲስ ቆጶስ ሳይፈቅድ ቄስና ዲያቆን አይሾምም:: ወኢይሰየም ቀሲስ አው ዲያቆን ዘእንበለ በምክረ ኤጲስ ቆጶስ ዘውእቶሙ ታኅተ ሥልጣኑ ወይሢም ኤጲስ ቆጶስ ባሕቲቱ እስመ ሣልሳይ ማዕረጊሁ»

## የቀሳውስት ተግባርና ሥልጣን

ሀ. ቄስ መምህር ነው:: መምህርም እንደመሆኑ የቀናች ሃይማኖትን ያስተምራል:: «እስመ ቀሲስ በአምሳለ መምህር:: ወይኩኑ ቀሳውስት በኀቤክሙ መምህራነ ለአእምሮተ እግዚአብሔር:: /ፍት.መን.አን.6 ድስቅ 27/

ለ. ቄስ ሥራው ማስተማር፣ ማጥመቅ፣ ቀድሶ ማቁረብ፣ መባረክ፣ ማሠርና መፍታት፣ ማናዘዝ ነው:: /ፍት.መን.አን.6 ክፍል 3/

ሐ. ቄስ በአንብሮተ እድ ሕዝቡን ይባርካል:: «ወይባርክ ወኢይትባረክ እምዘ ውእቱ ይንእስ» /ፍት.መን.አን.8 ረስጣ 58/

መ. ቄስ ሥልጣነ ክህነት አይሾምም አይሽርም:: /ፍት.መን.6 ክፍል 3/

## ትእዛዘ ቀሳውስት

ሀ. ቄስ ምእመናንን መጠበቅ፣ ሲታመሙ መጠየቅ፣ በትምህርት ማጽናት እንደሚገባው ታዟል። እውነተኛ ፍርድ መፍረድ ይገባዋል /ፍት.መን.አን.6 ክፍል 4/

ለ. በመሠዊያው ቀኝ የሚቆሙ ቀሳውስት ካህናቱን ያስተናብራሉ፤ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉትን በየተራቸው እንዲቀበሉ ይቆጣጠራሉ። በግራ የሚቆሙ ቀሳውስት ሕዝቡን ያስተናብራሉ። «ወቀሳውስት እለ ውስተ የማን ያስተሐምሙ ለረድኤት በውስተ ምሥዋዕ ከመ ያከብርዎ ለዘይደልዎ ክብር ወይመንንዎ ለዘይደልዎ ምናኔ ወቀሳውስትሰ እለ ውስተ ጸጋም ያስተሐምሙ በእንተ ጉባኤ ከመ ይኩኑ ብጹዓነ» /ፍት.መን.አን.6 ክፍል 4/

ሐ. ቀሳውስት ሐዋርያት ከሠሩት ሥርዓት ውጭ ትእዛዝ በማክበድ ሕዝቡን እንዳያስጨንቁ ታዘዋል። «ወኢይወስክ አሐዱ እምቀሳውስት ምንተኒ ከቡደ ውጹአ እምቀኖና አበዊነ ሐዋርያት።» /ፍት.መን.6 በስ 51/

መ. ቄስ ታሞ በሚመረመርበት በሚታከምበት ጊዜ ከአልሆነ በስተቀር በማንም ጊዜ ፈጽሞ ዕር ቃሉን ሊጥልና ሊጋለጥ አይገባውም። «ወኢይተዓረቅ ቀሲስ ግሙራ ቅድመ መኑሂ እምሰብእ ዘእንበለ በጊዜ ዐጸባ» /ፍት.መን.አን.6 ክፍል 4 በስ 53/

ሠ. ቀሳውስት ከኤጴስ ቆጶሱ ዘንድ በየዓመቱ ሦስት ጊዜ እንዲሰበሰቡ ታዘዋል። «ወይትጋብኡ ቀሳውስት ኀበ ኤጴስ ቆጶሳ ተሀሙ ሠለስተ ጊዜያተ በበዓመት» ፍት.መን.አን.6 ክፍል 4 ኒቅያ 59

ረ. ካህናት የራስ ጠጉራቸውን ማሳደግና ማጐፈር አይገባቸውም።

## ቀሳውስት ከሹመት የሚሻሩበት ሥርዓት

ሀ. በሥርዓተ ቤተክርስቲያን ሊጠብቀው የታዘዘውን የማይጠብቅ፣ እንዳይሠራው የተከለከለውን የሚሠራ፣ በሥርዓተ ቤተክርስቲያን ሕዝቡን የማያስተምርና የማይመራ ቄስ ቢኖር ከክህነቱ ይሻራል/ ፍት.መን.አን.6 ክፍል 5/

ለ. ሁለት ጊዜ የተሾመ፣ ሁለት ጊዜ ያገባ፣ ወይም ሁለት ሚስት ያለው ሕዝቡን የማያስተምር፣ የተቸገሩትን ካህናት የማይረዳ፣ ጉቦ ሰጥቶ የተሾመ፣ የኃጢአተኛውን ንስሐ የማይቀበል፣ በሐሰት የሚመሰክር፣ ሰውን የሚያጣላ፣ የሚኮራ፣ የክፋትን ሥራ የሚሠራ የሚሰክር፣ ኮከብ የሚቆጥር፣ አራጣ /ወለድ/ የሚቀበል፣ በሐሰት የሚምል፣ የጠንቋዮችን ነገር እውነት ነው ብሎ የሚቀበል፣ ከሴሰኛ ሴት የደረሰ፣ ሥር የማስ፣ ቅጠል የበጠሰ፣ ሰውን የሚማታ፣ ከመናፍ ቃን የተጠመቀ፣ የሰረቀ፣ የመናፍ ቃን ቁርባን የተቀበለ፣ አብሮአቸው የጸለየ፣ አባለ ዘሩን የሰለበ፣ ሲሰስን፣ በሐሰት ሲምል የተገኘ፣ በገበያ መካከል

የሚበላ፣ በመሸታ ቤት የሚጠጣ፣ የበከተውንና የአውሬውን ትራፊ የሚበላ፣ ከአይሁድ ምኩራብ ከአላውያን ቤተጸሎት የሚገባ፣ የአይሁድን ጾም የሚጾም፣ በዓላቸውን የሚያከብር፣ የበዓላቸውን እጅ መንሻ የሚቀበል፣ ሃይማኖታቸውን ወደለወጡ ሰዎች ቤተጸሎት ሄዶእጅ መንሻ የሚቀበል፣ ከተወገዘ ሰው ጋር የተነጋገረ፣ አብሮት የጸለየ፣ የኤጴስ ቆጶሱን ደብዳቤ ሳይዝ ሩቅ አገር የሄደ፣ በአገልግሎት ምክንያት ሚስቱን የተለየና የፈታ፣ እመነኩሳለሁ ተባሕትዎ እይዛለሁ ብሎ ሚስቱን የተወ፣ ያሰናበተ ካህን ከሹመቱ ይሻራል:: /ፍት.ነገ.አን.6 56 ክፍ5:: 2 ቀሌ.3::፣ 3 ቀለ.5/

ሐ. ቄስም ሆነ ዲያቆን ከሹመቱ በኃጢአት ከተሻረ በኋላ ደፍሮ ለአገልግሎት ቢገባ ከቤተክርስቲያን ተወግዞ ከምእመናን ይለያል:: እያወቁ በዚህ ድፍረቱ የተባበሩት ሁሉ ከምእመናን ይለያሉ /ፍት.ነገ.6 ረስጠብ/2 ቀሌ.19/

መ. ቄስ ወይም ዲያቆን በሀገሩ የተሾመውን ኤጴስ ቆጶስ ንቆ አ ቃሎ ለብቻው ቤተክርስቲያን ከሠራ፣ ኤጴስ ቆጶሱ እስከ ሦስት ጊዜ ጠ ርቶት ካልመጣ፣ እሱና የመሰሰሉት ከሹመታቸው ይሻራሉ:: /ፍት.መን.6 ረስጠብ/2 ቀሌ.22/

ሠ. ቄስ ያለበትን ቤተክርስቲያን ትቶ ወደሌላ ቤተክርስቲያን ከሄደ፣ እንዲመለስ ተነግሮት፣ ካልተመለሰ ከሹመቱ ይሻራል /-ፍት.መን.6:: /ረስጣ/1፣ ቀሌ/14፣ ኒቂያ 4/

ረ. ቄስ በቁጣ ወይም በማናቸውም ምክንያት ምእመናንን ሥጋ ወደሙን ከከለከለ ከሥልጣኑ ይሻራል:: /ፍት.መን.አን.6 ክፍል 5 ኒቅያ 27/

ሰ. ቀሳውስት ዲያቆናት በሥጋዊ ነገር ዋስ፣ ተያዥ ምስክር፣ አይሆኑም ይህን ያደረገ ከሹመቱ ይሻራል:: /ፍት.መን.6 ክፍል 6 ኒቂያ 28/

## የሢመተ ዲያቆናት ሥርዓት

1. ስዲቁና ሢመት የሚያበቁ ሁኔታዎች

   ሀ. ዲያቆናት ጭምቶች፣ ትዕግሥተኞች፣ ግብረ ገብነት ያላቸውና የሚታዘዙ፣ ሁለት ቃል የማይናገሩ፣ ማለት አንድ ጊዜ እውነት አንድ ጊዜ ሐሰት የማይናገሩ እብዝተው ወይን የማይጠጡ፣ የማይገባ ትርፍ ገንዘብ መቀበል የማይሹ፣ ንጹሕ በሆነ ልቡና ሃይማኖትን የተረዱ፣ ጋብቻ ያልደገሙ፣ ልጆቻቸውን ቤተሰቦቻቸውን ቀጥተው ያሳደጉ መሆን ይገባቸዋል:: በዚህ ሁሉ የተፈተኑና ነውር የሌለባቸው ሆነው ሲገኙ ዲቁና ይሾማሉ:: /1ጢሞ.9÷13 ፍት.መን.7፣ ፍት.መን.7 ክፍል 1 ጢሞ.7÷4/::

   ለ. በሥርዓተ ቤተክርስቲያን መሠረት ለማዕረገ ዲቁና መብ ቃታቸው ተመስክሮላቸው እንዲሾሙ ታዘዋል:: /ፍት.ነገ.7 ረስጣ 17

ሐ. ከዚህ ጋር ለሰው የሚራሩ፣ የሚያዝኑ፣ የማያንጐራጉሩ፣ ከቂም በቀል የራቁ፣ ቁጡዎች፣ ብስጩዎች ያልሆኑ፣ የማያዳሉ፣ ለመማርና ለማስተማር የተጉ እንዲሆኑ ታዘዋል /ፍት.መን.አን.6 ክፍል 1/

## ሢመተ ዲቁና

ሀ. ዲያቆን በአንብሮተ እድ ይሾማል «ሶበ ትሠይሞ ለዲያቆን አንብር እዴከ ላዕሌሁ ወጸሊ» /ፍት.መን.አን.7 ክፍል2 ረስጣ 54 ቅጠግ 54/

ለ. ዲያቆናት ሲሾሙ ቀሳውስትና ዲያቆናት ከኤጴስ ቆጶስ ጋር ሆነው አብረው ይጸልያሉ:: አንብሮተ እድ የሚያደርግለት ግን ኤጴስ ቆጶስ ብቻ ነው:: «ቀሳውስት ኩሎሙ ወዲያቆናትኒ እንዘ ይቀውሙ ይጸልዩ» ፍት.መን.አን.7 ክፍል 2 ረስጣ 54 ቅጠግ 14/

ሐ. «ዲያቆን 25 ዓመት ሳይሞላው አይሾምም» ይላል፣ ይሁን እንጂ ብቁ ሆኖ ከተገኘ ከዚህ ዕድሜ በታችም ያለ ቢሆን ይሾማል:: /ፍት.መን.አን.7 ክፍል 2 ዋጠግ 11/

መ. የዲያቆናቱ ቁጥር በቤተክርስቲያኑ ሰበካ ስፋትና ጥበት ይወሰናል:: /ፍት.መን.አን.7 ቀጠግ 14 ኒቅያ 67/

## የዲያቆናት ሕይወትና ሥርዓት

ሀ. ዲያቆናት እንደ ኤጴስ ቆጶስ እንደ ቄስ ያለነውር ነቀፋ መኖር አለባቸው:: «ወይኩኑ ካዕበ ዲያቆናት ዘእንበለ ነውር በአምሳለ ኤጴስ ቆጶስ ወይኩኑ ፍጹማነ በክህነቶሙ ለቤተክርስቲያን በዘይክሉ ገቢረ ዘእንበለ ሀፍረት»

ለ. ዲያቆናት በቦታው ሁሉ በመዓልትም በሌሊትም በጎ ሥራን የሚሠሩ መሆን ይገባቸዋል:: ከኃጢአት ንጹሕ ሆኖ መልካም አገልግሎት የሚያገለግል ዲያቆን ይረባል፣ ይጠቅማል፣ በጎ ዕድል ፈንታ ያገኛል:: /ፍት.መን.አን.7 ክፍል 4 ረስጣ 18/

ሐ. ዲያቆን የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደመሆኑ መጠን ለኤጴስ ቆጶሱ ለቄሱ ይላላካል:: «ወዲያቆንሰ ከመ ዘይትለአክ ለእግዚአብሔር ይትለአክ ለኤጴስ ቆጶስ ወለቀሳውስት በኩሉ ግብሮ» /ፍት.መን.አን.7 በዲ.5/::

መ. ዲያቆን ሕሙማንን በመጐብኘት፣ የችግረኞችን ጉዳይ ወደ ቄሱ ወደ ኤጴስ ቆጶሱ በማቅረብ ለችግረኞች ምጽዋት የሚሰጡትን ምእመናንን ሁሉ በማስተባበርና በመላላክ እንዲያገለግል ታዞአል:: /ፍት.መን.አን.7 ክፍል 3/

ሠ. በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዲያቆናት ወንጌል ያነብባሉ፣ በእኛ ቤተክርስቲያን አያነቡም:: «ወያነብብ ወንጌለ እመሂ ዲያቆን ወእመሂ ቀሲስ» ዲድስቅልያ 12 ፍት.መን.አን.6 ክፍል 3/

ረ. ዲያቆን በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ ሕዝቡ ሥርዓት ይዘው እንዲቆሙና እንዲጸልዩ እንዳያንቀላፉ እንዳይተቹ፣ እንዳይስቁና እንዳይሳለቁ ይቆጣጠራል /ፍት.መን.አን.12 ድስቅ 12/

ሰ. ሥጋውን ደሙን በማቀበል ጊዜ ሥጋውን ቄሱ ሲያቀብል ዲያቆን ደሙን ለሕዝቡ ያቀብላል /ፍት.መን.አን 7 ክፍል 3 ረስጠ 58/

ሸ. ቆሞሱና ሊቀ ዲያቆናቱ ለኤጲስ ቆጶስ እንደ ሁለት እጆች እንደ ሁለት ክንፎች ሆነው ሹመት በሚሰጥበት ጊዜ በቀኙና በግራው ይቆማሉ:: ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄድ አብረው ይሄዳሉ፣ ወደ ሌላም ቦታ ሲሄድ አይለዩም:: ሊ.ቃ ዲያቆናት በቀኙ ይቆማሉ፣ ሌሎች በግራው ይቆማሉ:: /ፍት.መን.አን.7 ኒቅያ 62/

## ዲያቆን ከማዕረጉ የሚሻርበት ምክንያት

ሀ. ጉቦ ሰጥቶ፣ በጉልበት አስገድዶ፣ አስፈራርቶ ወይም ይህን በመሰለ ሌላ ተንኰል የተሾመ ወይም ሁለት ጊዜ የተሾመ፣

ለ. ሁለት ሴት ያገባ፣ ወይም በተሾመ ጊዜ ከሴት ርቄ ንጽሕና ጠብቄ እኖራለሁ ብሎ ተሥሎ የተሾመ በኋላ ሥዕለቱን አፍርሶ፣ ሚስት ያገባ፣ ወይም ከዘማዊት ሴት የደረሰ፣ ተደብቆ ተክሊል ያደረሰ፣ ወይም እመነኩሳለሁ ተባሕትዎ እይዛለሁ ብሎ ሚስቱን የፈታ

ሐ. ዘወትር የሚሰክር፣ በክፉ ሥራ ጸንቶ የሚኖር፣
በሐሰት የሚመሰክር

መ. አራጣ የሚቀበል፣ ነጋዴ የሆነ

ሠ. ባልንጀራውን የሚያማ

ረ. በሰው የሚታበይ፣ ኃይልን የሚያሳይ፣ ሰውን የሚመታ፣ ኤጲስ ቆጶሱ ጠርቶት አልመጣም ብሎ የቀረ፣ ከደሟ ያልነጻችውን ሴት ወደ ቤተክርስቲያን ያስገባ፣ ሥጋውን ደሙን የሰጠ፣ ከተሻረ በኋላ የክህነት ሥራ የሚሠራ፣ ለብቻው ሌላ ቤተክርስቲያን የሠራ

ሰ. ቤተክርስቲያንን ትቶ ከሔደ በኋላ የተመለሰ፣ ከመናፍ ቃን የተጠመቀ፣ ቁርባናቸውን የተቀበለ፣ ከመናፍ ቃን ጋር የጸለየ ቤተክርስቲያኑን ትቶ ወደ ሌላ ቤተክርስቲያን የሔደ ወታደር የሆነ ከዲቁናው ማዕረግ ይሻራል:: /ፍት.መን.አን.7 ክፍል 5/

## ሥርዓተ ሢመቱ ለአናጉንስጢስ

ሀ. አናጉንስጢስ በሚሾምበት ጊዜ አስቀድሞ ኤጲስ ቆጶስ አንብብ ብሎ ወንጌል ይሰጠዋል ፍት.ነገ.አን 7 ክፍል 2 ረስጠ 20/::

ለ. ኤጲስ ቆጶስ አናጉንስጢስ ሲሾም አንብሮተ እድ አያደርግም:: በ ቃሉ ብቻ አናጉንስጢስ ብሎ ይሾመዋል/ ፍት.መን.8 ክፍል 2 ረስጣ 28 በደሰ 7/ ረስ.48

ሐ. አናጉንስጢስ ሚስት ያላገባ ከሆነ ከሴት ርቆ እንደኖረ ካልተመሰከረለት አይሾምም /ፍት. መን.አሩ 7 ክፍል 2/

የአናጉንስጢስ ሥራ

ሀ. አናጉንስጢስ አንባቢ ስለሆነ በቤተክርስቲያን ያነብባል /ፍት.መን.አን.8 ክፍል 3 ድስቅ ቀዳማዊ/::

ለ. አናጉንስጢስ ከፍ ካለ ቦታ ቆሞ ከብሉያት መጻሕፍት በክፍል እየከፈለ እየመጠነ ያነብባል /ፍት.መን.አን.8 ክፍል 3 ድስቅ 12/::

ሐ. አናጉንስጢሳውያን ንባብ በሚያነብቡት ጊዜ ልብሰ ተክህኖ አይለብሱም /ፍት.መን.አን.8 ክፍል 3/::

ስአናጉንስጢስ የሚሻርበት ምክንያት

ሀ. አናጉንስጢስ ከሰረቀ ከሹመቱ ከማንበብ ሥራው ይታገዳል፣ ከዓመት በኋላ ግን ወደ ሥራው ይመለሳል፣ ማዕረግ አይጨመርለትም፣ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በአንባቢነት ማዕረግ ይኖራል /ፍት.መን. አን.8 ክፍል 4፣ በስ.48/ ከተሾመ በኋላ መስንቆ መምታት ሊማር ወደ አንባቢነቱ መመለስ አይገባውም፣ ከተመለሰና በዚሁ ሥራ ከተገኘ በሰባት ሱባኤ ጾም ይቀጣል፣ ካልታረመ ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ይለያል:: /ፍት.መን.አን.8 ክፍል 4 በስ 74/

ሥርዓተ አናጉንስጢስ

አናጉንስጢስ ሚስት ማግባት ይችላል፣ ሚስቱ ከሞተችበት ሁለተኛ ያገባል /ፍት.መን.አን.8 ክፍል 5 ረስጠብ 117 በስ 55/

## የመዘምራን ሢመት ሥርዓት

ኤ ጳስ ቆጳስ መዘምራንን በቡራኬ ይሾማል እንጂ አንብሮተ እድ አያደርግም /ፍት.መን.አን.8 ክፍል 2/

የመዘምራን ሥራ

ሀ. መዘምራን ዘማሪዎች ስለሆኑ ይዘምራሉ /ፍት.መን.አን.8 ክፍል 8/

ለ. መዘምራን የሚዘምሩት ከመዝሙረ ዳዊት ነው:: /ፍት.መን.አን.8 ክፍል 3 ድስቅ 12/ በሀገራችን የቅዱስ ያሬድን ድርሰት ጭምር ይዘምራሉ::/

ሐ. መዘምራን በሚዘምሩበት ጊዜ ልብሰ ተክህኖ አይለብሱም:: /ፍት.መን.አን.8 ክፍል 3/

ሥርዓተ መዘምራን

መዘምራን ሚስት ማግባት ይችላሉ:: ሚስታቸው ከሞተችባቸው ሁለተኛ ማግባት ይችላሉ/ ፍት.መን.አን.8 ክፍል 5 ረስጠብ 17 በስ 55

ሐ. ዲያቆናውያት በሕዝቡ ዘንድ ክብር አላቸው /ወትኩን ዲያቆናዊት ክብርተ /ፍት.መን.አን.8/

መ. ዲያቆናውያት እንደ ዲያቆናት «ተንሥኡ ጸልዩ» እያሉ ጸሎት አያዝዙም፤ ዲያቆን ሳያዝዛቸውም ምንም ነገር አይሠሩም /ፍት.መን.አን.8 ክፍል 3 ረስጣ 6/::

ሠ. ስለማናቸውም ጉዳይ ለመነጋገር አንዲት ሴት ዲያቆናዊትን ሳትይዝ ብቻዋን ወደ ዲያቆን ወይም ወደ ኤጲስ ቆጶስ መሄድ አይገባትም፤ ክልክል ነው/ፍት.መን.አን.8 ክፍል 3 ረስጣ 6::

ረ. ዲያቆናዊት ሴቶችን ልትገሥጽ ልትመክር፣ ልታስተምር በመሳሰለው ሁሉ ልትረዳቸው ይገባል /ፍት.መን.አን.8 ረስጣ 34/::

ሰ. ዲያቆናውያት ቅስና አይሾሙም፣ ቄስ አይባሉም፣ በቤተክርስቲያን የማኅበር ጸሎት ጀማሪ ፈጻሚ አይሆኑም::

ቀ. ዲያቆናውያት ቃላቸውን ከፍ አድርገው ጮኸው አይጸልዩም «ወኢይጸልያ በልዑል ቃል» /ፍት.መን.አን.8 ክፍል 3 ዶቅ11/

## የክህነት ዓላማና ጥቅም

የክህነት ዓላማና ጥቅም ሰዎችን ከኃጢአትና ከሰይጣን ሥራ ሁሉ በመለየት በማስተማር በመቆጣጠር፣ በመጠበቅ፣ በመቀደስና በማንጻት በማናዘዝና በመፍታት

ሀ. ለጨለማው ዓለም ብርሃን ለመሆን

ለ. አልጫ የሆነውን ዓለም ለማጣፈጥ

ሐ. ምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን በመፈጸም ለምእመናን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ለማሰጠት፣ የእግዚአብሔር ልጆች የመንግሥቱ ወራሾች እንዲሆኑ ለማብ ቃትና ድኅነተ ነፍስ ለማሰጠት ነው::

መ እግዚአብሔርን በቅዳሴ፣ በውዳሴ ለማመስገንና መንፈሳዊ አገልግሎት ለመፈጸም ነው::

## ማስታወሻ

- ቤቱን ያላስተዳደረ ክህነት የማይሾምበት ምክንያት ቤቱን ያላሳመረ ቤተሰብ ማስተዳደር ያልቻለ፣ ቤተ እግዚአብሔርን ማስተዳደር ስለማይችል ነው::

  «እስመ ውእቱ ዘኢያሜኒ ሠሪዐ ቤቱ ኢያሜኒ ሠሪዐ ቤተ እግዚአብሔር ወቤተክርስቲያኑ» /1ኛ ጢሞ.3÷4-5 ፍት.ነገ5/::

- ሐዲስ አማኒ ኤጲስ ቆጶስነት እንዳይሾም የተከለከለበት ምክንያት ሰይጣን በአመጣው ትዕቢት እንዳይያዝና እንዳይታበይ ነው::

«በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያን አይሁን።» /1ኛ ጢሞ. 3÷6፣ ፍት.ነገ.አን.5፣3/።

- ዕውር ደንቆሮ ዘንጊ ኤጴስ ቆጶስነት እንዳይሾም የተከለከለው ነውር ሆኖበት አይደለም። በቤተ እግዚአብሔር ከሚሠራው ሥራ እሱ ሊሠራው የሚገባውን ሥራ መሥራት የማይቻለው ስለሆነ ብቻ ነው። «አኮ ከመ ውእቱ ነውር አላ እስመ ውእቱ ኢይክል በእንተ ፈጽሞቱ ለዘውእቱ ይትፈቀድ እምግብረ ቤተክርስቲያን» /3ቀሌ አንቀጽ 52፣ ፍት.ነገ.አንቀጽ5/።
- ኤጴስ ቆጶስ እሑድ እንዲሾም የተወሰነበት ምክንያት ሕዝቡ አምስቱን ቀን በተግባረ ሥጋ አሳልፈው ቀዳሚት በተግባረ ነፍስ ማለት ሰው በማስታረቅ፣ ሕሙማንን እሥረኞችን በመጠየቅ፣ ውለው ለጸሎት፣ ሥጋ ወደሙ ለመቀበል ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄዱትና የሚሰበሰቡት እሑድ ስለሆነ ሁሉ እንዲያውቀውና በሕዝብ ፊት እንዲሾም ነው። ሁለተኛው እሑድ ጌታ የተጸነሰበት፣ ብርሃነ መለኮቱን በደብረ ታቦር የገለጸበት፣ ከሙታን ተለይቶ የተነሣበት መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ የወረደበት፣ እመቤታችን ያረፈችበት፣ ቅዱስ ዕለት ስለሆነ በቅዱስ ዕለት ቅዱስ ሢመት እንዲፈጸም ነው። ስለዚህም ሌላ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር ወጥቼ ወርጄ ነግጄ አትርፌ አምስት ጨምሬበታለሁ እነሆ መክሊትህ ከነትርፉ ብሎ ኤጴስ ቆጶሱ በኋላ የሚያስረክብበት ዕለት ስለሆነ ነው። /ዘጸ.20÷8-11፣ ማቴ.2÷1፣ ማር.16÷1-13፣ ሉቃ.24÷1-43፣ ዮሐ.20÷1-21፣ የሐ.ሥራ.20÷1-21፣ ማቴ.25÷14-23/
- ኤጴስ ቆጶሳቱ በአንብሮተ እድ ኤጴስ ቆጶሱን ከመሾማቸው በፊት እጃቸውን የሚታጠቡበት ምክንያት «እኛ በምናውቀው በአፍአ ንጹሕ ብለን ሾመንሃል። አንተ በምታውቀው በውስጡ ዕዳ የለንበትም እዳው በአንተ ነው» ለማለት ነው።
- ኤጴስ ቆጶሳት ሲሾሙት መስቀል የሚያስይዙት «መከራ ትቀበላለህ» ለማለት ነው። «ዝውእቱ ዘተሠይመ ለቤተክርስቲያን ጉባኤ እምኀበ ሥሉስ ቅዱስ በምሥጢረ መስቀል።» /ፍት.ነገ.አን.5/
- ቀዳማዊው ኤጴስ ቆጶስ በተሿሚው እጅ ላይ እጁን የሚጭነው «እስከ አሁን ድረስ ከእኔ በታች ነበርህ ከእንግዲህ ወዲህ ግን በሥልጣነ ክህነት ከእኔ ጋር አንድ ነህ» ሲለው ነው።
- የሢመተ ኤጴስ ቆጶሳት በዓለ ሦስት ቀን የሚከበረው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የመነሣቱ ምሳሌ ነው። «ወያብዕሉ መዋዕለ በዓለ መንፈሳዊት በአምሳለ ምሥጢሩ ለዘተንሥአ በሣልስት ዕለት» /ፍት.ነገ.5 ማቴ.16÷21/

- ዲያቆናት በሚሾመው ኤጲስ ቆጶስ ራስ ላይ አራቱን ወንጌል ዘርግተው የሚይዙበት ምክንያት «ወንጌልን ገልጠህ ታስተምራለህ ስለ ወንጌል መከራ ትቀበላለህ» ለማለት ነው::
- በመጀመሪያው የኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ የርክበ ካህናት ዕለት እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ሦስተኛ ጊዜ በባሕረ ጥብርያዶስ ለደቀመዛሙርቱ የጸለየበትና የምእመናን ጠባቂነት አደራ የተሰጠበት ዕለት በመሆኑ ነው:: /ዮሐ.21÷17 ሁለተኛው ጉባኤ ጥቅምት 12 ቀን የሆነበት ምክንያት ይህ ዕለት የመጀመሪያውን ወንጌለ መንግሥት የጻፈው የሐዋርያው የማቴዎስ መታሰቢያ በዓል ከመሆኑም በላይ ወቅቱ ክረምቱ አልፎ በጋው የሚተካበት አዝመራ የሚሰበሰብበት ጊዜ ስለሆነ በበጋም ቸነፈርና ድንገተኛ ሞት ስለሚበዛ ከሞት አስቀድሞ በፍቅር በንጽሕህ ሆኖ ንስሐ ገብቶ በጸሎትና በምሥጋና እግዚአብሔርን ለመለመን ነው::
- በኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ /ሲኖዶስ/ መካከል ባለ ጠረጴዛ ላይ ወንጌል የሚቀመጥበት ምክንያት በጉባኤው መካከል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አለ ለማለትና ለእውነተኛ መፍትሔ እንፈርዳለን፣ በጽድቅ እንነጋገራለን ለማለት ነው::
- ዲያቆን በ30 ዓመቱ ቅስና እንዲሾም የተደረገበት ምክንያት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ30 ዓመቱ ስለተጠመቀና ማስተማር የጀመረው በዚሁ ዘመኑ ስለሆነ ነው /ሉ.ቃ3÷23፣ ፍት.ነገ.አን.6÷1/::
- ብሉያትን ሐዲሳትን ይልቁንም አራቱን ወንጌል ያልተማረ ቅስና እንዳይሾም የተከለከለበት ምክንያት ሐዲሳን ምእመናንን ትምህርተ ወንጌል እያስተማረ የሚጠብቅ ስለሆነ ነው::
- ኤጲስ ቆጶስ ቄሱንና ዲያቆኑን ብቻውን የሚሾመው ማዕረጉ ሦስተኛ ስለሆነ ነው:: ይኸውም ወደላይ ጳጳስ፣ ሊቀጳጳስ፣ ርዕስ ሊቃጳጳሳት፣ ወደ ታች ቄስ ዲያቆን ነው::
- ካህን ሁለት እኅትማማች ከአገባው ሰው ሰርግ እንዳይሔድ የተከለከለበት ምክንያት ጋብቻው ሕገወጥና ርኩስ ከመሆኑም በላይ ሰርገኛውም ሥርዓት የተላለፈ ስለሆነ ነው::
- ዲያቆን ለካህናት ሥጋውን ደሙን የማያቀብልበት ምክንያት እሱ የካህናት ተላላኪ እንጂ ካህን ስላልሆነ ነው::

# ሰ. ሥርዓተ ተክሊል

1. <u>የጋብቻ አመሠራረት</u>

ጋብቻ ከሕግጋተ እግዚአብሔር አንዱ ነው:: ስለ ጋብቻ በኦሪትም ÷ በወንጌልም ሕግ ተሠርቷል::

በድንግልና ሊኖሩ እግዚአብሔር ከፈቀደላቸው ሰዎች በቀር ሁሉ በጋብቻ እንዲኖር ጥንቱን በአዳምና በሔዋን ጋብቻን መሠረተ።

ይኸውም «ሰው ብቻውን ሊኖር አግባብ አይደለም የምትረዳውን ጓደኛ እንፍጠርለት እንጂ» ብሎ እግዚአብሔር ለአዳም ሔዋንን በመፍጠሩ ታውቋል። /ዘፍ.2÷18/።

እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ ዕንቅልፍ ባለበት አንቀላፋም፥ ከጎኑም አንዲት አጥንት ወስዶ ሥፍራውን በሥጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት። ወደ አዳምም አመጣት። አዳምም አለ «ይህቺ አጥንት ከአጥንቴ ናት ሥጋዋም ከሥጋዬ ናት። እሱዋም ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል። ሚስቱንም ይከተላል። ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ» /ዘፍ.2÷22–24/።

እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት» /ዘፍ.1÷27/።

የአዳምና የሔዋን ጋብቻ የሕጋዊ ጋብቻ መሠረት ነው። ለአዳም ብዙ ሴቶች አለመፈጠራቸው ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት እንጂ አያሌ ሴቶች ያልተፈቀዱለት መሆኑን፥ ለሔዋን ብዙ ወንዶች አለመፈጠራቸው ለአንዲት ሴት አንድ ባል እንጂ አያሌ ወንዶች ያልተፈቀዱ መሆኑን ያመለክታል።

በአዳምና በሔዋን የተጀመረው ሕጋዊ ጋብቻ ወደ ልጆች ሲተላለፍ በብዙዎቹ ዘንድ ሕጋዊነቱና ሥርዐቱ ባይጠበቅም ሕገ እግዚአብሔር በጠበቁትና በታወቁት አባቶች ዘንድ ተጠብቆ ኖሯል።

ጥቂቶቹንም ለምሳሌ ያህል ብናቀርብ በዘመነ አበው የኖኅ ጋብቻ የተባረከ ሕጋዊ ጋብቻ ነበር። ሕጋዊና የተባረከም በመሆኑ በሕገ ወጥ ግንኙነትና በዝሙት የተባዛው የዓለም ሕዝብ በንፍር ውሀ ሲጠፋ የኖኅና ቤተሰቡ ከጥፋት ውሃ ድነዋል። በእርሱም ዘር ዓለም በሰው ልጆች ተሞልታለች /ዘፍ.7÷9/።

እንዲሁም የይስሐቅና የርብቃ፥ የዮሴፍና የአስኔት ጋብቻ ሕጋዊና የተባረከ ጋብቻ ነበር።

ከክርስትና በፊት የነበረው የጋብቻ ሥርዓት የዘርና የእምነት ልዩነት ይታይበት ነበር። በክርስትና ሥርዓት የእምነት ልዩነት የሚደረግ ቢሆንም በጋብቻ የዘር ልዩነት አይፈጸምም።

ለምሳሌ በኦሪቱ እሥራኤል ከአሕዛብ፥ አሕዛብ ከእሥራኤል እንዳይጋቡ ክልክል ነበር። «ኢተሀብ ወለተከ ለአሕዛብ ወኢንትሣእ ወለቶሙ ለአሕዛብ» /ዘዐ.7÷3/።

በኦሪቱም ወንድሙ ሳይወልድ ከሞተ የሚች ወንድም ሚስቱን አግብቶ ዘር ይተካ ነበር:: /ዘዳ.25÷5-10፣ ማቴ.22÷24-28/::

ጋብቻ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሕግ በመሆኑ በኦሪትም ሆነ በወንጌል ማንም ሰው ሚስቱን እንዳይፈታ ተከለከለ::

ይህም በመሆኑ በኦሪቱ ሰዎች ሚስቶቻቸውን ሲጠሉና ሊፈቱ ሲፈልጉ ሌላ የተንኮል ዘዴ አዘጋጁ ይኸውም የሰዎችን አሚሙዋት ሊመረምር የሚችል የፍልስፍናጥበብ ባልተገኘበት በዚያ የሞኝ ዘመን ወንዶች ሚስቶቻቸውን መርዝ እያጠጡ አፍ እያፈኑ ልብ እያሹ መግደል ጀመሩ፣ ይህ የሰዎች ተንኮል በግልጽ እየታወቀ ስለሔደ አሪትን የጻፈ ሙሴ የጋብቻን ሕግ ለማሻሻል ተገደደ፣ የተሻሻለውም ሕግ ፍቺን የሚፈቅድ ሲሆን ሥርዓቱ ግን ጠበቅ ያለ ነበር፣ ይኸውም ባሉም ሚስቱን ሊፈታት ከፈለገ በመግደልና ተንኮል በመሥራት ፋንታ የምትፈታበትን ነውር በደብዳቤ ጽፎ በዐደባባይ አንብቦና አጋልጦ እንዲፈታ ሙሴ በአሪት ሥርዓት ሠራ::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጋብቻ ሲያስተምር ፈሪሳውያን በማናቸውም ምክንያት ሰው ሚስቱን ሊፈታ ይገባል ወይ ብለው ቢጠይቁት የመለሰላቸው መልስ «እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው መለየት ስለማይገባው ባል በማናቸውም ምክንያት ሚስቱን ሊፈታ አይገባውም» ባላቸው ጊዜ ለተቃውሞ ያቀረቡት ጥያቄ ይህ ሙሴ ያሻሻለውን ሥርዓት ነበረ በጥያቄያቸውም እንደተገለጠው እንግዲህ ሙሴ ሰው ሚስቱን ሲፈታ የፍችዋን ደብዳቤ ጽፎ ይፍታት ለምን አለ ቢሉት ሙሴ ይህን ያዘዘ ስለልባችሁ ክፋት እንጂ ቀድሞስ እንዲህ አልነበረም:: እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ መፍጠሩ ማግባት መፍታት እንዳይኖር ነው በማለት ካላመነዘረችበት በስተቀር ማንም ሰው ሚስቱን እንዳይፈታ የተፈታችውንም እንዳያገባ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል አዘዘ /ዘፍ.1÷27፣2÷24፣ ዘዳ.2÷4፣ ማቴ.19÷3-12፣ 5÷31-32/::

ጋብቻን ያከበሩ በሕጋዊ ጋብቻ የኖሩ ደጋግ ቅዱሳን በሕገ ልቡና እንደነበሩ ሁሉ በሕገ ኦሪትም ነበሩ::

ለምሳሌ የኢያቄምና የሐና ጋብቻ ቅዱስ ጋብቻ ነበር:: የተቀደሰ ጋብቻ በመሆኑም የቤዛዊተ ዓለም የቅድስት ድንግል ማርያም ወላጆች የአምላካችን÷ የፈጣሪያችን የመድኃኒታችን አያቶች ለመሆን በቅተዋል::

እንዲሁም የዘካርያስና የኤልሣቤጥ ጋብቻ የተባረከ ጋብቻ ነበር ቡሩክና ሕጋዊ በመሆኑም መጥምቀ መለኮት ዮሐንስን አፈራ::

ጋብቻ በኦሪትም በወንጌልም የታዘዘና የተከበረ መሆኑን በዚህ መረዳት አያዳግትም «ክቡር አውስቦ በኩሉሄ ወለምስካቦሙኒ አልቦቱ ስእበት» ዕብ.13÷4/::

ጋብቻ በብሉይም ሆነ በሐዲስ በእግዚአብሔር ዘንድ የተከበረ በመሆኑ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በሆነ ጊዜ ትምህርት በጀመረበት ወራት የገሊላ አውራጃ በመትሆን በቃና ወደ

ሠርግ ቤት ተጠርቶ በሔደ ጊዜ ፈጽሞ አክብሮታል:: ያንንም ጋብቻ ባርኮታል::

ስለ ጋብቻ ኦሪትና ወንጌል በአንድ ቃል «ወንድ አባቱንና እናቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል፣ በሚስቱም ይዋሐዳል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» በማለታቸው እውነተኛ ምስክሮች ሆነዋል::

ዳግመኛም ቅዱስ ወንጌል «እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለይም» አለ::

ዳግመኛም ሐዋርያው ጳውሎስ «ወንዶችም ሚስቶቻችሁን እንደራሳችሁ አድርጋችሁ ውደዱ ማንም ማን ሥጋውን ሊጠላ የሚቻለው የለም» በማለቱ ሴትን ለባሏ አካል አደረጋት:: ዳግመኛም «ሴቶች ሆይ ስሙ ክቡር ለሚሆን ለእግዚአብሔር እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ» አለ:: ቀጥሎም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእሱዋ ሰውነቱን ለሞት የሰጠ ላት ቤተክርስቲያንን እንደሚወድዳት ባልም ሚስቱን እንዲወድ አዟል::

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ «አንተ ብፁዕ ነህ በጎ ነገርም ይደርግልሃል፣ ሚስትህ በቤትህ አዳራሽ ውስጥ እንደ አማረ ወይን ትሆናለች ልጆችህም በማዕድህ ዙሪያ እንደ አዲስ ዘይት ተክል ይሆናሉ:: እነሆ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንዲህ ይባረካል ባለ ዘመኑ ልክ በጎ ነገሮችን ያያል» ሲል የዘመረው በጋብቻ የሚገኘውን በረከትና መልካም ኑሮ ያረጋግጣል /መዝ.127÷1–4/::

ጋብቻ በዚህ ዓይነት በሕግ ሲፈጸም የሰዎችን ኑሮ ሲያሳምር መልካም ዘር ሲተካ በሕገ ወጥነት በአመንዝራነት ሲፈጸም ደግሞ የሰዎችን ኑሮ ሲያበላሽ እስከ ዘመናችን ደርሷል::

2. <u>የጋብቻ ተፈላጊነት</u>

የጋብቻ ተፈላጊነት ስለ ሦስት ነገር ነው ይኸውም:–

1ኛ. በኑሮ ለመረዳዳትና ሕይወትን በጋራ ለመምራት ነው:: «ሰው ብቻውን ሊኖር አይገባውምና የምትረዳውን እንፍጠርለት»:: ይላል /ዘፍ.2÷18/

2ኛ. ለመባዛትና ዘር ለመተካት ነው «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉዋት» ይላል /ዘፍ.1÷28–29፣ 9÷1–3/::

3ኛ. ከዝሙት ለመጠበቅ ነው:: «ወከመሰ ኢትዘምው ኵሉ ብእሲ ይንበር በብእሲቱ ወኵላ ብእሲት ትንበር በምታ» ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አዟል /1ኛ ቆሮ.7፤2÷5፣ 1–9/::

3. <u>መተጫጨት</u>

የጋብቻ መቅድሙ መተጫጨት ነው:: የመተጫጨት ባህልና ሥርዓት:–

ሀ. የፈቃድና የስምምነትን
ለ. የዕድሜን
ሐ. የሥጋዊና መንፈሳዊ ዝምድናን
መ. የሃይማኖትን አንድነት ዘርዝሮ ይገልጣል::

ተጋቢዎች ከተዋወቁ እርስ በርሳቸውም ከተፈቃቀዱና ከተስማሙ ለወላጆቻቸውም አሳውቀው ፈቃድና ስምምነት ካገኙ በኋላ የውዴታ ቃላቸውን በቅድሚያ ለመምህረ ንስሐ ወይም ለቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ወይም ለክፍሉ ኤጲስ ቆጶስ በመናገር ወደ ጋብቻው ቃል ኪዳን ያመራሉ።

በመተጫጨት ጊዜ በብርቱ ሊታሰብበትና ጥናት ሊደረግበት የሚገባው ዐቢይ ነገር ትዳርን የሚመሠርቱ የወጣቶች ዕድሜ መመጣጠን ጉዳይ ነው። ወጣቶች በሚጋቡበት ጊዜ በተፈጥሮ ሕግ በሃይማኖት በሥርዓትና በማኅበረሰብአ የጋብቻ ድንጋጌ መሠረት በዕድሜ የማይቀራረቡ ከሆነ በጋብቻው ላይ ችግር እንደሚያስከትል ከወዲሁ መታወቅ ሊኖርበት የሚገባው ነው።

ዕድሜን በተመለከተ ወንዶች ከ20 በላይ ሴቶች ከ15 ዓመት በላይ ሲሆናቸው መተጫጨትና መጋባት የሚፈቀድላቸው መሆኑ በቤተክርስቲያን ቀኖና ተመልክቷል /ፍት.መን.24ም.3 ክፍል 2/።

በመተጫጨት ጊዜ ሊጠነቀቁለትና ሊጠብቁት የሚገባ ሌላው ጉዳይ በተጋቢዎች መካከል የለው የዝምድና ሁኔታ ነው።

ጋብቻን የሚከለክል የዝምድና ዓይነትም 3 ነው እርሱም፦

1ኛ. ሥጋዊ ዝምድና

2ኛ. የጋብቻ ዝምድና

3ኛ. መንፈሳዊ ዝምድና ነው። ይህም ዓይነት ዝምድና መጠበቅ እንዳለበት በቅዱሳት መጻሕፍትና በቤተ ክርስቲያን የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ ተነግሯል።

እሥራኤላውያን ቅርብ የሆነ የሥጋ የጋብቻ ዝምድናን አፍርሰው እንዳይጋቡ ብሉይ ኪዳን በጥብቅ ያስጠነቅቃል /ዘሌ.18÷7-20፤ 20-21ም።/ በሐዲስ ኪዳንም አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን እንደተነገረው ዝምድናው ካልተራራቀ በቀር ሥጋዊም ሆነ የጋብቻ ዝምድና ያላቸው ሁሉ እንዲጋቡ አይፈቀድም የዚህም መሠረተ አሳብ በማርቆስ 6÷19፤ በ1ቆሮንቶስ 5 ተገልጧል።

ቤተ ክርስቲያናችን ሥጋዊና መንፈሳዊ ዝምድናን ለማስጠበቅ እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ዝምድና ያላቸው እንዲጋቡ አትፈቅድም።

1ኛ. <u>ሥጋዊ ዝምድና</u>

በቤተ ክርስቲያናችን የሕግ መጽሐፍ ፍትሐ ነገሥት በአንቀጽ 24፤842-853 ቁጥር ተዘርዝሮ እንደተገለፀው ሥጋዊ ዝምድና የሚጠበቀው እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ነው። ይህም በአንድ ወገን ሰባት በአንድ ወገን ሰባት ከተቆጠረ በኋላ ስምንተኛዎቹ ሊጋቡ ይችላሉ ማለት ነው።

2ኛ. <u>የጋብቻ ዝምድና</u>

ወደላይ ወንድ የአባቱን የአያቱን ሚስት፥ እኅት፥ እናት አያገባም። ወደታች የልጁን፥ የልጅ ልጁን ሚስት ልጇዋን፥ እኅትዋን፥ እናቷን፥ አያቷን አያገባም።

ወደኅን የወንድሞቹንና የልጆቻቸውን ሚስት÷ ልጁዋን እኅትዋን÷ እናትዋን÷ አያትዋን አያገባም::

የሚስቱን አያት እናት አክስት እኅትዋን÷ ልጁዋን÷ የልጅ ልጁዋን በዚህም ደረጃ ያሉ የዘመዶችዋን ሚስቶች አያገባም:: በዚህ አንጻር በሚስት በኩል የተከለከለው ዝምድና ሁሉ በባልም በኩል የተከለከለ ነው /ፍት.መን.34፣853/::

3ኛ. <u>መንፈሳዊ ዝምድና</u>

የመንፈሳዊ ዝምድና ዓይነት ብዙ ነው ሆኖም በጋብቻ እንዳይፈርስ የሚጠበቀው መንፈሳዊ ዝምድና በጥምቀተ ክርስትና ያለው ዝምድና ነው:: ይህም እንዲጠበቅ በቤተክርስቲያን የሕግ መጽሐፍ ፍትሐ ነገሥት ታዟል::

በዚህም መሠረት ወደላይ የክርስትና ልጅ የክርስትና አባቱን ሚስት ልጁን የልጅ ልጁን እኅቱን አያገባም::

ወደታች የክርስትና አባቱ የክርስትና ልጁን እናት÷ እኅት÷ የእኅቱንና የወንድሙን ልጅ አያገባም /ፍት.ነገ.24፣847/::

ከዚህም ሌላ በሃይማኖት የማይመሳሰሉ ወንድና ሴት መጋባት እንደሌለባቸው ተከልክሏል:: እሥራኤላውያት ሴቶች ልጆቻቸውን ለአሕዛብ እንዳይሰጡ የአሕዛብንም ሴቶች ልጆች እንዳያመጡ በብሉይ ኪዳን የተደነገገው ሕግ በሐዲስ ኪዳንም የተጠበቀ ነው /ዘዳ.7÷3–4/::

ነገር ግን ወንድ አማኒ ሆኖ ሴትዋ ባታምን አሳምኖ ማግባት ይችላል፤ ወይም ሴትዋ የምታምን ብትሆንና ወንዱ ባያምን አሳምና ልታገባው ትችላለች:: እንደዚሁም ወንዱ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ ሆኖ ሴትዋ የሌላ እምነት ተከታይ ብትሆን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ እንድትሆን አድርጎ ማግባት ይችላል ሴትዋም እንዲሁ ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መልሳ ማግባት ይገባታል /1ቆሮ.7÷12–17፤ ፍት.ነገ.24፣912–915/::

በጋብቻ የሃይማኖት አንድ መሆን ለተጋቢዎች እጅግ ጠቃሚ ነው:: ሁለቱ ዕጮኞች ከዚህ በላይ የተገለጸውን ሥርዓት ጠብቀው በወላጆቻቸውና በመምህረ ንስሐቸው የውዴታ ቃላቸውን ከገለጡ በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን ይሔዳሉ:: ከዚያም የጋብቻ ደንብ የሚያዘውን ይፈጽማሉ:: ከኤጲስ ቆጶሱ ወይም ከቤተክርስቲያን አስተዳዳሪው የጋብቻ ፈቃድ ሲያገኙ ለቁርባን ኪዳን ያዘጋጃሉ::

4ኛ. <u>ቁርባን ኪዳን /ቀለበት ማሠር/</u>

የመተጫጨት ሥርዓት በውልና በስምምነት ከተጠናቀቀ በኋላ የሚቀጥለው ሥርዓት የቀለበት ማሠር ወይም ቁርባን ኪዳንን በቃል መሐላ መፈጸም ነው::

ቀለበት በክብነቱና ፍጻሜ የሌለው በመሆኑ የቁርባን ኪዳን ጋብቻም ከሕይወት ፍጻሜ በቀር መፋታትና መለያየት የሌለበት መሆኑን

ይተረጉማል:: በሌላም በኩል ጋብቻን በሕግ ለሚጠብቁትና ለሚፈጽሙት ታላቅ ክብር አለው፤ የፍቅርም ምልክት ነው:: ይህም በመሐልየ ሰሎሞን «አንብረኒ ከመ ሕልቀት ውስተ ልብከ እንደ ቀለበት በልብህ ላይ አኑረኝ...» ተብሎ ተጽፏል /መሐ.8÷6/::

በሥርዓተ ጋብቻም ቀለበት የሚደረገው የቃል ኪዳን ምልክት በመሆኑ ነው:: ቃል ኪዳን በሁለት ሰዎች መካከል በመተማመን የሚፈጸም በመሐላ የሚጸና የማይለወጥና የማይፈርስ÷ በሁለቱም በኩል የሚጠበቅ ጽኑ የፈቃድ ውል ነው::

የቀለበት ማሠር ወይም የቃል ኪዳን አፈጻጸም ሥርዓትም እንደሚከተለው ነው÷

1ኛ. ለጋብቻ የተጫጩት ወገኖች ከጋብቻው ቀን አስቀድሞ ከቤተክርስቲያኒቱ የጋብቻ አገልግሎት ክፍል የተሰጣቸውን ማስረጃ ጋብቻቸውን ለሚፈጽሙበት ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ አቅርበው ቃል ኪዳናቸውን በቤተክርስቲያን ይፈጽማሉ::

2ኛ. ሙሽራውና ሙሽራ ፀቱ ከዘመዶቻቸው ጋራ ሆነው በቃል ኪዳን በተሰጠው ሕግ መሠረት የቀለበት ማሠሩ ስነ ሥርዓት ይፈጸምላቸዋል:: በመተጫጨትም ጊዜ የሰጡትን የፈቃድ ቃል በንስሐ አባታቸው አማካይነት በመሐላ ያጸናሉ::

5ኛ. <u>ሥርዓተ ተክሊል</u>

በሥርዓተ ጋብቻ ቅደም ተከተል መሠረት በመተጫጨትና በቃል ኪዳን የተመሠረተው ጋብቻ በተክሊል ይፈጸማል:: ክርስቲያናዊ ጋብቻ ትክክለኛነቱ የሚታወቀው በተክሊልና በሥጋ ወደሙ ሲፈጸም ነው:: ጋብቻን ያለ ሥርዓተ ተክሊል ለመፈጸም አልተፈቀደም /ፍት.ነገ.24ም.5 ክፍል ዳግም÷ መጅ 1/::

ሥርዓተ ተክሊል በቤተክርስቲያን ሕግ መሠረት ካህንና ምእመናን ሳይለዩበት በድንግልናና በንጽሕና ለኖረው ክርስቲያን ሁሉ ይፈጸማል::

ሥርዓተ ተክሊል በሚያደርሱበት ቀን ሙሽራው ከዘመዶቹ ጋር ወደ ቤተክርስቲያን ሄዶ ሙሽራውና ዘመዶቹ በሰሜናዊው ማዕዘን÷ ሙሽራ ፀቱና ዘመዶቹዋ በደቡባዊ ማዕዘን ሥፍራ ስፍራቸውን ይዘው ይቆማሉ::

ከዚህ በኋላ በምዕራብ በኩል በመካከለኛው ክፍል ማለት በቅድስቱ ውስጥ ከመቅደሱ ፊት ለፊት ካለው ቦታ ላይ ሊቀ ዲያቆናቱ ሙሽራውና ሙሽራ ፀቱ ሥርዓተ ተክሊል የሚፈጽሙበትን ምንጣፍ አንጥፈው ለሁለቱ የሚሆን መቀመጫ÷ እንዲሁም አንድ ጠረጴዛ ሙሽሮቹ በአንድነት የሚለብሱት ነጭ መጎናጸፊያ የሚቀቡትን ቅብዕ ቅዱስ የሚቀዳጁዋቸውን አክሊላት ያዘጋጃል::

ቀጥሎም ካህናቱ ሥርዓተ ተክሊሉን ያደርሱላቸዋል:: ሥርዓተ ተክሊሉ እንደተፈጸመ ሙሽሮቹ አስቀድሰው ቅዱስ ቁርባን ተቀብለው ጋብቻቸውን ያጸናሉ::

6ኛ. ምሥጢረ ተክሊል

ተክሊል ማለት ከለለ አከበረ ካለው ግሥ የወጣ ቃል ነው:: ይኸውም ክብር ማለት ነው::

ጋብቻ በቤተክርስቲያን ውስጥ በ ቃል ኪዳንና በቡራኬ፥ በጸሎተ ተክሊልና በቅዱስ ቁርባን ሲፈጸም ምሥጢርነት አለው:: ከዚህ ውጪ ግን ምሥጢር አይባልም:: ምሥጢር መባሉም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ይህ ምሥጢር /ጋብቻ/ ታላቅ ነው:: እኔ ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያን እላለሁ» ኤፌ.5÷32/ ብሎ በተናገረው መሠረት በተክሊሉ ጊዜ በሚታዩ ምልክቶችና በሚፈጸሙ ሥርዓቶች የማይታይ ጸጋ ስለሚገኝበት ነው::

በተክሊል ሥርዓት አፈጻጸም ጊዜ የሚታዩት ምልክቶችና ሥርዓቶች ቀጥሎ ያሉት ናቸው::

1. ሙሽሮቹ የሚያደርጉት ቀለበት
2. የሚለብሱት ነጭ ልብስ
3. የሚቀቡት ቅብዐ ቅዱስ
4. የሚቀዳጁት አክሊል
5. በእነዚህ ምልክቶችና በሙሽሮቹ ላይ የሚያደርሰው የካህኑ ጸሎትና ቡራኬ ናቸው:: እነዚህ ምልክቶች ሙሽራውና ሙሽራ ፀሏ ከመንፈስ ቅዱስ ለሚቀበሉት የማይታይ ጸጋ መቀበያ ምክንያቶች ናቸው::

የጸሎተ ተክሊል ፍጻሜ ጸሎተ ቅዳሴ ነው:: ከጸሎተ ተክሊል አያይዞ ጸሎተ ቅዳሴ ደርሶላቸው ሙሽሮቹ ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ:: ጸሎተ ተክሊል ተደርሶ ቁርባን ከቀረ ግን ተክሊሉ ፍጹም አይደለምና ጋብቻው አይጸናም:: «ወማዕሠረ ተዋስቦስ ኢይከውን ወኢይትፌጸም ዘእንበለ በህልዎተ ካህናት ወጸሎተ ዘላዕሌሆሙ ወይመጥዎሙ ቁርባነ ቅዱሰ በጊዜ ተክሊል ዘቦቱ ይትወሐዱ ክልዔሆሙ ወይከውኑ አሐደ ሥጋ በከመ ነገረ እግዚእነ ሎቱ ስብሐት ወዘእንበለ ዝንቱሰ፥ ኢይት ኀለቁ ሎሙ አውስቦ» ይላል /ፍት.ነገ.አን.24 መጅ 1/::

7ኛ. በምስጢረ ተክሊል የሚገኝ ክብርና ጸጋ

ምስጢራተ ቤተክርስቲያን በተባሉት ሥርዓቶች ሁሉ ለምእመናን የሚሰጥ ልዩ ክብር አለ::

ተክሊልም ከምስጢራተ ቤተክርስቲያን አንዱ እንደመሆኑ ከቅዱስ ቁርባን ጋር ሲፈጸም ይህንን ታላቅ መንፈሳዊ ክብር ያስገኛል::

ሙሽራውና ሙሽራ ፀሏ በቅዱስ ጋብቻ አንድ ይሆናሉ:: ይኸው አንድነታቸውም «እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውም» በሚለው ቃል መሠረት መለያየት ሳይኖር እስከ ሞት ድረስ የጸና ይሆንላቸዋል /ማቴ.19÷6/::

ሽንገላና ግብዝነት የሌለበት እውነተኛ ፍቅር ይኖራቸዋል:: «ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው» ብሎ ክቡር ዳዊት እንደተናገረው የተባረኩ ልጆችን ይወልዳሉ /መዝ.126÷3/:: በአጠቃ ይ የመከባበርና የመፈ ቃቀር፥

የመረዳዳትና የመተማመን፣ በሁሉ ነገር የመስማማት የመተባበር መንፈስ በምሥጢረ ተክሊል ያገኛሉ::

8ኛ. ከጋብቻ በኋላ የባልና ሚስት አኗኗር::

ሀ. ባልና ሚስት የኑሮ ዕኩልነት አላቸው:: የሴት ከባሉዋ ጎን መገኘት የተፈጥሮን መበላለጥ አያመለክትም፣ እንዲያውም ከፍ ብላ ከራሱ ዝቅ ብላ ከእግሩ አጥንት አለመፈጠሩዋ ከጎን መፈጠሩዋ የበላይና የበታች ሳትሆን ዕኩል መሆኑዋን ያሳያል::

ባል ለሚስቱ ራስ ነው፤ ሚስት ደግሞ ለባሉዋ ዘውድ ናት ባል ለሚስቱ ጠባቂዋ ኃይሉዋ ነው÷ ሚስት ደግሞ ለባሉዋ ክብሩ ናት÷ ይህንንም እውነተኛ ትምህርት ቅዱስ ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች ባስተማረበት መልእክቱ ለሱ አድርጎ በመተንተን በምሳሌ እያደረገ ተርጉሞታል /1ቆሮ.11÷6/::

ልዑል እግዚአብሔር የአዳምን ብቸኝነት ተመልክቶ የምትስማማውን የኑሮ ጓደኛ /ሔዋንን/ በፈጠረለት ጊዜ በነፍስም በሥጋም አዳምን አሳክሎ አስመስሎ አስተካክሎ ፈጥሯታል÷ በተፈጥሮ ጠባይም ሆነ በአስተሳሰብ ከአዳም አላሳነሳትም:: አዳምም ሔዋን አሱን አህላ እሱን መስላ በተሰጠ ችው ጊዜ «ይህች አጥንት ከአጥንቴ የተገኘች አጥንቴ ናት፣ ይህችም ሥጋ ከሥጋዬ የተገኘች ሥጋ ናት» በማለት አካሉ አምሳሉ መሆኑዋን አረጋገጠ፣ ስሚንም «ሔዋን» ብሎ ሰይሚታል:: ሔዋንም ማለት ሕይወት የሕያዋን እናት ማለት ነው /ዘፍ.2÷23፣ ኩፋ.4÷6/::

ከጾታ ልዩነት በቀር በባልና ሚስት መካከል አንዱን የበላይ ሌላውን የበታች የሚያደርግ የተፈጥሮ ልዩነት የለም:: እንዲያውም ባልና ሚስት በመካከላቸው መከፋፈል የሌለባቸው አንድ አካል ናቸው:: ፍቺና መለያየት የሌለበት የጋብቻ ቃል ኪዳናቸው ያዋሕዳቸዋል::

የተፈጥሮ ምሥጢር የሚተረጎምበት የጋብቻ ቃል ኪዳናቸው ምክንያት ወንድ የወለዱትን÷ ያሳደጉትንና ያስተማሩትን እናቱንና አባቱን ትቶ ሚስቱን ይከተላል:: ስለ ሚስቱ ሰውነቱን ለመከራ አሳልፎ ይሰጣል:: አባት እናቱን አገሩንም አያስባቸውም /ካል.ዕዝ.4÷20-21/::

ሰው ከወለዱት ከእናቱና ከአባቱ ሚስቱን ይወዳታል /ካል.ዕዝ.4÷25/::

የፍቅርና የአንድነት ሕይወታቸውን በአንድ አሳብ በአንድ ምክርና የጋራ ፈቃድ የሚመራ ነው:: ስለሆነም ጋብቻ በባልና ሚስት መካከል በአሳብ÷ በምክር÷ በሥራ የተቀናጀ በፍቅር ተዋሕዶ የጸና እኩልነት መከባበር መተሳሰብ መተዛዘንና መደጋገፍ የሰፈነበት እንዲሆን ያስፈልጋል::

ለ. ባልና ሚስት በቃል ኪዳን ቀለበት ተሣስረው በፈቃደ እግዚአብሔር ከተዋሐዱ በኋላ ባል ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ መጠበቅ ማድረግ ይገባዋል:: ሚስትም ለባሏ የሚገባውን መጠበቅ ማድረግ አለባት /1ቆሮ.7÷3/::

ሐ. በጋብቻ ሕይወት በመጠራጠር ሳይሆን በመተማመን በመናናቅ ሳይሆን በመከባበር ባልና ሚስት በፈሪሀ እግዚአብሔር አንድ ልብ መሆን ያስፈልጋቸዋል።

የሥነ ፍጥረት ባለቤት እግዚአብሔር የሰጠው ሕግ የሠራው ሥርዓት ነውና ወንዶች በኃይልና በጉልበት ሳይሆን ሚስቶቻቸውን በፈሪሀ እግዚአብሔር ሊያስተዳድሩዋቸው ሊወዱዋቸውና ሊያከብሩዋቸው ይገባል።

የአሳብና የምክር ተካፋይነት የትዳር አቻነት መብትና ነፃነት እንዳላቸው ያለማመንታት እንዲያረጋግጡላቸው ያስፈልጋል።

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ የጋብቻን ምስጢርና ክብር በክርስቶስና በቤተክርስቲያን መስሎ ያስተላለፈውን መልእክት ማስተዋል ይገባል።

ይህም ማለት ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ከቀኝ ጎኑ በፈሰሰው ደሙ ንጽሕት ክብርት ያደርጋት ዘንድ ራሱን ለሕማም ለሞት አሳልፎ እንደሰጣት የራሱም ማደሪያ ትሆን ዘንድ እንደመረጣት እንዲሁም ወንዶች /ባሎች/ ሴቶቻቸውን /ሚስቶቻቸውን/ እንደራሳቸው አድርገው ሊወዷቸው ይገባል «ራሱን መጥላት የሚቻለው የለም ለሰው ሁሉ የተሰጠው የሕይወት መመሪያ የተፈጥሮ ወንድምህን እንደራስህ መውደድ ነው። ሚስቱን የሚወድ ራሱን ወደደ» /ኤፌ.5÷25–29/።

በሴቶች በኩል እንደዚሁ የተለየ አመለካከትና የተዛባ ትርጉም ሳይሰጠው ከቅዱሳት መጻሕፍት በተገኘ ትምህርትና መመሪያ ሴቶች ለእግዚአብሔር እንደሚገዙና ለሕጉ እንደሚታዘዙ ለባሎቻቸው በፍቅር በፍርሃትና በአክብሮት እንዲታዘዟቸው ተጽፏል። ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ራስዋ ገዥዋ እንደሆነ ሁሉ ለሴትም /ለሚስት/ ገዥዋ ባሏ መሆኑ ተመልክቷል። ይህም ሚስት ለባልዋ÷ ባል ለሚስቱ መከባበርንና መተዛዘንን ያሳያል እንጅ የገዥና የተገዥ ምልክት አይደለም።

ሴቶች በባሎቻቸው ዘንድ በዓለማዊ ልብስና ጌጣጌጥ ብቻ ሳይሆን ቀደም ብሎ የነበሩ በእግዚአብሔር ላይ ፍጹም እምነት የነበራቸው ደጋግ ሴቶች ለባሎቻቸው በመታዘዝ በመልካም ሥራ ያጌጡ እንደነበር ከበጎ ግብራቸው የተነሣ ገድል እና ድርሳን እንደተጻፈላቸው እንደነሣራ እንደነርብቃ ባለ አኗኗር የባሎቻቸው ሕይወት እንደሆኑ ተጽፏል። /1 ጴጥ.3÷1–6/።

ስለዚህ ሴት ባሉዋ ያዘዛትን ልትፈጽም እንጂ በባሉዋ ላይ የሌላ ትእዛዝ ፈጻሚ ልትሆን የወደደችውን ልታደርግ በራስዋ ላይ ሥልጣን የላትም÷ በርሱዋ ላይ የማዘዝ ሥልጣን ያለው ባሉዋ ብቻ ነው። እንደዚሁም ወንድ በሚስቱ ላይ የሌላ ፁሑን ፈ ቃድ ሊፈጽም በራሱ የማዘዝ ሥልጣን የለውም። በእሱ ላይ ሥልጣን ያላት የምታዝዝበት ሚስቱ ናት /1ቆሮ.7÷4/።

መ. ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትታዘዝ ሚስትም አሳዳሪዋ ስለሆነ ለባሉዋ መታዘዝ ይገባታል። እንዲሁም ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ራሱንም ለሞት አሳልፎ እንደሰጣት ሥጋውን ደሙን

እንደ መገባት፥ እንደዚሁም ወንድ አካሉ ናትና ሚስቱን መውደድ፥ መርዳት፥ ይገባዋል /ኤፌ.5፥22-23/።

ሠ. ለሴት በሥጋዊ ጌጥ ከማጌጥ ይልቅ ለባሏዋ በመታዘዝ ባሏዋን በመፍራት በመውደድ ጌታዬ እያለች በመጥራት ስትፈራና ስታፍር መልካም ሥራ በመሥራት ንጹሕ ልቡናዋን ገልጣ እያሳየች በትሕትና በመንፈሳዊ ኃይል በመገዛት ማጌጥ አለባት። ወንድም የምድር ሀብትና ክብር ብቻ ሳይሆን የሰማይ ሕይወትና ክብር ተሳታፊው ስለሆነች ሚስቱን ሳይንቅ እንደ ዓይን ብሌን መጠበቅ አለበት። ባልና ሚስት አንድ ልብ አንድ አፍ ሆነው በመተማመን መኖር ይገባቸዋል እንጂ በአሳብ መለያየት መተማማት የለባቸውም /1 ጴጥ.3፥1-9/።

ረ. ለጾምና ለጸሎት ከተወሰነ ቦታ ጊዜ በስተቀር ባልና ሚስት መለያየት የለባቸውም። ሰይጣን ድል እንዳይነሣቸው ተጠባብቀው መኖር ይገባቸዋል። /1ቆሮ.7፥5/።

ሰ. ሴት ባረገዘች ጊዜ ጽንስዋ ከገፋ፥ ሆድዋ ከሰፋ በኋላ ወንዱ ከእሱዋ ጋር መገናኘት የለበትም «ወለእመ ኮነ ብእሲ ዘይዴመር ምስለ ብእሲቱ እምድኅረ ተከሥተ ጽንሳ ወዘንቱ ኢርቱዕ ወኢብውህ ሎቱ ለዝንቱሰ ኢይትፌቀድ ነገር በእንቲአሁ» /ፍት.ነገ.24/።

ሸ. ባልና ሚስት በጽንስ፥ በሕርስ፥ በትክት ጊዜ በበዓላት፥ በአጽዋማት ቀን ሩካቤ ሥጋ ማድረግ አይገባቸውም።

9ኛ. <u>ፍቺ እንዳልተፈቀደ</u>

ሰው ሚስቱን ሊፈታ ይገባልን? አይገባውም። ጋብቻ በተፈለገ ጊዜ የሚፈጸም ባልተፈለገ ጊዜ የሚፈርስ ጊዜያዊ ተባብሮ የመኖር ዘዴ ሳይሆን የሃይማኖትና የሥነ ምግባር አንድነት ልባዊ ፈቃድና ስምምነት የዕድሜ ተቀራራቢነት የአካልና የአእምሮ ጤንነት ያላቸው የወንድና ሴት ዘላቂነት ያለው ጽኑዕ አንድነት ነው። ይህ ስለሆነም በማናቸውም ምክንያት ሁሉ መፋታት አይገባም።

ለአዳም ብዙ ሴቶች አለመፈጠራቸው ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት እንጂ ብዙ ሚስቶች ያልተፈቀደለት መሆኑን፥ ለሔዋንም ብዙ ወንዶች አለመፈጠራቸው ለአንዲት ሴት አንድ ባል እንጂ ብዙ ባሎች ያልተፈቀዱ መሆኑን ያመለክታል።

በጋብቻ አንድነት ውስጥ ፍቺ ወይም መለያየት መኖር እንደሌለበት በቅዱሳት መጻሕፍትና በቀኖና ቤተክርስቲያን ተደንግጓል።

በብሉይ ኪዳን ነቢዩ ሚልክያስ ባልና ሚስት መፋታት እንደሌለባቸው ሲያስተምር «እግዚአብሔር የሚፈልገው ምንድን ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል፣ መፋታትን እጠላለሁ ይላል እግዚአብሔር የእሥራኤል አምላክ» ብሏል /ሚል.2፥15-16/።

ጠቢቡ ሰሎሞንም «የሕፃንነት ባልዋን የምትተው የአምላኳን ቃል ኪዳን የምትረሳ ቤትዋ ወደ ሞት ያዘነበለ ነው» ብሏል:: /ምሳ.2÷17/::

በሐዲስ ኪዳንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ሰው በማናቸውም ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን?» ተብሎ ከፈሪሳውያን ለተጠየቀው ሲመልስ «እግዚአብሔር በመጀመሪያው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው... አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም:: እንግዲህ እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለይ» በማለት ጋብቻን ጥንቱን በእግዚአብሔር ፈቃድ ሲመሠረት ጊዜያዊ ሳይሆን እስከ ሕይወት ፍጻሜ ዘላቂና ጽኑዕ አንድነት ያለው እንደሆነ አስተምሯል /ማቴ.19÷5–6፤ ማር.10÷2–9/::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህን መሠረት በማድረግ «ሴት ከባልዋ አትፋታ ልትፋታ ብትወድ ግን ያለ ባል ትኑር አለዚያም ከባልዋ ጋር ትታረቅ ባልም ሚስቱን ሊፈታ አይገባውም» /1ቆሮ.7÷10–11/::

እንዲሁም «ሴት ከባሉዋ አትለይ ወንድም ከሚስቱ አይለይ ሁላችሁም በጌታችን ትእዛዝ አንድ ሆናችሁ ኑሩ» /1ቆሮ.11÷1/::

በተጨማሪም «አንተ ሰው ሚስት አግብተህ ከሆነ መፋታትን አትሻ» /1ቆሮ.7÷27/ ሲል የጋብቻን ጽኑነት አረጋግጧል::

በቤተክርስቲያን የሕግና የቀኖና መጽሐፍም «ለፍቺ ያበቃል ተብሎ ከተናገረው ምክንያት በቀር ባል ሚስቱን፥ ሚስትም ባልዋን መፍታት እንደማይገባ ተወስኗል /ፍት.ነገ.24 ክፍል 9 ቁጥር 11–17/::

በቤተክርስቲያን ጋብቻ እንዲህ ሊፈርስ የማይገባው መሆኑ እየታወቀ ማንኛውም ሰው ሚስቱን ሊፈታ ቢወድ ከካህናቱ አንዱ ነውሯን የሚናገር ደብዳቤ መጻፍ የለበትም፤ ከጻፈ ግን መልሶ እስከሚያስታርቃቸው ድረስ ከምእመናን ይለያል:: «ወለእመ ፈቀደ አሐዱ ከመ ይድኀር ብእሲቶ ወጻፈ አሐዱ እምካህናት መጽሐፈ ኀዳጋቢሃ ይሰደድ እስከ ይመይጣ ለተዋሰቦ ወያስተሳልም» /ፍት.ነገ.አን.9 ቁ.5 ረስጠጅ 71/::

10. <u>ፍቺና ሁለተኛ ጋብቻ</u>

ሀ. ሁለተኛ ጋብቻ የሚፈቀደው ሚስት ወይም ባል በሞት ሲለዩ ብቻ ነው:: ከዚህ በቀር ሁለተኛ ጋብቻ አይፈቀድም:: ባልና ሚስት በሞት ካልሆነ በስተቀር ፈጽሞ መለያየት ከደረሰባቸው ግን ወደ ኋላ የቀረው ንጽሕናውን ጠብቆ መኖር የማይቻለው ከሆነ ሁለተኛ ማግባት ይችላል:: ሁለተኛዋም ከሞተች እስከ ሦስት ጊዜ ድረስ ማግባት ይችላል::

«ሴት ባሉዋ በሕይወት ሳለ በሕግ የጸናች ናት ባሉዋ የሞተ እንደሆነ ግን ለባሉዋ ከገባችለት ቃል ኪዳን ነጻ ናት:: ባሉዋ በሕይወት ሳለ ከሌላ ወንድ ብትደርስ ዘሙት ይሆንባታል:: ባሉዋ የሞተ እንደሆነ ግን ሌላ ብታገባ ዝሙት አይሆንባትም ሰሰነች አትባልም» /ሮሜ.6÷2–3/::

ሚስቱ የሞተችበት ሰው የሚያገባው የሚስቱ ሙት ዓመት ካለፈ በኋላ ነው ሴት ባልዋ ከሞተ ከ10 ወር በኋላ ታገባለች።

«ወአመሰከ የፌ መንጢጥ ዘኢንባቢ ይትገሐሥ እምአውስቦ ዳግማዊ እፎ እንከ ፌድፋደ ይደሉ ለእንስሳ ነባቢ ፍሬ ነገር የማይናገር የፌ መን ጢጥ /ርግብ/ ከሁለተኛ ግቢ የሚከለከል ከሆነ ፍሬ ነገር የሚናገር ሰውማ ከሁለተኛው ግቢ መከለከል እንደምን አይገባውም» /ፍት.ነገ.አን.24 በስ.45/

«ወበአንተ ዝንቱ ፍና ይደሉ ዐቂበ ዛቲ ሕግ እስመ ይእቲ ታወርዶሙ ለክቡራን እምክብሮሙ ዘውእቶሙ ካህናት ወይእቢ ሎሙ ትከውን ምንንተ» /ፍት.ነገ.አን ።

ወኢያውስብ ዘእንበ ይኅልፍ አሐዱ ዓመት እሞተ ብእሲቱ /ፍት.ነገ.አን.7/።

«ወእመኒ ብእሲት አውሰበት ብእሴ እምቅድመ ይትፈጸም አሠርቱ እውራኅ እምከመ ሞተ ምታ ኢትረስ ንዋየ ምታ» /ፍት.ነገ.አን.24/።

ለ. ከላይ ከተጠቀሰው በሞት ምክንያት ከሚደረገው መለያየት ሌላ ወንድ ሚስቱን መፍታት የሚገባው ስታመነዝርበት ብቻ ነው። ወይንም ሴት ባልዋን መፍታት የሚገባት ሲያመነዝርባት ብቻ ነው።

ማንኛውም ወገን ማለት ወንድም ሆነ ሴት በዝሙት ምክንያት ከፈታ በኋላ በዝሙት ምክንያት የተፈታችውን ወገን ማግባት አልተፈቀደለትም። ማግባት የሚችለው ንጽሕናውን ጠብቆ በሥጋው በደሙ ተወስኖ የኖረውን ወገን ብቻ ነው /ማቴ.5÷31-33፣ 19÷7-9/።

ሐ. በተፈጥሮ ወይም ከጊዜ በኋላ የሚከሠቱ ለፍቺ የሚያበቁ ችግሮችም ሲያጋጥሙ በሕገ ቤተክርስቲያን መሠረት ፍቺ ይፈቀዳል። እነዚህም ነገሮች /በፍት.ነገ. አን.24 ቁጥር 940-958/ ተዘርዝረዋል።

ለሁለተኛ ጋብቻ መጽሐፈ ተክሊል አይጸለይም ሥርዓተ ተክሊል አይደረግም፣ የሚጸለየው ፍትሐት ዘወልድና ጸሎተ ንስሐ ብቻ ነው።

«ወኢይጸልዩ ላእለ አውስቦ ዳግማዊ... ዘውእቱ ጸሎተ ተክሊል ወአኮ ጸሎተ ፍትሐት» ይላል /ፍት.መን.አን.9 ከፍል 4 ሥር 8 በስ 12/።

ወአውስቦሰ ዳግሚት ተሐዕዕ እምቀዳሚት ወለዛቲሰ ተሠርዐ ከመ ኢትኩን ላቲ በረከተ ተክሊል አላ ይግበሩ ጸሎተ አስትሥርዮ /ፍት.ነገ.24፣ዕንቆራ 18/።

«ወተጋብእሰ ማዕከለ አውስቦ ዳግማዊ አው ዘይበዝኅ ኢይደሉ እስመ ውእቱ ዝሙት ከሡት ዘተነግረ» /ፍት.ነገ.አን.24/።

11ኛ. <u>ሦስተኛ ጋብቻ</u>

ሀ. ሦስተኛ ጋብቻ ፈጽሞ የተናቀ ነው። ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው ሚስቱ ከሞተችበት አንድ ሰው ለሦስተኛ ጊዜ ማግባት ቢፈልግ በሕገ ቤተክርስቲያን መሠረት የንስሐ ጸሎት ተደርጎለት በቤተክርስቲያን ያገባል። ከ3 ጊዜ በላይ ማግባት ግን ለክርስቲያን አልተፈቀደም።

«ወአውስቦሰ ሣልስ ምኑን ውእቱ ወአልቦ በኀቤነ እምድኅረዝ አውስቦ ሕጋዊ» ይላል /ፍት.ነገ.አን.24/::

እንዲሁም «ወለእመቦ ዘአውሰበ ዘኢኮነ እምሕግነ ይትከላዕ ዓመተ ወዘዐውሰበ ራብዐ ኢይቅረብ» ይላል /ፍት.ነገ.24/ አይቀረብ ማለት ነው::

ለ. የማዓስባን ማለት አግብተው የፈቱና በንስሐ የተመለሱ ምእመናን ጋብቻቸውን በሥርዓተ ጸሎትና በቅዱስ ቁርባን ለመፈጸም ወደ ቤተክርስቲያን በሚመጡበት ጊዜ ቄሱ ከሁሉ አስቀድሞ ለመጋባት የተፈቃቀዱበትን የሁለቱን ሰዎች ጋብቻ የሚከለክል ምክንያት አለመኖሩንና በእነሱም በኩል እስከ መጨረሻው መለያየትን የማያስከትል ስምምነት በመካከላቸው መኖሩን ይመረምራል::

ከመጋባት የሚከለክላቸው ምክንያት አለመኖሩን÷ ስምምነታቸውም ፍጹም መሆኑን በሚገባ ከተረዳ ጸሎት ያደርስላቸዋል:: ከጸሎቱም በኋላ ሥጋውን ደሙን ያቀብላቸዋል::

ሐ. በጋብቻ ላይ ጋብቻ በሚስት ላይ ሚስት ማስቀመጥ ክልክል ነው:: «ወኢያንብር ብእሲ ክልዔተ አንስተ በምክንያተ ተድላ» ይላል /ፍት.ነገ.አን.24/::

መ. ካህን ሁለተኛ ቢያገባ ከክህነቱ ይሻራል:: ሦስተኛ ቢያገባ ግን አልተፈቀደለትም፣ ርኩስ ነው::
«ወለእመ ኮኑ ዕደው ካህናት ይደቁ አማዕርጊሆሙ ወእምድኅሬሁሰ ለእመ ደገሙ ይከውኑ ርኩስ» /ፍት.ነገ.አን.24 ምዕ.5 ክፍል 3 ቁጥር 5–6፣ ኒ.ቅ.19/::

ሠ. ከወንድ ዝሙት ቅጣት ይልቅ የሴት ዝሙት ቅጣት ይበልጣል:
«ወይደሉ ከመ ይጽናዕ ኩነኔ ዝሙታ ለብእሲት ፈድፋደ እምብእሲ »
/ፍት.ነገ.አን.24 ሥር 24 ቁጥር 35/::

12ኛ. <u>የሥርዓተ ተክሊል አፈጻጸም</u>

የሥርዓተ ተክሊል አፈጻጸም÷ የቀለበት ማሠሪያም ሆነ የጋብቻው ሥርዓት ሚያዝያ 1 ቀን 1956 ዓ.ም. በሊቃውንት ጉባኤ በታተመው መጽሐፈ ተክሊል የተገለጸ ስለሆነ በዚሁ መጽሐፍ መሠረት ሥርዓቱ ይፈጸማል::

13ኛ. <u>የሥርዓተ ተክሊል ትርጉም</u>

ሀ. አንድ ወንድ ማግባት የሚገባው አንዲት ሴት ነው፥ ወይም አንዲት ሴት ማግባት የሚገባት አንድ ወንድ ነው ብዙ ሴት ማግባት የሚገባ ቢሆን ሥላሴ ለአዳም ብዙ ሴት መፍጠር በቻሉ ነበር ብዙ ወንድ ማግባት የሚገባም ቢሆን ኑሮ ለሔዋን ሥላሴ ብዙ ወንድ በፈጠሩላት ነበር፤ ነገር ግን አንድ ወንድ በአንዲት ሴት÷ አንዲት ሴትም በአንድ ወንድ መኖር በደስታም በመከራም አብረው መኖር እንዲገባቸው ለሔዋን አዳምን ብቻ ለአዳምም ሔዋንን ብቻ ፈጠሩ /ዘፍ.2÷20–25፤ ማቴ.19÷3–6/::

ለ. ወንድ ወደ ሴት ሔዶ እንዲያጭ የተደረገበት ምክንያት ቋል የመርዓዊ÷ ትስብእት የመርዓት ምሳሌ በመሆኑ ነው:: ይኸውም ቋል ሽቶ ሥጋን ተዋሐደ እንጂ ሥጋ ፈልጎ ያልተዋሐደ ስለሆነ በዚህ ምሳሌ ነው::

አዳም ሔዋንን በተጣላት ጊዜ ቅዱስ ገብርኤል መጥቶ ሲያስታርቃቸው ሄደህ ታረቅ ቢለው እሱዋ ትምጣ እንጂ እኔ አልሔድም ባለው ጊዜ «አኮ መፍትው ትሑር ብእሲት ኀበ ብእሲ» ማለቱ ወንድ ወደ ሴት እንዲሔድ እንጂ ሴት እንድትመጣ ስለማያመለክት ነው::

ሐ. ሰባት ዓመት ሳልሞላው ልጅ ሚስት አይታጭለትም፤ ምክንያቱም አዳም ከሰባት ቀን በፊት ሔዋንን ስላላገኘ ነው /ኩፋሌ 4÷28፤ ፍት.ነገ.አን.24/::

መ. የሙሽራውና የሙሽራ ፀቱ ተዋሕዶ የክርስቶስና የቤተክርስቲያን ተዋሕዶ ምሳሌ ነው:: «ዐቢይ ውእቱ ዝ ነገር አንሰ ዕብሎ ባዕለ ክርስቶስ ወላእለ ቤተክርስቲያኑ /ኤፌ.5÷32/::

ሠ. ሙሽሮች በ ቋል ኪዳናቸው ጊዜ ቀለበት የሚያደርጉት የቋል ኪዳንና የሃይማኖት ምልክት በመሆኑ ነው::

ረ. ቋል ኪዳን የሚገቡበት መስቀል የመከራቸው ምልክት ነው::

ሰ. ዘመድና ዘመድ እንዳይጋቡ÷ ባዕድና ባዕድ እንዲጋቡ የተወሰነበት ምክንያት ባዕድ መለኮት ባዕድ ሥጋን ስለተዋሐደ የዚያ ምሳሌ በመሆኑ ነው::

ሸ. አብረው ያደጉ ሰዎች የማደጎና የጉድፈቻ ልጆች አሳዳጊዎቻቸው ጭምር እርስ በርሳቸው አይጋቡም፤ ምክንያቱም አንድ ጡት ጠብተው ስለሚያድጉ÷ አሳዳጊዎችም እንደ ልጅ ይሆኑናል ብለው ስለሚያሳድጓቸው ነው::

«አውስቦ አዘማድ ዘበንብረት ወለእመኒ ወጽኡ እምታሕተ ምልክናሆሙ ውእቶሙ ወለእመ ተፈልጡ ዘሐፀንዎሙ ወእሙንቱ ዘሀለው በተሳትፎ ጠቢወ ጥብ ወውሉዶሙ ወወላድያኒሆሙ ወለእመኒ እሉ ወአበዊሆሙ ወአበወ አበዊሆሙ ወአኀው አበውሆሙ፤ ወአኀው አበውሆሙ፤ ወእኅተ እማቲሆሙ ወብእሲተ አብ...» /ፍት.ነገ.አን.24 ቀ.54/::

ቀ. ያመኑ ሰዎች ያላመኑትን እንዳያገቡ የተደረገበት ምክንያት በኦሪቱ ሥርዓት «ኢተሀብ ወለተከ ለአሕዛብ ወኢትንሣዕ ወለቶሙ ለአሕዛብ» በተባለው መሠረት የእግዚአብሔር ወገኖች የሆኑት እሥራኤል ከአሕዛብ ስለማይጋቡ በዚህ ሥርዓት ምሳሌ ነው /ዘዳ.6÷3/::

በ. ባለጸጋ ድሀ አላገባም ማለት አይገባውም የተባለው ባዕል መለኮት ነዳይ ሥጋን ስለተዋሐደ ነው::

«አንሰ ዕብሎ ላዕለ ክርስቶስ ወላእለ ቤተክርስቲያኑ» /ኤፌ.5÷32/

እፎ ቤተነዳይ ኀደረ ከመ ምስኪን እምሰማያት ወረደ ላእሌሃ ፌቲዎ ስነ ዚአሃ ወተወልደ እምኔሃ /ሰዓታት/::

ተ. በሥርዓተ ተክሊል ላይ ሙሽሮች የሚለብሱት ልብስ ሰማይ በከዋክብት ምድር በጽጌያት እንደሚያጌጡ ጌጣቸው÷ የደስታ÷ የድኅነት÷ የንጽሕና የሰላምና የጤንነት የልጅነት /ከእግዚአብሔር መወለድ/ ምልክት ነው::

ቸ. ሙሽሮች ዘይት የሚቀቡት ሰማያዊ ክብር እንዲያገኙ÷ የጽድቅና የፍርድ መሣሪያ እንዲሆናቸው÷ ንጽሕናቸውን እንዲጠብቁ÷ የማይጠ ወልግ መልክና የሥጋ ብርሃን እንዲሰጣቸው÷ የጌጥና የደስታ÷ የእውነተኛ ሀብት መንፈስ እንዲያድላቸው÷ የድኅነት ኃይልና የጠላት ዲያብሎስን ሥራ ሁሉ ድል የሚነሣ እንዲሆናቸው÷ ነፍሳቸውና ሥጋቸውን ልቡናቸውንም እንዲያድንላቸው የብልጽግናና የመልካም ሥራ ፍሬን እንዲሰጣቸው ነው::

ኀ. ሙሽሮች የሚያደርጉት አክሊል የክብራቸው ምልክትና ምሳሌ ነው::

ነ. ሴት ከወንዱ ሥልጣንና ትእዛዝ በታች የምትኖረው ተፈጥሮዋ ከወንድ ጎን ስለሆነ ነው /ዘፍ.2÷21–24/::

ኘ. ሴት ጽንስዋ ከገፉ ሆድዋ ከሰፋ በኋላ ባሏ እንዳይገናኛት የተከለከለበት ምክንያት የተጸነሰው ወንድ ከሆነ ግብረ ሰዶም መሥራት ሴት ከሆነች ከልጁ መገናኘት ስለሚሆንበት ነው::

አ. በአራስነት በወር አበባ ግንኙነት ክልክል ነው ምክንያቱም 1ኛ/አባለ ዘርን ደዌ የሚያገኘው ስለሆነ 2ኛ/የሚጸነሱትን ሕፃናት ደዌ ሥጋ የሚያገኛቸው ስለሆነና ለምፅ ስለሚወጣባቸው ነው::

«ወተከልያሰ እምነ ናካቤ በመዋዕለ ትክቶሃ ወኀርሰ ዝኒ በእንተ ዘይረክቦ ለአባለ ዘርዕ እሙስና ወዘይዳለቆሙ ለውሉድ እለ ተጸንሱ በከርሥ እምነ እንታክቲ ግብር ሕማመ ዝልጋሴ ወለምፅ» /ፍት.ነገ.አን.24ም.5ክፍል 3 ቁ.47–49/::

ከ. በጾም ናካቤ የተከለከለበት ምክንያት ለጾም የሚገባው ፈቃደ ነፍስ ለመፈጸም እንዲቻል ነው÷ ሁለተኛም ሰውነትን በንጽሕና ለመጠበቅ ነው:: ሦስተኛም የሚወለደውን ልጅ ከመቅሰፍት ለመጠበቅና ለማዳን ነው::

«ወለተከልያሰ በመዋዕለ አጽዋም ዝኒ ከመ ይትፌጸም ከዊነ ፈቃድ ዘበእንተ ጾም... በእንተ ክብረ ነፍስ ነባቢ ወለዐ ቀበ ሥጋሁ ወለዐቀበ ወልዱ» /ፍት.ነገ.አን.24 ም.5 ክፍል 3 ቁ.50–52/::

ኸ. ሰውን እንስሳ ነባቢ ያለበት ምክንያት ሰው በተፈጥሮው ነባቢት ነፍስን በመዋሐዱ መላእክትን ሲመስል ደካማ ሥጋን በመልበሱ እንስሳትን ስለሚመስል ነው:: ማለት በነፍሱ የመላእክትን ሥራ ሲሠራ በሥጋው የእንስሳትን ሥራ ስለሚሠራ ነው:: ጌታችንም የአዳምን ሥጋ በመልበሱ መጽሐፍ እንስሳ ይለዋል::

«ወኮነ እንስሳ ነባቤ» /አፈ ወረቅ ድርሳን 1 ገጽ 22/

ወ. ሙሴ እንደ ልቡናችሁ ክፋት መጠን ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ጻፈላችሁ ያላቸው ሙሴ አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት አንዲት ሴት ከአንድ ወንድ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ በደንጊያ ተወግሮ በእሳት ተ ቃጥሎ ይሙት ብሎ ሥርዓት ሠራ÷ ወንዱ የሞተችበት እንደሆነ ሴቷም የሞተባት እንደሆነ በፈቲው ጾር እየተናደዱ የሚሞቱ ቢሆን ወደ እግዚአብሔር አመለከተ:: ሚስቱ የሞተችበት ባልዋም የሞተባት ያግቡ አለው ወንድ የጠላት እንደሆነ በጉልበቱ እያሻሸ የሚገድላት ሴቲቱም የጠላችው እንደሆነ በጉልበት ባየሆንላት በጥበብ በሥራይ የምትገድለው ሆነ:: በዚህ ምክንያት ዳግመኛ ወደ እግዚአብሔር አመለከተ:: የምትፈታበትን ነውር የሚናገር ደብዳቤ ጽፎ ይፍታት ብሎ ስለነገረውና በዚህ ምክንያት ሙሴ እንዲፈታ ስለፈቀደ ነው::

ዐ. ያፈ መንጢጥ /ርግብ/ ለሕጋዊ ጋብቻ ምሳሌ የሆነችበት ምክንያት ባሉዋ ስለሞተባት በጥፍሩዋ መላስዋን ሰንጥቃ ሌላውን ወንድ ትከለክላለች ማለት የተሰነጠቀ ምላስዋን እያሳየች ስለምትመልስ ነው /ድርሳነ ሚካኤል ገጽ 79/

ዘ. 60 ዓመት የሞላትን ሴት ማግባት ተከልክሏል፣ ምክንያቱም ልጅ መውለድ ስለማትችል ሙቀት ልምላሜ ስለተለያት በማርጀቱዋ ምክንያት ባሉዋን መርዳትም ስለማትችል ነው /ፍት.ነገ.አን.24 ቁ.105/::

የ. ለምእመናን ሦስተኛ ጋብቻ ሲፈቀድ ለካህናተ የተከለከለበት ምክንያት የካህን ሁለተኛ ጋብቻ የምእመናን ሦስተኛ ጋብቻ÷ የካህን ሦስተኛ ጋብቻ እንደ ምእመናን አራተኛ ጋብቻ የሚቆጠር ስለሆነ ነው::

ደ. ከወንድ ዝሙት ቅጣት የሴት ዝሙት ቅጣት የሚበልጥበት ምክንያት 1ኛ/ ወንድ ከዝሙት ባይከለከል ሴት ከባሉዋ ትለያለችና መለየት አይገባትም ለማለት ሲሆን ሴት ከዝሙት ካልተከለከለች ባልዋን ቅንዓት ይይዘውና ሚስቱን ከእርሱዋ ጋር ያመነዘረውን ሰው÷ አባቱዋን÷ ወንድሟን÷ እናትዋን እስከ መግደል ይደርስና ብዙ ነፍስ ያጠፋል:: ሚስቱና ዘመዶቹዋ ግን ይህን ያህል ዓመፅ አይፈጽሙም:: ግፋ ቢል ሚስቱ ልፋታ ነው የምትለው፣ ዘመዶችዋም ቢሆኑ ልጃችንን ከብታችንን ስጠን ይላሉ እንጂ እንግደል አይሉም 2ኛ/ ሴት ካመነዘረች ዘር ይደባለቋል:: 3ኛ/ ድንግል ሴት ብታመነዝር በዝሙት÷ ማኅተመ ድንግልናዋን አጠፋች ትባላለች ወንድ ግን ማኅተመ ድንግልናውን አጠፋ አይባልምና በዚህ ምክንያት ነው ከወንድ ዝሙት ቅጣት የሴት ዝሙት ቅጣት የበለጠው:: ወዘንቱስ ዘተገብረ እስመ ዝሙትስ ለብእሲ ዝነ. በእንተ ከመ ኢ.መፍትው ትትፈለጥ ብእሲት እሞኔሁ እስመ ብዝን ሐሠሣሁ ለሕግ ከመ የአትት ዕፀበ ዘይመጽእ ላዕለ ስብእ በበይናቲሆሙ ወለብእሲሰ ፈድፋደ ይእኀዞ ቅንዓት እስከ ይቀትል ብእሲ ለእመ ዘመወት ላዕሌሁ ወዓዲ ይቀትል ብዕሴ ዘዘመወ ምስሌሃ መዓዲ ይገብር ዘንተ በአቡሃ

ወበእኁሃ አው በእማሃ ወብእሲትስ ወአዝማዲሃ አኮ ከማሁ ወዓዲ እስመ ዘርእ ይቀውም በእንተ ዘዐቅቦተ ብእሲት ወለእመ ዘመወት ይትቲ ይመስን ርስት ወትውልደ አበው ወዓዲ እስመድንግል በዝሙት ታማስን አረአያ ድንግልሃ ወበእሲሰ አኮ ከማሁ /ፍት.ነገ.አን.24 ሥርዋዕ 24 ቁጥር 36–46/::

# የስብከት ዘዴ

በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ቀዳማዊ

## ለሰባኪው የሚያስፈልገው

ሀ. ትምህርት፣

ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለዓለም ያስተዋወቀችው በትምህርት ነው:: ክርስቶስ በማስተማር ጊዜው አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት መርጦ ካሠለጠነ በኋላ ምስክሮች እንዲሆኑት ወደ ዓለም ላካቸው:: ሐዋርያትም የተሰጣቸውን አደራ በማክበር ትምህርት ቤቶችን እያቋቋሙ ቃለ ሕይወት ወንጌልን ለሁሉም እንዲዳረስ አደረጉ፤ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን መንግሥት በትምህርት ለዓለም አስተዋወቀች ስንል፣ በየጊዜው መልኩንና ጠባዩን እየለዋወጠ ከሚመጣው ሰው ሠራሽ ሥልጣኔ ባለመራቅ፣ ዕለታዊ ችግሮችንና ዘመናዊ አስተሳሰቦችን በማጥናት ከቤተክርስቲያን መሠረታዊ እምነትም ጋር በማወዳደርና በማነፃፀር አጥጋቢ መልስ በመስጠት ነው::

የቤተክርስቲያን ስብከት መደምደሚያው፣ አናቱ፣ መሐሉ፣ እንብርቱ ክርስቶስ ነው:: ክርስቶስ የነበረ፣ ያለ፣ የሚኖር፣ እንደመሆኑ መጠን አይለወጥም:: ቋንቋ ግን መገናኛ ነውና ቤተክርስቲያን የአካባቢዋንና የጊዜውን ቋንቋ ብትጠቀም ለሐዋርያዊ ሥራዋ አመቺ ይሆንላታል::

ለዚህ አገልግሎት የሚመረጠው ካህን በመጀመሪያ ትምህርት ያስፈልገዋል:: ትምህርትም ሲባል መጀመሪያ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማለትም ብሉይ ኪዳንንና ሐዲስ ኪዳንን፣ እንዲሁም የሊቃውንትን መጻሕፍት አዘውትሮ ማንበብ አለበት ዮሐ.5÷39፣ ቀዳማዊ ጢሞ.4÷16:: ለማስተማር የተመደበው ካህን ቅዱሳት መጻሕፍትንና ሌሎችም የሚያግዙ መጻሕፍትን ካላወቀ ትምህርቱ ሰዎችን አይስብለትም:: ከዚህ ጋር ሁለገብ ሙያ እንዲኖረው ያስፈልጋል:: በዘመኑ ካሉት ሰዎች ያነሰ ሙያ ካለው ሰሚዎችን ለማሳመን አይችልም:: ይልቁንስ በዚህ ፋንታ እርሱም ተንቆ ቤተክርስቲያኑንም ያስገምታል:: ሰባኪው የምስክርነት ቃሉን የሚሰጠው በአስረጅ ስለሆነ ለተነሣበት ርዕስ አስረጅ የሚሆኑትን ጥቅሶች ከሊቃውንትም ሆነ ከቅዱሳት መጻሕፍት ወይም ከሌሎች የታሪክ መጻሕፍት አስረጅዎችን መሰብሰብ ግዴታው ነው::

ይህ ሁሉ ሊሆን የሚቻለው በማንበብና በመማር ስለሆነ በስብከት ዘዴ ውስጥ ቅድሚያ ለትምህርት ይሰጣል /1ኛ ጴጥ.3÷5፣ ቆላ.4÷6፣ ኢሳ.8÷12/:: ሰባኪው ለሰሚዎቹ የሚያስተላልፈውን መልዕክት ብቻ መመልከት የለበትም:: የሱን ትምህርትና መልእክት የሚያስተባብሉ ጽሑፎችና ሰው ሠራሽ አስተሳሰቦችንም አስቀድሞ የሰማና ያወቀ መሆን አለበት:: ለምሳሌ፣ ስለሰው ተፈጥሮ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት የሚሰብክ

መምህር ሌሎች እነቻርልስ ዳርዌን ስለሰው ተፈጥሮ ምን ይሉ እንደነበር ማወቅ አለበት። መልሱንም ማዘጋጀት አለበት። ስለ ሥነ ፍጥረት ዓለም በየመልኩ በእግዚአብሔር ጥበብ መፈጠሩን በሚያስተምሩበት ጊዜ ሌሎች /ፒታጐራሳውያን/ የሚሉትን ማወቅ ይገባዋል። ካላወቀ መልስ ሊያዘጋጅ አይችልምና። ስለዚህ ነው ከላይ ሰባኪው ካህን ሁለገብ ዕውቀት ያስፈልገዋል የተባለው።

በጥንት የቤተክርስቲያን ታሪክ የምናው ቃቸው ሰባኪዎች /ጠበብት/ ቅዱሳት መጻሕፍትን ብቻ ሳይሆን ወይም የክርስቲያን ሃይማኖት ደጋፊዎች የጻፏቸውን ብቻ ሳይሆን ነ ቋዎች የጻፏቸውን መጻሕፍት ያነቡ ነበር። በሙያም በኩል በዘመናዊው የነበረውን የፍልስፍና ትምህርት በሚገባ ያውቁ ስለነበር ለሐዋርያዊ ምስክርነት አግዟቸዋል።

ሰ. ክርስቲያናዊ ሕይወቱን የጠበቀ እንዲሆን ያስፈልጋል

ሰባኪው ትምህርቱን የሚያስተላልፈው ሰሚዎች እሱን እንዲመስሉ ስለሆነ በሰሚዎች ዘንድ የርሱ ሕይወት ግልጽ መሆን ይገባዋል። እርሱ የሚሠራውን አትሥሩ፣ እርሱ የማይሠራውን ሥሩ ብሎ የሚያስተምር ከሆነ ትምህርቱ ተቀባይ ያጣል። አትስረቁ ብሎ የሚያስተምር መስረቅ አይገባውም፣ አትስስኑ ብሎ የሚያስተምር መሰሰን አይገባውም። አትዋሹ ብሎ የሚያስተምር ሐሰት መናገር የለበትም /ማቴ.23÷2-4 ሮሜ.2÷21-24 1ኛ ጢሞ.5÷22፣ 4÷11-12። 2ኛ ጢሞ.2÷22 ቲቶ.7÷8/። የሚናገረውን በተግባር የሚያሳይ፣ ነውር፣ ነቀፋ፣ የሌለበት ብኃጢአት የማይታማ ክርስቲያናዊ ሕይወቱን የጠበቀ፣ ክርስቶስ ለጠላቶቹ የመለሰውን አስመስሎ ለመመለስ የሚችል መሆን አለበት /ዮሐ.8÷46 ፣ 14÷30/።

ያስተማረው ትምህርት እንዳይናቅና ተቀባይ እንዳያጣ እግዚአብሔርንም እንዳያስድብ ሰባኪው በግል ሕይወቱ ጠንቃ መ ሆን አለበት /1ኛ ቆሮ.9÷27 ኢሳ.52÷5 ሕዝ.36÷20/። ሰሚዎች እሱን እንዲመስሉ የሚያስተምር መምህር እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶስን መምሰል አለበት /1ኛ ቆሮ.4÷16፣ 11÷1/። በክርስትና ትምህርት አስመስሎ መናገር ብቻ ሳይሆን አስመስሎ መሥራት፣ የሚመስሉትን ሁኖ መገኘት ግዴታ ነውና። እነዚህን ሁሉ ያሟላ ካህን ቢያስተምር በመቅረዝ ላይ እንዳለች መብራት ለሁሉ ያበራል።

ሐ. አርአያ ክህነት ያለው መሆን አለበት

አንዳንድ የሃይማኖት ሰባኪዎች አቋማቸው ሲታይ ከሚናገሩት ቃል ጋር የተለያየ ነው። እነዚህም ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በሚያስተላልፉበት ጊዜ እነርሱ ከ ቃሉ ጋር ዝምድና የላቸውም። ማቴዎስ ለመምህራን ይህንን ለማስታወስ ነው ስለ ዮሐንስ መጥምቁ የሕይወት ታሪክና አርአያ ክህነት በሚገባ የተናገረው /ማቴ.3÷4፣ 2ኛ ነገ.1÷8/። /ከካህናት/ የሚፈለገው አለባበስ ብቻ ሳይሆን አባታዊ አቋምም ነው። ይህም ማለት ወንጌልን የሚሰብክ ሁሉ ማገልደም ሠቅ መታጠቅ አለበት ሳይሆን የትሕትና አቋም አባታዊ አገላለጥ መንፈሳዊ አርአያ ያስፈልገዋል

ማለት ነው:: ለምሣሌ አንድ ወንጌል ሰባኪ ሱፉን፣ ክራባቱን አሳምሮ እጁን ወደ ኪሱ ወጣ ገባ እያደረገ በትካዜ መንፈስ እየተንጐራደደ ወንጌልን አስተምራለሁ ቢል ምንም አዋቂ ቢሆን አርአያ ክህነት ስለሌለው ሰሚዎች ታሪክ ተማሩ እንጂ ሕይወት ያለውን ቃል አይተውና ሰምተው አልተመለሱም:: ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ መሲሕ ክርስቶስ የተናገረው ትንቢት /ኢሳ.42÷1-4/ አርአያ ክህነትን የሚመለከት ነው:: ሰባኪ ወይም መምህር የእግዚአብሔር ትርጁማን ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ትርጁማን ከሆነ የእግዚአብሔርን ቋንቋ ማወቅ አለበት:: የእግዚአብሔርን ፊ ቃድ የማያውቅ የእግዚአብሔርን ቋንቋ የማይሰማ ሰባኪ የእግዚአብሔር ትርጁማን ለመሆን እንዴት ይችላል::

ስለዚህ ሰባኪው በመንፈሳዊ ሕይወት የተ ቃኘ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ከሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ሙሉ በሙሉ ተርጉሞ ለማስተላለፍ ይችላል:: ነቢያት በመንፈሳዊ ሕይወት የተ ቃኙ አርአያ ክህነት ያላቸው ስለነበሩ የእግዚአብሔር ትርጁማኖች ነበሩ /ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር/ «እግዚአብሔር እንዲህ አለ» እያሉ መልእክታቸውን አድርሰዋልና ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የእግዚአብሔርን ቋንቋ አውቀው የእሱ ትርጁማኖች ለመሆን በቅተዋል:: ክርስቶስ ከቤተክርስቲያን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ስለማይለይ ቋንቋው ገብቷቸው መልእክቱን የሚያስተላልፉለትን ሐዋርያት አሁንም እየጠራ ነው::

## መ. ራስን አለመስበክ

ሰባኪው በስብከት መድረክ ላይ ቆሞ ራሱ፣ የሚሠራውን ሥራ በመተንተንና እራሱን በመካብ ጊዜን የሚያሳልፍ መሆን የለበትም:: እንዲያውም መድረኩ የክርስቶስ መንግሥት የሚሰበክበት ስለሆነ በጣም አስፈላጊ በሆነ ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ስለራሱ እንዲተርክ አይፈቀድም:: ሰባኪው ስለዚህ ጉዳይ ዮሐንስ መጥምቅን እንደ ምሳሌ ቢወስድ ጥሩ መመሪያ ይሆነዋል:: ዮሐንስ መጥምቅ ለጠየቁት ሰዎች የሰጠው መልስ «እኔ በገዳም የሚሰብክ አዋጅ ነጋሪ ነኝ፣ የእግዚአብሔርን መንገድ አጽዱ ጥረጉ» የሚል ነው:: /ማቴ.3÷11-12፣ ዮሐ.1÷27/:: ስለመሲሕ ግን ሲናገር የጫማውን ጠፍር ለመፍታት እንኳ የማይቻለው መሆኑን በግልጥ መሰከረ:: ሰባኪው በስብከቱ መድረክ ላይ በዚህ ዓይነት መልእክቱን ሲያስተላልፍ፣ ማለት የራሱን ኢምንትነት የራሱን ድካም የእግዚአብሔርን ግን ኃይልና ሥልጣን ቢናገር ሰሚዎችም ለእሱ የሚገባውን ክብር አይነሱትም::

## ሠ. የሰባኪውና የአድማጮች ግንኙነት

ሰባኪው ትምህርቱን ከመጀመሩ በፊት አድማጮችን በዓይኑ መ ቃኘትና ፍላጐታቸውን በሐሳቡ መለካት ይኖርበታል:: ረግተው ቦታ እስኪይዙ ወደሱም እስኪመለከቱ ድረስ መጠበቅ አለበት:: ከዚያ በኋላ በተሰጠው ርዕስ ወይም ለበዓሉ ተስማሚ በሆነ ርዕስ ትምህርቱን ይጀምራል:: ከሚሰጠው ትምህርት ውስጥ የትምህርቱ ምሥጢርና

የሰሚዎች አቋም መመጣጠን ይኖርበታል። አንዳንድ ሰባኪዎች ምን ዓይነት ሰሚዎች እንዳሏቸው ሳይለኩ ብዙ ይናገራሉ። እነዚህ ሰባኪዎች ለራሳቸው እንጂ ለሌላው አያስተላልፉም። እነርሱ መናገራቸውን እንጂ ለሰሚዎች አሳሰቡም። ለሰሚዎች የሚያስቡ የስብከት ዓላማ የገባቸው የወንጌል ሰባኪያን ግን የሰሚዎቻቸውን አቅም ያውቃሉ /1ኛ ቆሮ.3÷1-3፣ ዕብ.5÷12-14/። የዚህ ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ በተናጋሪውና በሰሚዎች መካከል መግባባት ይሆናል። በትምህርት ላልበሰሉ ምእመናን ስለ ሳይንስና መጽሐፍ ቅዱስ ልዩነት ወይም ግንኙነት እንሥቼ አቀርባለሁ ቢል ሰባኪው የራሱን ዕውቀት እንጂ የሰሚዎችን አቅም አልተመለከተም ማለት ነው። በዕውቀት የበሰሉ ሰዎች አስተምረን አስረዳን ብለው በጠየቁት ቀን አራቆ አመሥጥሮ ሊያስረዳ ይችላል /1ኛ ቆሮ.2÷6/።

ረ. የስብከት ሰዓት

የስብከት ሰዓት ሊያጥርም ሊረዝምም ይችላል። በዓሉ እንደ ልደት፣ እንደ ጥምቀትና እንደ ትንሣኤ ያለ ሕዝብ ለሌላ ግላዊ ሥራ የማይቸኩልበት ከሆነ አንድ ሰባኪ ብቻ ሳይሆን ሁለት ሦስት ሰባክያን እየተፈራረቁ ሲሰብኩ ቢያድሩና ቢውሉ ትልቅ ፈውስ ነው /የሐዋ ሥራ 20÷7። ምእመናኑ የሃይማኖታቸውን ታሪክ ያጠናሉ። የቤተክርስቲያና ቸውንም ሥርዓት ያውቃሉ።

ሕዝብ ወደ ሌላ ሥራ ለመሄድ የሚቸኩልባቸው ዕለታት ግን ስብከቱ እጥር ምጥን ብሎ ቢበዛ ለ ሩብ ሰዓት መሆን አለበት፣ ምእመናን በየፋብሪካቸውና በልዩ ልዩ መንግሥታዊ ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሠሩ ከሆነ ሰዓት እንዳያልፍባቸው፣ ወይም ሰዓት ያልፍብናል ብለው ፈርተው ትምህርቱን ሳይሰሙ እንዳይሄዱ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርንና ሰውን የማገናኘት ግዴታ ስላለባት በዚህ ሁሉ ትኩረት ልትሰጥበት ይገባል። አባቶች የተወጉትን ያቆዩትን ልጆች ለመከታተል ያስቸግራቸዋልና።

ሰ. ርዕስን መጠበቅ

ሰባኪው ሊጠነቀቅባቸው ከሚፈለጉት ዋና ዋና ግዴታዎች በትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ርዕስን መጠበቅ ነው። ርዕስ ማለት ቃሉ እንደሚያሳየው የትምህርቱ መነሻ ወይም ራስ ማለት ነው። ለበካር /ጀማሪ/ ሰባኪዎች ርዕስን ጠብቆ መስበክ በጣም ያስቸግር ይሆናል። ይልቁንም ትምህርቱ የሚሰጠው በ ቃል እንደሆነ በካሩ ሰባኪ በጣም ይቸግረዋል። ያሰበውም ከፍርሃት የተነሣ ይጠፋዋል። ይደነጋገረዋል። ቶሎ እንዲያልቅለትና ከሰው ፊት እንዲገላገል ብቻ ግራ ቀኝ አማትቶ ይቀመጣል። በጽሑፍ የሚሰጥ ስብከት ከሆነ ግን አስቦ ተጠንቅቆ ጽፎ ስለሚቀርብ ርዕሱን ጠብቆ ይሄዳል። ልሙድ ሰባኪ ቢጽፍም ባይጽፍም ርዕስ አይለቅም። ሰው ማንነቱ ተለይቶ የሚታወቀው በገጹ በፊቱ እንደመሆኑ መጠን ስብከትም ስለምን፣ ስለማን እንደተናገረ የሚታወቀው ርዕሱ ተጠብቆ ሲነገር ነው። ርዕሱን ባለመጠበቅ በግዴለሽነት የሚሰጥ

ትምህርት ለአድማጮች ጥቅም ካለመስጠቱም በላይ ተናጋሪውንም ያስገምታል። ርዕስ ሳይጠብቅ የሚናገር ሰባኪ የሰከረን ሰው ይመስላል። የሰከረ ሰው ሚዛኑን ጠብቆ ካለመርገጡ የተነሣ ሽቅብ ቁልቁል እንደሚረግጥ ርዕስ ጠብቆ የማይናገር ሰባኪም የሚናገራቸው ነጥቦች ሚዛን ካለመጠበቃቸው የተነሣ ምሥጢራቸው የተበታተነ ነው። ርዕስን ጠብቆ መናገር በቅዱሳት መጻሕፍት የተለመደ ነው። የሙሴ ኦሪት የነቢያት ትንቢት የተነገሩት ርዕሳቸውን ጠብቀው ነው። ኋላም በአዲስ ኪዳን ጌታና ደቀመዛሙርቱ ባስተማሩት ትምህርት የተፋለሰ ርዕስ የለም። ሐዋርያትን መስሎ በክርስቶስ መንበር ላይ ሆኖ የሚያስተምር ሰባኪው ካህን በሚያስተምርበት ጊዜ ሁሉ የጌታንና የሐዋርያትን ትምህርት ማስተዋል አለበት። የተሰጠው ወይም ሊናገር የተነሣው ስለእምነት እንደሆነ የእምነትን ምንነት እያስፋፋ በእምነት የተጠቀሙትን ሰዎች እየጠቀሰ በአስረጅነት በማቅረብ ቢሰብክ ርዕስ ጠብቋል። ስለ ጸሎትም ስለምጽዋትም በሌሎችም የክርስቲያን ምግባራት ርዕሳቸውን ጠብቆ ቢያስተምር ሰሚዎችን ይጠቅማል። ግዴለሽ ከሆነ ግን ቃሉን እዚህም እዚያም በማንጠባጠብና በማዝረክረክ ስለእምነት ጀምሮ እንደሆን ያን ሳያሥር ስለጾም፣ ስለምጽዋት፣ ስለሌላም ሁሉ ቢቀባጥር ሰሚዎችን ይጐዳል እራሱም ይጐዳል።

ሸ. ሰባኪው የሚናገረውን የሚያምን መሆን አለበት

እመኑ ብሎ የሚያስተምር ከሆነ ራሱ በቅድሚያ ስለሚናገረው ነገር ርግጠኛ መሆን አለበት /ጢሞ ካልዕ 1÷2/። የሚያምነውን የሚያውቅ መሆን አለበት። ቃሉም ሆነ ትምህርቱ አወላዋይ አገላለጥ እንዲኖረው አያስፈልግም፣ «ወይም» የሚል አማራጭ ቃል፣ «ይመስለኛል» የሚል የፌዝ ቃል ስብከቱን ያረግበዋል /ካልዕ ቆሮ.1÷18/። ስለዚህ በተቻለ መጠን ሰባኪው ትምህርቱን በተረጋገጠ ሁኔታ ያስተላልፈ እንደሆነ የአድማጮችን ስሜት እንዳይባዝን ለጉጥ ይይዘዋል።

በዚህ ዓይነት የሚያስተምር ሰባኪ ሰሚዎችን ገዝቷቸዋል ይባላል። እነርሱም ትምህርቱን ለመስማት ልባቸው ይሰቀላል። ያደንቁትማል። /ማቴ.7÷28-29፣ ሉ.ቃ19÷48/። በቤተክርስቲያን መመሪያ መሠረት የስብከት ማዕዘን /ማዕከል/ ምሥጢረ ሥጋዌ ነው። የቤተክርቲያን ትምህርት ትናንት ለነበሩት ዛሬም ላሉት ኋላም እስከ ዓለም ፍጻሜ ለሚነሡት ባለመለወጥ የሚኖር የሕይወት ምንጭ ነው /ዮሐ.4÷14/። ይህንን የሕይወት ምንጭ የሰጠን ኢየሱስ ክርስቶስም ዘለዓለማዊ ነው /ዕብ.13÷8/።

# ምዕራፍ ሁለት

## የስብከት ዓይነቶች

የስብከት ዓይነቶች ሁለት ናቸው::

አንዱ ባለ አንድ ሐረግ ነው:: «አንድ ሐረግ ቢስቡ ዱር ይሰበስቡ» እንደሚባለው ሁሉ ለርዕስ የያዘውን አንድ በረፍተ ነገር በማብራራት ተመሳሳይ ከሆኑ ጥቅሶች ንባቦችና ታሪኮች ጋር በማዛመድ ሙሉ ስብከት ይሰጥበታል::

ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ለዕለቱ በዓል የተነበበውን ምንባብ በሙሉ በአጫጭር አገላለጥ ማቅረብ ነው:: እነዚህ ሁለት የስብከት ዓይነቶች ብዙ አቀራረብ አሏቸው::

ሀ. <u>እንደ ሰምና ወርቅ ይቀርባሉ፡</u> ለምሳሌ በማቴ.7- የሚታየው ግብዝ ሰው በወንድሙ ዓይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ለማውጣት ሲታገል በራሱ ዓይን ውስጥ ግን ሞፈር ተደንቅሮበት መገኘቱን ጌታ መስክሯል፣ ከዚህ ንባብ ውስጥ ጉድፍ ቀላል ኃጢአት ሞፈር ከባድ ኃጢአት እንደሰምና ወርቅ ሆኖ ገብቷል፣ ማቴ.13÷ የተሰጠው ትምህርት በሙሉ የሰምና ወርቅ ግርፍ ነው::

ለ. <u>እንደ አንፃርም ሆኖ ይቀርባል፡</u> በማቴ.7- መጨረሻ ላይ የክርስቶስን ትምህርት ሰምቶ የሚሠራው የማዕበል ብዛት ያላፈረሰው ቤቱን በዐለት ላይ የሠራ ሰውን ይመስላል:: ቤቱን በዐለት ላይ መሥርቶ ስለሠራ የሰውየው ቤት በማዕበል ብዛት እንዳልፈረሰ ሁሉ የክርስቶስን ትምህርት ሰምቶ በሥራ ላይ የሚያውል ሰውም በመከራ ብዛት ሃይማኖቱን አይተውም፣ አይለውጥም፤ የክርስቶስን ትምህርት ሰምቶ የማይሠራው ደግሞ የማዕበል ብዛት ያፈረሰው ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሞኝ ሰውን እንደሚመስል ተናግሯል፣ ቤቱን በአሸዋ ላይ ስለሠራው የሰውየው ቤት ፈጥኖ እንደፈረሰ ሁሉ የክርስቶስን ትምህርት ሰምቶ የማይሠራ ሁሉ መከራ ፈተና በመጣ ጊዜ ፈጥኖ ሃይማኖቱን ይክዳል ማለት ነው::

ሐ. እንዳንድ ጊዜ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሎች እንደ ሰምና ወርቅ ወይም እንደ አንፃር ሳይሆን በራሳቸው ንባብ ብቻ ወርቅ ሆነው ይፈታሉ::

ይህም እንደ ኅብር ቅኔ ማለት ነው:: በዮሐ.6- ስለሰማያዊው ኅብስት የተሰጠው ትምህርት በዚሁ ወንጌል በምዕራፍ 10 ክርስቶስ እኔ ነኝ መልካም ጠባቂ ብሎ ራሱን ለምእመናን ያስተዋወቀበት አገላለጥ በኅብር ቅኔ መልክ የቀረበ ነው፣ ባፈታትና በአቀራረብ ልዩ ልዩ መልክ ይኑረው እንጂ ሰባኪው እንደተመቸው ወይም እንደችሎታው የተሰጠውን ርዕስ ከነዚህ ከገለጽናቸው በአንዱ መልእክቱን ያስተላልፋል፣ መጀመሪያ ርዕሱን ለሰሚዎች ያስተዋውቃል፣ በመተርጐም በማብራራት፣ ለምሳሌ

ርዕሱ ስለጾም እንደሆነ ከሁሉ በፊት ጾም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ቃሉን ይተረጉማል::

ከዚያም ጾም ለማንኛውም ሃይማኖት ግዴታ መሆኑን በብሉይ ኪዳን ሰዎች ዘንድ የጾም ሥርዓት እንዴት እንደነበረ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ሰዎች ውስጥ በጾም ከእግዚአብሔር ጋር የታረቁትን ሰዎች በአስረጅነት በመጥቀስ ማቅረብ የሰባኪው ግዴታ ነው::

በብሉይ ኪዳን ማለቂያ አካባቢ የነበሩ የፈሪሳውያን ጾም እንዴት እንደነበርና በቤተክርስቲያን በምን ዓይነት ሥነ ሥርዓት ልንጾም እንደታዘዝን፣ በጾማችን ወራት ምን ማድረግ እንዳለብን፣ ስንት አጽዋማት እንዳሉና የጾም ሥርዓት የጀመረልን ማን መሆኑን፣ ቅዱሳን ሐዋርያትና ሌሎችም አበው በጾም ከፈጣሪያቸው ጋር ያላቸው ወዳጅነት የጠበቀና የጠነከረ መሆኑን፣ እኛም ይህን የክርስቲያኖች ጽኑ መሣሪያ ጾምን አክብረን እንድንጠብቀውና ጠላታችን ዲያብሎስን ድል እንድንነሣበት ጥንቃቄ የሚያስፈልግ መሆኑን ለምእመናን ያስተላለፈ እንደሆነ ስብከቱ ለምእመናን ራሳቸውን የሚያዩበት ብርሃን ይሆንላቸዋል:: አንዳንድ ሰባክያን በክብረ በዓል ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት አጋጣሚ ትምህርት ለማግኘት ምእመናን ጓጉተው በጉጉት በሚጠባበቁበት ወቅት በመስበኪያው ዐውደ ምሕረት ሆነው የበዓሉን ታሪክ በመተረክ ብቻ ብዙ ሰዓት ይወስዳሉ፤ ነገር ግን ሕዝቡ በፀሐይ ከመቀቀልና ከመጠበስ በቀር ለሕይወቱ ትዝታ የሚሆነው ትምህርት ይዞ አይመለስም፤ ታሪኩንም ቅሉ ሰባኪው በቃሉ ያጠናው እንደመሆኑ መጠን ስለሚያንበለብለው ለአድማጮች ከነፋስ ጋር የሚናገር ይመስላቸዋል:: ስለዚህ ሰባኪው ታሪክ በሚተርክበት ጊዜ ታሪኩን ከአምስት ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ ተርኮ ወደ ማራቀቅና ማመሥጠር ከገባ የሰሚዎችን ሐሳብ ከታሪኩ ይልቅ መራቀቁ ወደርሱ ይስብለታል:: ለምሳሌ የጊዮርጊስን በዓል ለማክበር ሚያዝያ 23 ቀን ለሚሰበሰብ ሕዝብ የጊዮርጊስን የሕይወት ታሪክ አንዷ ታሪክ ሳትቀር ልተርክ ከማለት ጊዮርጊስ መቼ እንደተወለደ፣ በማን ዘመን እንደነበረና ክርስቲያናዊ ተጋድሎውን መቼ እንደጀመረ፣ ተጋድሎው በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እንደተፈጸመ ባጭሩ ካስረዳ በኋላ ቤተክርስቲያን እንደ ጊዮርጊስ ያሉ የሃይማኖት ጀግኖች ልጆች ምን ጊዜም የሚያስፈልጋት መሆኑን፣ ሰማዕትነት በእሳት በመቃጠል በስለት በመቆረጥ ብቻ ሳይሆን በሱሰኝነት የሚወዱትን ነገር ለመተው የሚደረገው ሙከራ ሁሉ ሰማዕትነት መሆኑን፣ በሃይማኖት በኩል ሽሙጫንና ግልምጫን ሳይሰቀቁ አምልኮተ እግዚአብሔርን አጠንክሮ መያዝ የሚገባን መሆኑን ይህንንና ይህን የመሳሰለውን ሁሉ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ሕይወት ልንማር ይገባል፣ በመጨረሻም የድልና የጽድቅ አክሊል ባለቤቶች እንሆናለን ብሎ የተጠማውን ሕዝብ ቢያረካው ለሰባኪው የሥራ ፍሬ ነው::

ሰባኪው መልእክቱን በሚያስተላልፍበት ጊዜ ድምፁ ባሕርያዊ ድምፅ መሆን አለበት:: እጅግ የናረ እንደሆነ የሚሰማው ፍሬ ነገሩ ሳይሆን ውበቱ ነው፣ ድምፁ እጅግ አንጀት እርቆት ወደ ሆዱ የገባ ከሆነ ምእመናን ሊሰሙት አይችሉም:: ስብከት በንባብ መልክ አይከርም እንደ

ውይይትም አይረግብም። በካር ሰባኪዎች በድምፅ በኩል ሁለት ዓይነት ጉድለት አለባቸው፣ አንዳንዶች ከፍርሃት የተነሣ ትንፋሻቸው እስኪቆረጥ ድረስ እንደ ግእዝ ስድ ንባብ ይናገራሉ።

አንዳንዶች ደግሞ ትንፋሻቸው ወደ ሆዳቸው ይገባና የሚሉት አይሰማም። በስብከት ዘዴ የሠለጠኑ ልሙዳን ሰባኪዎች ግን በሜዳ ላይ እንደሚተም ውኃ ሳያከናም ሳያረግቡም አስማምተው ያጥለቀልቁታል፣ በድርቅ የተጐዳው ሁሉ በትምህርታቸው ይረካል /መዝ.71÷6/።

ቤተክርስቲያን የማዳን መልእክቷን ስታስተላልፍ የቆየችው በየአካባቢው ሕዝብ ቋንቋና ባሕል ነው። የጊዜውን አቋምና የሕዝቡን ስሜት መደብ አድርገው የእግዚአብሔርን ቃል ያስተላልፋሉ፣ አንድ ሰባኪ ምሳሌ ቢመስል ታሪክም ቢተርክ ሰሚው ሕዝብ በለመደው በሚገባው በሚችለው መሆን አለበት፤ ለምሳሌ ትምህርቱ ለገበሬዎች እንደሆነ በእርሻና በዘር፣ በስንዴና በእንክርዳድ፣ በገብስና በጊንጭ ይህን በመሳሰለው ገበሬ በሚያውቃቸው ቃላትና ምሳሌዎች የሆነ እንደሆነ በቀላሉ ሊገባው ይችላል። ለዓሣ አጥማጆች በመረብ በዓሣ፣ ለነጋዴዎች በሸቀጥ ዕቃ በትርፍና በኪሣራ፣ ለሴቶች በእርሾና በዱቄት፣ በቅርብ በሚያውቁትና በሚሠሩት መስሎና አጣምሮ ያቀረበው እንደሆነ ትምህርቱ ብዙ ነፍስ ወደ እግዚአብሔር ይመልሳል። በማቴዎስ 13 ከመጀመሪያው ጀምሮ የተጻፈውን በመመልከት ለአስተማሪ የተማሪዎችን ስሜት ለመሳብ በእነርሱም አስተሳሰብና በሚያውቁት ቋንቋ መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን ለማወቅ ይቻላል።

በስብከት ያለፈውን ታሪክ መልክ ካለው ሁኔታ ጋር በማወራረስ ይሰጣል፣ ይህንንም ከላይ ተመልክተናል፤ ያለውንም ሁኔታ ካለፈው ጋር በማገናዘብ ትምህርት ለመስጠት ይቻላል። 2ኛ ጴጥ.2÷1 ስብከት ባለፈውና ባለው ሁኔታ ላይ ብቻ ሳይወሰን ለወደፊትም በትንቢት መልክ ይነገራል፣ /ማቴ.24፣ ሉቃ21÷23 23÷2፣ 2ጴጥ.3÷3/።

ምእመናን በተሰበሰቡበት አደባባይ ለማስተማር የሚቆመው መምህር ራሱ የሚያውቀውን ሁሉ የምእመናን አእምሮ ሊወስነው በሚችለው መመጠን እንዳለበት ባለፈው ተነግሯል።

እዚህ ላይ ልናስታውሰው የምንፈልገው በስብከት ጊዜ ስለ ምሥጢረ ሥላሴ አንድነትና ሦስትነት የሕዝብ አእምሮ ሊወስነው የማይችለውን ምሥጢር ሲተርኩ መዋል ፈሊጥ አይደለም፤ ለተማሪዎች መንፈሳዊ ኮሌጅ ወይም በካህናት ማሠልጠኛ የሚሰጠውን የነገረ መለኮት ትምህርት ለየዋሖን ምእመናን ማቅረብ ቃለ እግዚአብሔርን የመስማት ፍላጐታቸውን ይዘጋዋል፤ ዳግመኛም ወደ ትምህርት ገበታ አይቀርቡም፡ ምሥጢሩ የማይገባቸው ስለሆነ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌም ሆነ ስለ ምሥጢረ ሥላሴ በሰፊው አብራርቶ ማስተማር የሚቻለው ቅድም በጠቀስናቸው የትምህርት ተቋሞች ውስጥ ነው።

የስብከት ዓይነት የተለያየ ቢሆንም ዓላማው አንድ ስለሆነ ሰባኪው በራሱ የተፈጥሮ ስጦታና የአነጋገር ስልት መጓዝ አለበት እንጂ የሌሎች

ሰባኪዎችን የአነጋገር ስልት ለማስመሰል መሞከር የለበትም። የ ቃሉም ባለቤት እግዚአብሔር ስለሆነ ከራሱ ጥናት ጋር በራሱ ስልት መናገር አለበት። ብዙ ሰባኪዎች በድምጽና በአቋም ሌሎችን ለመምሰል ኃይለ ቃላቸውንም በመውረስ መልእክት ለማስተላለፍ ይሞክራሉ። ነገር ግን ድምፁና አቋሙ የእነርሱ ስላልሆነ አይዋሐዳቸውም። አንዳንድ ጊዜም ሳያስቡት ወደ ራሳቸው የአነጋገር ጠባይ ይገባሉ፣ በዚህ ጊዜ ያ ዘር እና የአነጋገር ስልት የእነርሱ አለመሆኑ ይታወ ቃል።

ስብከት እንደምክር ሆኖ ይሰጣል። እባካችሁ ምእመናን እንዲህ አድርጉ፣ እንዲህ ግን አታድርጉ፣ ብሎ ሰባኪው ትምህርቱን በምክር መልክ ያስተላልፋል /1ኛ ጴጥ.5÷1/። «አመን ትድናለህ፣ እመኚ ትድኛለሽ» ምክር ነው፣ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» ብሎ ማስተማር-ምክር ነው፣ ምክር አባታዊ መሆን አለበት። መላልሶ መምከርም አለበት።

ምክሩ ግቡን እስኪመታ ድረስ ሰባኪው ሳይታክትና ሳይሰለች ከመከረ እግዚአብሔር ያግዘዋል። ብዙዎችንም ከጥፋት ይመልሳል። እንደምክር በማባበል ብቻ ሳይሆን በመገሠጽም ትምህርት ይሰጣል። በምክር አልመለስ ያሉ የአባያ ጠባይ ያላቸውን ፌዘኞች መምህሩ በመራራ ቃል ይገሥጻቸዋል። እንደ ዮሐንስ መጥምቅ ያለ መምህር ከሆነ በእግዚአብሔር ሕግ ላይ የሚያፌዙትን ሄሮድሳዊ ጠባይ ያላቸውን ባለሥልጣኖች ፈሪሳዊ ጠባይ ያላቸውን ትምክህተኞች ክርስቲያኖች ነን ባዮችን በተግሣጽ ይገርፋቸዋል። የማቴ.3÷7-11፣ 14÷4።

ጌታም ፈሪሳውያንን በግብዝነታቸው ገሥጿቸዋል። «ወዮላችሁ» ብሏቸዋል /ማቴ.22÷21-23/። የክርስቶስ ወራሾች ሐዋርያትም ትምህርታቸውን ለዓለም ያስተላለፉት በዚህ ዓይነት ነው። /ማለት በምክር በማባበልና እንዲያም ሲል በተግሣጽ ነው።/ 1ኛ ቆሮ.4÷25፣ 1ኛ ጢሞ.5÷20፣ 2ኛ ጢሞ. 4÷2። ምክሩም ሆነ ተግሣጹ ምእመናንን የሚያንጽ /ምንተ ንግበር?/ የሚያሰኝ እንዲሆን ያስፈልጋል /የሐዋ.ሥራ2÷36/። በማናቸውም ዓይነት የሚተላለፈው ስብከት ዓላማው ክርስቶስ የሞተላቸው ምእመናን እንዳይጠፉ ለመጠበቅ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

## ስብከት የሚሰጥባቸው ቦታዎች

ሀ. የስብከት ማዕከላዊ ቦታ ቤተክርስቲያን ናት። ምእመናን በቤተክርስቲያን ሲሰበሰቡ የወንጌል ሰባኪው በቅዳሴው መካከል ወንጌል እንደተነበበ ያለዚያም በቅዳሴው ማለቂያ «እግዚኦ» ከተባለ በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል ያሰማል። እግረ መንገዱንም በነፃ የተሰጠ ንን የአምላክ ሥጋና ደም እንዲቀበሉ ይጋብዛቸዋል። ቤተክርስቲያን ምእመናንን የማስተማር ብቻ ሳይሆን የመመገብም ኃላፊነት ስላለባት

ትምህርቱን ከምግባር ጋር አዋሕዶ ቢያቀርብላቸው ጥሪውን ሰምተው ወደ መንፈሳዊው ማዕድ ይቀርባሉ። ስብከት በቤተክርስቲያን የሆነው ለዚህ ነው።

ለ. ስብከት በምእመናን ቤት፣ ሐዋርያት በጥንት ስብከተ ወንጌልን ማስተማር የጀመሩት በምኩራብ ነው። ቀን በምኩራብ ሲያስተምሩ ውለው ማታ ደግሞ እንረፍ ሳይሉ በምእመናን ቤት ጸሎተ ማዕድ እየፈተቱ ሐዋርያዊ ተልእኳቸውን ያሟሉ ነበር፣ /የሐዋ.ሥራ.2÷46-47/። ተከታዮቻቸውም አባቶች ቤተ ክርስቲያን ነጻነቷን እስካገኘችበት እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ በምእመናን ቤትና በአይሁድ ቤተመቅደስ ብቻ ሳይሆን በካታኮምብ /ግበ - በምድር ስብከታቸውን ሲያካሂዱ ቆይተዋል። ትንሣኤን በመ ቃብር ውስጥ ሆነው ሲመሰክሩ ኑረዋል። ቤተክርስቲያን የትንሣኤ መመስከሪያ መድረክ ስለሆነች ሳይቸግር በየቤቱ እየተሰበሰቡ እንሰብካለን ማለት ግን ሐዋርያዊ ትውፊት አይደለም። የክርስቶስ ትንሣኤ የማስተማሪያና የመማሪያ ቦታ ቤተክርስቲያን ብቻ ናትና።

ሐ. እግዚአብሔር እንደ ፀሐይና እንደ ዝናብ ቦታ ሳይለይ ለኃጥኡም ለጻድቁም እኩል መድረስ ስላለበት ሰባኪው የወንጌልን መልእክት በልዩ ልዩ ምክንያት ተፈርዶባቸው ወደ ወህኒ ቤት ላሉ እስረኞችም ማስተላለፍ አለበት። በወህኒ ቤት ኃጢአት የሠሩ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን አንድ ጊዜ ወንጀለኞች ተብለናል፣ በኅብረተሰባችን ዘንድ ተጠልተናልና ብለው በኃጢአት ላይ ኃጢአት በጥፋት ላይ ጥፋት እንዳይጨምሩ እዚያው ባሉበት ሁነው እግዚአብሔርን ይቅርታ ቢለምኑ ቢጠይቁ ንስሐ ቢገቡ ሥጋ ወደሙን ቢቀበሉ፣ ከእግዚአብሔር ምሕረትን የሚያገኙ መሆናቸውን ማመልከት ተገቢ ነው። ክርስቶስም ከሞተና ከተቀበረ በኋላ ከትንሣኤው ቀደም ብሎ የነጻነትን ወንጌል የሰበከው በነፍሳት ወኅኒ ቤት መሆኑን ጠቅሶ ቢነግራቸው /1ኛ ጴጥ.3÷10/። ያለጥርጥር ወደ ንስሐ ይመለሳሉ። እግዚአብሔር በወኅኒ ቤት እንኳ ያሉትን እንደማይዘነጋ ከተረዱ ተስፋ የቆረጠው ልቡናቸው እንደገና ይለመልማል። ስለዚህ ሰባኪው በወኅኒ ቤትም ድምፁን ቢያሰማ ብዙ ነፍሳት ይድናሉ።

መ. የታሠሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆን የታመሙ ሰዎች በሞትና በሕይወት አፋፍ ያሉ ስለሆነ ተስፋ በመቁረጥ ሆዳቸው ይባባል። በዚህ ጊዜ ነው የሚያጽናና የሚያስፈልገው። ክርስቶስ ሲያስተምር ብዙ ጊዜ ከበሽተኞች ጋር ይገናኝ ነበር። በሽተኞች ወዳሉበት ይሄድ ነበር። በሽተኞችም እሱ ወዳለበት ይመጡ ነበር። ተከታዮቹ ሐዋርያትም እንደዚሁ ነበሩ ማቴ.9÷18-26፣ ዮሐ.5÷1-9፣ የሐዋ.ሥራ.3÷6-9። የሐዋር.ሥራ 3÷6-9፣ የሐዋ.ሥራ 5÷15-16/። የቤተክርስቲያን የመዳን መልእክት ሁለገብነቱ ማለት ላመነ ሁሉ የሚሰጥ መሆኑ የሚታወቀው ይህ ሲሆን ነው። ወንጌልን የሚያስተምር ካህን ለበሽተኞች የወንጌልን ተስፋ ከሰበከ በሞት አፋፍ የሚገኙ በሽተኞች ተስፋ ባለመቁረጥ ለነፍስ አባታቸው ኃጢአታቸውን ተናዘው ሥጋውን ደሙን ተቀብለው

ያርፋሉ። ቢድኑም ጥሩ የቤተክርስቲያን አማኞች ሆነው ከዚህ ዓለም እስኪለዩ ፈጣሪያቸውን ያገለግላሉ። በዚህ ፈንታ ግን ሰባኪው ወደ በሽተኛው ሂዶ «ምን ኃጢአት ብትሠራ ነው በል እግዚአብሔር ይህን ሁሉ መዓት ያመጣብህ በአንተ ላይ የደረሰውን ለጠላት አይስጠው አሁንማ ምን ቀረህ መሞትህ እኮ ነው» እያለ በመራራ ንግግር ተስፋ ቢያስቆርጠው በሽተኛው ይደነግጣል። ተስፋም ይቆርጣል። መቼስ አንድ ጊዜ እግዚአብሔር ጠልቶኛል ብሎ ንስሐ ሳይገባ ሥጋውን ደሙን ሳይቀበል ይሞታል። ከሰባኪው የሚፈለገው ይህ ሳይሆን ከላይ እንደተገለጠው «አይዞህ ትድናለህ ደኅና ነህ፣» በሚል አጽናኝ የተስፋ ቃል ድምፁን ያሰማው እንደሆነ እንዲህ ያለው ሰባኪ የክርስቶስንና የሐዋርያትን አሠር የተከተለ ነው ለማለት ይቻላል። በሽተኛውም ሕመሙ ይቀንሳል። በብዙ የክርስቲያን ሀገሮች ለበሽተኞች ወንጌልን ማስተማር የተለመደ ነው። በሰንበትና በሌሎችም የበዓላት ቀኖች የወንጌል መምህራን ካህናት በየቤቱና በየሆስፒታሎች እየዞሩ ለሕመምተኞች የመዳን ወንጌልን ይሰብካሉ። በእኛም ዘንድ ይህ ቢለመድ መልካም ነው።

ሠ. በሽተኛው በድንገተኛም ሆነ በቆየ በሽታ ምክንያት ከምድራዊ ሕይወት በሚለይበት ጊዜ ካህኑ በሕመሙ ጊዜ እንዳልተለየው ሁሉ በመቃብሩ ቦታ በመገኘት ዛሬ በሞት ጥላ ሥር የተኛውን ምእመን ነገ በትንሣኤ ክርስቶስ የሚነሣ መሆኑን ሞት ለክርስቲያኖች የሕይወት ፍጻሜ አለመሆኑን ገልጦ በዚያ ለተሰበሰበው ሕዝብና ለቤተሰብ አልቃሾች ሰፊ ትምህርት መስጠት አለበት። ሟች ወንድማቸውን እኅታቸውን ለመሸኘት የተሰበሰቡ ምእመናን ሁሉ ይህ የሞት ጥሪ ሳይደርሳቸው በፊት በንስሐ ለሥጋውና ለደሙ የተዘጋጁ እንዲሆኑ ሰባኪው በመልእክቱ ማስጠንቀቅ ይኖርበታል። በመቃብር አጠገብ ትንሣኤ፣ በሞት አጠገብ ሕይወት መኖሩ ለክርስቲያኖች ግልጥ እንዲሆንላቸው ያስፈልጋል።

ተ. በመከራ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በደስታም ጊዜ በኀዘን ቦታ ብቻ ሳይሆን በደስታም ቦታ እየተገኘ ሰባኪው የእግዚአብሔርን ቃል ማስተላለፍ አለበት። ጌታ በሞትና በበሽታ ጊዜ ሳይሆን በደስታቸውም ጊዜ በተደሰቱት መካከል ይገኝ ነበር። በተአምራት ለመገለጥና አዲሱን ወይን የሰው ሕይወት ለዓለም ለማስተዋወቅ አዲሱ የሰው ሕይወት ጣዕሙ እንዴት እንደሆነ ለማሳየት። ታዲያ በመቃብር አጠገብ ትንሣኤ ማለት እንዴት ያለ መሆኑን በእነ አልአዛር ትንሣኤ ያሳየ ክርስቶስ /ዮሐ.11÷44/። አሁንም በሠርግ ቤት ተገኝቶ ከሰው ሠራሹ ማለት ከምድራዊው ሕይወት ይልቅ በአምላክ ፊቃድ የተመሠረተው የክርስትና ሕይወት መንፈሳዊው ሕይወት የሚጥም የሚያረካ መሆኑን ሰበከ። የክርስቶስ ተከታይ ካህንም በሠርግ በሚገኝበት ጊዜ ተሾሞቶ ጠጥቶ ሰክሮ ለመውደቅ ሳይሆን አዲሱን ቤታቸውን ለመመሥረት የተዘጋጁት ሙሽሮች ሕገ እግዚአብሔርን ቢጠብቁ እግዚአብሔር የሰጣቸውን የጋብቻ ሕግ አክብረው ቢኖሩ ክርስቶስ

የሚሰጣቸውን ጣፋጭ ሕይወት የሚያገኙ መሆኑን መንገር አለበት። ንጹሕ ዘርና ሰላማዊ ኑሮ የሚገኘውም ጋብቻውን እግዚአብሔር ሲባርከው በእሱ ሲፈጸም መሆኑን ሰባኪው መግለጥ አለበት። ካህኑ የእግዚአብሔር ወኪል ስለሆነ በኃዘንም ሆነ በደስታ ቦታ በሚገኝበት ጊዜ አርአያ ክህነቱን ጠብቆ የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ መናገር አለበት። ወደ ነገረ ዘርቅ ወደ ሐሜትና ወደ ሌላም እርሱን ወደማይመለከት ጉዳይ ከሄደ ግን እግዚአብሔርን ያስቆጣል፡ ቤተክርስቲያንንም ያስድባል።

ቸ. የቤተክርስቲያን ጉዞ በዓለም ውስጥ እንደመሆኑ መጠን የዓለምን የኑሮ ዓይነቶች በጨው ትምህርት የማጣፈጥ ኃላፊነት የቤተክርስቲያን ነው።

ስለዚህ ትምህርቷን ምእመናን በሚሰበሰቡበት ቦታ ሁሉ በገበያ ቦታም እንኳ ማድረስ አለባት። በገበያ ሻጩም ሆነ ገዢው በሚሸጡበትና በሚገዙበት ጊዜ እንዳይተፋፈሩ፤ አንዱ ለሌላው የሚገባውን እንዲያደርግለት፣ ሁለገብ የሆነ ትምህርት ቢሰጥ ቤተክርስቲያን ብዙ ትርፍ ታገኛለች። በተለይም የዚህን ዓለም ሕይወት በገበያ አነጻጽሮ ገበያው ሲገዛ ሲሸጥ ከዋለ በኋላ እንደሚበተን የዚህን ዓለም ለጊዜው ያለ መስሎ የሚጠፋ መሆኑን ገልጦ ወደማታልፈው ወደ ነፍስ ገበያ ወደ ቤተክርስቲያን መጥታችሁ በነጻ የተሰጠንን የአምላክን ሥጋና ደም ተመገቡ ብሎ ጥሪ ቢያደርግ ብዙዎች ይሰሙታል። እነ ቅዱስ ጳውሎስ በጥንተ ስብከት በምኵራብ ብቻ ሳይሆን በገበያም ያስተምሩ እንደነበር የሐዋርያት ሥራ ያስረዳል /የሐዋ.ሥራ 17፥17/።

የወንጌል ትምህርት ለሁሉም በሁሉም ቦታ አስፈላጊ መሆኑን ለማመልከት እዚህ ላይ አንዳንድ ቦታዎችን ብናወሳም የወንጌል ትምህርት መልእክቱ በዚሁ ይወሰናል ለማለት አይደለም። በይፋ በአደባባይ ብቻ ሳይሆን ቤተሰብንም ጓደኛንም ከክፉ ሥራና ከአጉል እምነት እንዲጠበቁ ማስተማር በቤተክርስቲያንና በሌሎችም ሸንጎዎች ወንጌልን እንደማስተማር ይቆጠራል /የሐዋር.ሥራ5፥42/። ያም ሆነ ይህ ቤተክርስቲያን መረቧን በየአቅጣጫው ከጣለች የድካሟን ዋጋ እንደማታጣ ግልጥ ነው። ይህም ሊሆን የሚችለው መረቡን ወደ ባሕር የሚጥለው አጥማጅ መረቡን ከመጣሉ በፊት የመረቡን ሁኔታ የአየሩን ጠባይ ዓሣ በብዛት የሚያዝበትን አይቶና ተጠንቅቆ ከጣለ ያሰበውን ያህል እንደሚይዝ ሁሉ ምእመናንን በቃለ እግዚአብሔር ለማጥመድ ወደ ዓለም የተላከው የወንጌል ሰባኪም ብዙ ነፍሳትን ለማጥመድ የሚችለው መረብ ትምህርቱን አዘጋጅቶ የጊዜውን ሁኔታና የሚያስተምራቸው ሰዎች በምን ዓይነት ሊሳቡ እንደሚችሉ ገምቶ የተነሣ እንደሆነ ነው። መንፈሳዊ ኃይል ያለው ሰባኪ በመጠጥ ቤቶችና በሌሎችም መሰል ቦታዎች እየተገኘ ሕይወታቸውን ላጡት የሕይወት ቃል ቢነግራቸው የጠፋውን ለመፈለግ ይመጣሉ። በዚህም የክርስቶስ ወኪል መሆኑን በግብር ያረጋግጣል። ክርስቶስ ከኃጥአን ጋር ይውል ነበር፣ ለቀራጮችም የንስሐ ትምህርት ይሰጥ ነበር። ክርስቶስ ኃጢአትን ይጠላ ነበር። ኃጥአንን ግን ይወድ ነበር። ወደ ንስሐ

እንዲመለሱ ሰባኪውም ከኃጢአታቸው ሳይሳተፍ ኃጢአተኞችን ለመመለስ ኃጢአተኞች በብዛት ወደሚገኙበት አካባቢም የእግዚአብሔርን ድምፅ ማሰማት አለበት:: እግዚአብሔር ኃጥአንን ለመፈለግ ወደዚህ ዓለም መምጣቱ /ማቴ.9÷13/:: የገባቸው እነ ቅዱስ ጳውሎስ /1ኛ ቆሮ.9÷19-23/:: ሌሎችም ሐዋርያት ሁሉን ለመጥቀም በየቦታው ሁሉ እየተገኙ የእግዚአብሔርን አዋጅ ያስተላልፉ ነበር::

# ምዕራፍ አራት

## በዕድሜ፣ በዕውቀትና፣ በሀብት ለተለያዩ ምእመናን የሚሰጡ ስብከቶች

ሕፃንም ሆነ ዐዋቂ፣ የተማረም ሆነ ያልተማረ፣ ድሀም ሆነ ሀብታም በአንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን ከመንፈስ ቅዱስ በጥምቀት ከተወለዱ በኋላ ሁሉም እኩል ናቸው:: ወንጌልን የሚያስተምር ካህን ለእነዚህ ሁሉ የሚገባቸውን ትምህርት እያዘጋጀ ማቅረብ አለበት::

ሁሉም በያሉበት ዓለም የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው እንዲጠቀሙ::

## ሀ. ስብከት ለሕፃናት፡-

በሀገራችን ሕፃናት የሃይማኖት ትምህርት አያስፈልጋቸው ይመስል ካህናትም ሆኑ ወላጆች እንደ ትርፍ ነገር ይቆጥሯቸዋል:: አንዳንድ ወላጆች ካልሆኑ በቀር ብዙዎች ወላጆች ወደ ቤተክርስቲያን እንሂድ ብለው በሚነሡበት ጊዜ እንኳ «ደግሞ የልጅ ቤተክርስቲያን መሄድ ምን ሊያደርግ ነው» እያሉ ይከለክሏቸዋል:: ካህናትም በቤተክርስቲያን እንደ ቁም ነገር አድርገው አይቆጥሯቸውም:: ይህም አለማወቅ ነው:: አንዳንድ ወላጆች ግን ካህናትም ሆኑ ምእመናን ልጆቻቸው ቡራኬ እንዲያገኙላቸው ማለዳ ከእንቅልፋቸው እየቀሰቀሱ ወደ ቤተክርስቲያን ይወስዷቸዋል:: ታሪካቸው በወንጌል እንደተመዘገበላቸው እንደነዚያ ደግ ወላጆች /ማቴ.19÷13-15/:: እነዚያ ወላጆች ሕፃናትን ለማስባረክ ወደ ጌታ ሲያቀርቧቸው ሕፃናትን ከቁም ነገር ባለመቁጠር ሐዋርያት ተቈጥተው ነበር:: ጌታ ግን መንግሥተ ሰማያት እንደነሱ ላሉ የምትሰጥ መሆኗን በዚያ ለነበሩት ሁሉ አስተማረ:: አሁንም ቤተክርስቲያን የሕፃናትን ወደ እርሷ መምጣት እንደ ቀላል ነገር ልትቆጥረው አይገባም:: አትቆጥራቸውምም::

ሕፃናት በልጅነት ወራት ሃይማኖታቸውንና ታሪካቸውን ያጠኑት እንደሆነ ለሀገራቸውም ለቤተክርስቲያናቸውም ምርጥ ዕቃይ ሆናሉ::

ወደ ብሉይ ኪዳን ታሪክ ብንመለከት ነቢያት ሃይማኖታቸውንና ታሪካቸውን የወረሱት በሕፃንነት ነበር:: ለምሳሌ እነ ዳንኤል፣ እነሲድራቅ፣ ሚሳቅና፣ አብዳናጎ ተማርከው በሄዱበት አገር የንጉሡን ግርማ ሳይፈሩ አምላካችን ያድነናል ብለው ወደ እሳት ለመወርወር

የወሰኑትና አምላካቸውንም ያመሰገኑት በልጅነታቸው ሃይማኖቸውን ስለተማሩ ነው:: /ዳን.3÷ /

በአዲስ ኪዳንም የቤተክርስቲያን ልጆች ከሕፃንነታቸው ጀምረው በቤተክርስቲያናቸው የሚሰጠውን ትምህርት ክርስቲያናዊ ሥርዓት እየተከተሉ በማደጋቸው ለክርስትና ትምህርት ምስክሮች የሆኑ ሕይወታቸውንም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያደረጉ በአነስተኛ ግምት የሚቆጠሩ አይደሉም:: ለሕፃናት የሚሰጥ ትምህርት በሦስት ቢከፈል ጥሩ ውጤት ይኖረዋል:: ይኸውም በመጀመሪያ ወጣቶችን በዕድሜ ለሦስት መክፈል ይቻላል:: አንደኛ ከሰባት እስከ አሥር ያሉትን፣ ሁለተኛ ከአሥር እስከ አሥራ አምስት ያሉትን ሦስተኛ ከአሥራ አምስት እስከ አሥራ ስምንት ያሉትን ማለት ነው::

ከሰባት እስከ አሥር ዕድሜ ላሉት ሕፃናት ከቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ ነክ የሆኑትን ሁሉ በሙሉ ቢሰጣቸው በሕፃናት አእምሮ የሠረጸ ትምህርት በደንጊያ ላይ እንደተቀረጸ ቅርጽ እንደሚባለው ሁሉ ታሪኩን በ ቋሚ ጭምር ይይዙታል:: አይረሳቸውም:: ከተቻለም ታሪኩን በ ቃልና በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በሥዕልም ቢያስተምሯቸው የበለጠ ያስደስታቸዋል:: ከአሥር እስከ አሥራ አምስት ላሉት ደግሞ ማለትም ታሪኩን አጥንተው ለፈጸሙት በታሪኩ ውስጥ የተሸፈነውን ምሥጢርና የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ታሪክ ቢያስጠኗቸው የማይነ ቃቅ አዕማድ ይሆናሉ:: በተለይም በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለተዋሕዶ ሃይማኖታቸው ሲሉ አባቶቻቸው የተቀበሉትን መከራና ያፈሰሱትን ደም በሚገባ አገላለጥ ሲነግሯቸው ወጣቶቹ በቤተክርስቲያን ፍቅር ይ ቃጠላሉ:: እነርሱም እንደ አባቶቻቸው ስለቤተክርስቲያናቸው ፍቅር ግንባራቸውን ለመስጠት ይዘጋጃሉ:: ከአሥራ አምስት እስከ አሥራ ስምንት ዓመት ላላቸው ደግሞ ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያንን መሠረታዊ ታሪክ እምነትና እንዲሁም ቀኖና በቤተክርስቲያን ስንት ጉባኤያት እንደተሠ ሩና ያሳለፏቸውንም ቀኖናዎች ቢያስጠኑዋቸው ከዚህ ጋር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከነማን ጋር ግንኙነት እንዳላትና እንደሌላት፣ የእምነቷን ሥርዓትና የቀኖናዎቿን መጠን ቢያስተምሯቸው በሃያ ዓመት ዕድሜአቸው ለማንኛውም ነገር ተጠያቂዎች ይሆናሉ:: ካህናትም ቢሆኑ በዓለም ሸንጐ ቀርበው ቤተክርስቲያናቸውን ለዓለም የሚያስተዋውቁ ይሆናሉ:: ሌላም ሥራ ቢይዙ በደረሱበት ሁሉ ለቤተክርስቲያናቸው ምስክር ይሆናሉ:: እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቤተሰቦችና ሌሎችም ክርስቲያኖች የሆኑ ሁሉ ወጣቱን የሚያሳድጉት በዚህ ዓይነት ነው:: ካደገ በኋላ እንደ ጥሪውና እንደ ዝንባሌው ወደ ልዩ ልዩ የሥራ መስክ ቢገዝም ካህኑና ምእመኑ ነገረ ሃይማኖትን ለማወቅ እኩል ናቸው:: ምእመናኑ በሃይማኖት ስም ማንም ሊያወናብዳቸው አይችልም:: ካህናት የቤተክርስቲያንን መመሪያ ከልጅነታቸው ጀምረው ያጠኑት ስለሆነ የቤተክርስቲያን አስተዳደር አዲስ አይሆንባቸውም:: ማዛዝና መታዘዝ እንዴት እንደሆነ ያው ቃሉ::

የተጣለባቸውንም ከፍተኛ ኃላፊነት አደራ /የሐዋርያነት አደራ/ በታማኝነት ይጠብ ቋሉ /2ጢሞ.3÷13-15/።

## ለ. ስብከት ለምሁራንና ላልተማሩ ምእመናን፡-

በሥላሴ ስም ተጠምቀው በአዲስ ሕይወት ለሚመላለሱ ምእመናን የተማሩም ቢሆኑ ያልተማሩ ሁሉም ወንድማማቾች ናቸው። እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ወደ ቤተክርስቲያን በሚመጡበት ጊዜ ሰባኪው ለሁሉም የሚድኑበትን ትምህርት ማስተላለፍ አለበት። ይልቁንም ዐዋቂ ነን ባዮች በአላዋቂዎች እንዳይመኩና እንዳይታበዩ የዚህ ዓለም ዕውቀትና ፍልስፍና ከእግዚአብሔር የተገኘ ስለሆነ ባላዋቂው ወንድማችን እንኩራበት፣ እንታበይበት ከትሕትና የራቀውን ጥበብና ፍልስፍና አጠፋለሁ ብሏልና እግዚአብሔር /ኢሳ.29÷14፣ 1ቆሮ.1÷19/ እያለ የቅዱሳት መጻሕፍትን አስረጅ እያሰባሰበ ቢያስረዳቸው ከትዕቢት ይፈወሳሉ። የሰው ዕውቀት አንዱ ከሌላው እየሸመተው ነው እንጂ ከራሱ ባሕርይ የተገኘ አይደለምና፣ ከራሱ ያልተገኘ ከሆነም ሊያስመካው አይገባም 1ኛ ቆሮ.4÷7። ከዚህም ጋር ዐዋቂዎች ምእመናን በሙያቸው ያልተማረውን ወንድማቸውን እንዲያስተምሩ እሱም እንደነሱ ኑሮውን እንዲያሻሽል እንዲያደርጉ ለወንድማቸው ሕይወት ኃላፊነት ያለባቸው መሆናቸውንና የእርሱ ውድቀት ለሃይማኖታቸውና ለቤተክርስቲያናቸው ውርደት መሆኑን ሳይሸሽግ ገልጦ መናገር አለበት። የሌሎች የእምነት ድርጅቶች ለትምህርቱና ለምክሩ ማሠሪያ የሁላችንም ፈጣሪ እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ያደረገውን ጉዞና ራስን ማዋረድ አብራርቶ ማስተማር አለበት፣ ይህ የሆነ እንደሆነ ሁሉም በድርሻው ይሠራል።

ያልተማሩት ምእመናንም ከተማሩት ጋር በጸሎትና በአምልኮት ቦታ በቤተክርስቲያን በአንድነት በሚገኙበት ጊዜ ከምሁራን ወንድሞቻቸው ጋር በክርስቶስ አንድ መሆናቸውን እንዲያውቁትና ዝቅተኛነት እንዳይሰማቸው በተፈጥሮ የተሰጣቸው ዕውቀት መብዛት ማነስ ሳይሆን እያንዳንዱ በተሰጠው መክሊተ ሃይማኖት ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን ማትረፉና አለማትረፉ ብቻ መሆኑን ቢያስተምር አልተማርኩም የሚለው «አልተማርኩም አላውቅም ስለማላውቅ የወደድሁትን ሁሉ እሠራለሁ ብጠየቅም ስለማላውቅ ነው እላለሁ» ብሎ ያሰበውን የሞኝ ግምት ያስተወዋል።

በዕውቀት የተለያዩ ምእመናን ብቻ ሳይሆኑ በሀብትም የተለያዩ ምእመናን የአንዲት ቤተክርስቲያን አባል ናቸው። እነዚህ በሁለት ዓይነት የኑሮ ደረጃ ላይ የቆሙ ምእመናን አምልኳቸውን ለመግለጥ ቃለ እግዚአብሔርን ለመስማት ወደ ቤተክርስቲያን ይመጣሉ። በዚህ ጊዜ ብልሁ መጋቢ ካህን ለሁለቱም የሚስማማ ሁለቱንም የሚያገናኝ ሁለቱንም ያቀፈ ስብከት ማስተማር አለበት።

ለባለጸጎች ብልጽግና ከእግዚአብሔር የተገኘ መሆኑን፣ እግዚአብሔር ሰውን ባለጸጋ ማድረጉ ለሌላው እንዲተርፍ እንጂ ከሚበቃው በላይ እንዲያካብት አለመሆኑን ገልጦ ለማስረዳት በብሉይ ኪዳን ከነበሩት ባለጸጎች በሀብታቸውና በንብረታቸው ሳይመኩ እንግዳ በመቀበል

የተራበን በማብላትና የተጠማን በማጠጣት፣ ለታረዘ በማልበስ እግዚአብሔርን ያገለገሉትን አበው ታሪክ ለአድማጮች በሰፊው አብራርቶ ማሰማት የሰባኪው ተቀዳሚ ሥራ ነው።

ከዚያም በአዲስ ኪዳን ትምህርት ሀብት ሁሉ ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው፣ ክርስቲያኖች ምድራዊ ድልብ እንዳያደልቡ /ማቴ.6÷19-21/ መታዘዛቸውን በማስመልከት ገንዘብ መውደድ የኃጢአት ሥር መሆኑን /1ኛ ጢሞ.6÷10/ ባለጸጐች አድማጮችን ማስገንዘብ ይኖርበታል። ገንዘብ የሚወዱና በድልብ ላይ ድልብ የሚያነባብሩ ሀብት የእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን የዘነጉ ስግብግብ ባለጸጐች በክሕደት ወጥመድ ማለት ገንዘብን በማምለክ ወጥመድ የተያዙ መሆናቸውንና አወዳደቃቸው የከፋ መሆኑን እንዲያውቁት አስረጅ አቅርቦ ማስጠንቀቅ አለበት /ሉቃ.12÷15-21፣ 1ኛጢ. ሞ.6÷10/ በመጋቢነቱ ካወቀበት ግን ሀብት ሁሉ የእግዚአብሔር ስለሆነ ባለጸጋ መሆን ኃጢአት አይደለም። ማከፋፈሉ ግን ብልህ መጋቢነትን ይጠይቃል። ይህ ካልሆነ ማለት ሀብት አግኝቶ በመጋቢነት ካልታወቀ የገንዘቡ የሀብቱ ባለቤት በመጣ ጊዜ ውርደት ያስከትላል /ማቴ.24÷45-51/። ይህን የሐዲስ ኪዳን ትምህርት ያጤነ ለገንዘብና ለእግዚአብሔር ማለትም ለሁለቱም መገዛት የማይቻል መሆኑን ተረድተው ብዙ ሀብታቸውን ርግፍ አድርገው ትተው እጃቸውንም ልባቸውንም ለእግዚአብሔር የሰጡ አበው ታሪክ እንደ ፈርጥ ሆኖ ቢጠቀስ የሰባኪውን ማስጠንቀቂያ ያጠነክርለታል። በምክር ቢያስተምር አንሰማም ያሉትን ባለጸጐች ግን እንደ ያዕቆብ ሐዋርያ በሙሾ ጠባይ ወዮላቸው ባለጸጐች እያለ ማስጠንቀቂያውን ሊያቀርብ ይችላል። የእግዚአብሔር አስተርጓሚ አዋጅ ነጋሪ ነው። /ያዕ.5÷1-6/። ምናልባት ደንግጠው ቢመለሱ መምህሩ በዚህ ሁሉ መልእክቱን ካስተላለፈ በኋላ ቢሰሙት ያድናቸዋል ባይሰሙት ግን ራሱን ያድንበታልና /1ኛጢሞ.4÷16/። ዋናው ቁም ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስጠይቀው ሀብት ሳይሆን በመጋቢነት አለማወቅ ነው። መልእክቱ የሚተላለፈው ለባለጸጐች ብቻ ሳይሆን ለድሆች ምእመናንም በባለጸጐች ወንድሞቻቸው እንዳይቀኑና ጥላቻው እንዳያድርባቸው ሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን እንደ መግቢያ አድርጐ ትምህርቱን መጀመር አለበት። ከዚያም በማያያዝ ድሆች ምእመናን የእግዚአብሔርን በረከት እየለመኑ ቢሠሩ እንደሌሎች ወንድሞቻቸው እራሳቸውን የሚችሉበት ገንዘብ ለማግኘት መቻላቸውን የሚያበስር ዜና ቢነገራቸው የእግዚአብሔርን ረድኤት አጋዥ አድርገው ወደ ሥራው ይሠማራሉ።

ባለጸጐች ትምክህትና ትዕቢት ስስት እንደሚያጠቃው ሁሉ ድሆችንም ምቀኝነትና ስንፍና ያጠቃዋል። እግዚአብሔርንም ያማርራሉ። ሰባኪው እንደ መልካም ዶክተር የሁለቱንም የውስጥ በሽታ ነቅሎ ለመጣል ማንኛውንም ዘዴ መፈተን አለበት።

በአጠቃቅም ለሁለቱ ተቋኊዎች አስታራቂ መገናኛ ድልድይ የሚሆነው የካህኑ ትምህርት ስለሆነ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። ቤተክርስቲያን ሀብታሞችን የምትደግፍ ከሀብታሞች ጋር የምታጨብጭብ ድሆችን ግን

የምትጸየፍ የምትንቅ እየመሰላቸው ብዙ ሰዎች የተሳሳተ አነጋገር ስለሚናገሩ ካህኑ ስለሁለቱ የሚሰጠው ትምህርት አሻሚ ሳይሆን ግልጥ ሆኖ የሚታይ መሆን አለበት:: ሰባኪው መልእክቱን በሚያስተላልፍበት ጊዜ ስለዚህ ሁሉ ነገር በቅድሚያ ያወቀና የተረዳ መሆን አለበት:: አንዳንድ በካር ሰባክያን ባለጸጋውን ነቅፈው ድሀውን የደገፉ እየመሰላቸው ገንቢ ምክርና ተግሳጽ እንደመስጠት ፈንታ ባለጠግነትን ወይም ሠርቶ ማግኘትን የሰይጣን ግብር አስመስለው ያቀርቡታል:: በዚህ ጊዜ ብዙ የቤተክርስቲያን ሰዎች ሰባኪው የሚለው ስለማይገባቸው «አትሥሩ ተቀምጣችሁ ዋሉ ማለቱ ነውን?» ብለው በልቡናቸው ቅሬታ ያድርባቸዋል:: አንዳንዶች ግን ይህንኑ አነጋገር ምክንያት በማድረግ ከቤተክርስቲያን እየራቁ ይሄዳሉ:: ሌሎች ደግሞ ድህነትን የእግዚአብሔር ቁጣ በማስመሰል ባለጸጐችን የሚክብና የሚያሞካሽ የውዳሴ ከንቱ ስብከት ይሰብካሉ:: በዚህ ጊዜ ደሃው የቤተክርስቲያን አባል በባለጠጋው ወንድሙና በዚያ ሰባኪ ላይ የጥላቻ መንፈስ ያድርበታል:: ከዚህም የተነሣ «ላለው ቅንጭብ ያረግዳል፣» እንደሚባለው «ቤተክርስቲያን ያላቸውን ሰዎች ነው የምትደግፈው ድሃን ቁም ነገር አትልም» በማለት ከቤተክርስቲያን ይር ቃል:: ስለዚህ ከላይ እንደተገለጠው የሰባኪው ፍሬ ነገር በሁለቱም ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ሁሉንም ያቀፈ እንዲሆን ያስፈልጋል::

# ምዕራፍ አምስት

## ስብከትና ፖለቲካ

ፖለቲካ ማለት የምድራዊ መንግሥት የአመራር ሥርዓትና ስልት ነው:: አንድ አገር ወይም ሕዝብ በመንግሥትነት ከታወቀ የራሱ የሆነ ፖለቲካ አለው:: ነገሩ በጣም ግልጥ እንዲሆን የመንግሥትና የሕዝብ ግንኙነት የመንግሥትና የመንግሥት ግንኙነት ሁሉ ፖለቲካ ይባላል::

ይህን የመንግሥት ፖለቲካ የሚመሩ በዚሁ የሠለጠኑ ባለሥልጣኖች አሉ:: መንግሥታቸው ከሕዝባቸው ጋር ወይም ከሌላው መንግሥትና ሕዝብ ጋር ሊኖረው የሚገባውን የአመራር ሥልት በተማሩት ትምህርት ያውቁታል:: ወንጌልን የሚሰብክ ሰባኪም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ስላለው ግንኙነትና በሰውና በሰውም መካከል ስላለው የወንድማማችነት ግንኙነት በሰፊው ተንትኖ ያው ቃል:: ወንጌልን የሚያስተምር ሰባኪ ስለፖለቲካ ጥናት ቢኖረውም ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ በፖለቲካ ውስጥ እንዳይገባ መጠንቀቅ አለበት:: በቤተክርስቲያን የወንጌል ሰባኪዎች እነ ቅዱስ ጳውሎስ በወንጌልና በፖለቲካ መካከል ያለውን ልዩነትና ግንኙነት በደንብ ያውቁ ነበር፣ ምእመናን ምንም እንኳ በክርስቶስ ነጻ የወጡ ቢሆኑም በህገር ደረጃ ደግሞ አለ ቃ የለሽ መስለው እንዳይታዩ ይመክሯቸው ነበር /ሮሜ.13÷1-17/:: እግዚአብሔርን መፍራት የአገርን መሪዎች ማክበር በቤተክርስቲያን ጥንተ ስብከት የታወቀ ነው:: /1ኛ ጴጥ.2÷13-14/:: እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ሕጉን መጠበቅ ነው::

መሪዎችን ማክበር ማለት ስለሀገር ስለሕዝብ አንድነትና ነጻነት እነርሱ በሚያዙት መሠማራት ማለት ነው። ሰባኪው እነዚህን መሪ ንባቦች በጤናማ ትርጓሜ ተርጉሞ ለአድማጮች ቢያሰማ በፖለቲካውና በወንጌል ትምህርት ሰላምና አብሮ መሥራት ይመሠረታል። አንድ የቤተክርስቲያን ምእመን የሚኖርባት ሀገር በግፈኞች ከተወረረች መንግሥት ያን ምእመን በጠላት ላይ እንዲዘምትና የሀገሩን ዳር ድንበር እንዲያስከብር ቢያዘው ሃይማኖቴ ይከለክለኛል ሊል አይችልም። ይህን የሃይማኖት ቅርንጫፍ ያቋቋሙት አገሮች የጥፋት መልእክታቸው በሀብትና በዕውቀት ዝቅተኛ ወደሆነው ወደ ሦስተኛው ዓለም እስያና አፍሪቃ ይልኳቸዋል። እነርሱም እየመጡ ሰውን ግራ ያጋቡታል ለራሳቸው ግን የራሳቸውን መከላከል ብቻ ሳይሆን የጦር ፋብሪካቸው እንዳይዘጋባቸው ልዩ ልዩ የመለያያ ዘዴዎችን በመፍጠር በሰው ደም ይነግዳሉ። ሰባኪው ዓይናማ ከሆነ ፖለቲካና ስብከት የሚለያዩበትን ማለትም ልዩነታቸውን ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። ዓላማቸው የተለያየ ነውና። በፖለቲካ ከምድራዊ መንግሥት ጋር ግጭት ለመፍጠር አንዳንድ አድር ባዮች ይሞክራሉ። ይህም የተጀመረው አሁን ዛሬ አይደለም። ቤተክርስቲያን ስትጀመር ጀምሮ የነበረ ፈተና ነው። የቤተክርስቲያን ራስ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከቄሣር መንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር ለማጣላት የሞከሩ ሄሮድሳውያን ራት አግባዎች «ለቄሳር ግብር መስጠት ይገባል ወይስ አይገባም?» የሚል ጥያቄ አቅርበውለት ነበር። እርሱ በሃሳባቸው አይገባም ቢላቸው ከቄሣር መንግሥት ጋር ለማጋጨት ነው። ይገባል ቢላቸው ደግሞ ይህስ ጥሩ የሃይማኖት መምህር አይደለም ብለው አላዋቂውን ሕዝብ ለማወናበድ ነው። መድኃኒ ግን የቤተክርስቲያን አባላት ምእመናን አለቃ የለሾች አለመሆናቸውን ሲገልጥ የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርን ግን ለእግዚአብሔር መስጠት ይገባል አላቸው። /ማቴ.22÷15-22/ አሁንም ሰባኪው የፖለቲካውና የወንጌልን ጠባይ አጥርቶ ካወቀ ከስህተቱ ይጠነቀ ቃል። ለገዥዎች እንድንታዘዝ ለእነርሱም የሚገባውን ሁሉ እንድናደርግ ቅዱሳት መጻሕፍት አዘዋል። እንድንሰብክ የታዘዝነው ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን ብቻ ነው /1ኛ ቆሮ.1÷23/።

አንዳንድ ሰባክያን በየጊዜው የሚነሡ ባለሥልጣኖችን በማሞካሸት እንጀራቸውን ያበስሉ እየመሰላቸው ወንጌልን ለመስበክ መስቀል ጨብጠው ቅዱስ መጽሐፍ ይዘው በቤተክርስቲያን የፖለቲካ ንግግር ያደርጋሉ። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት የተቀመጡ ምእመናን ሰባኪዎችን ይታዘቧቸዋል። ሌሎች ሰባኪዎች ደግሞ የተነሡበትን ርዕስ ማብራራት ሲያቅታቸው ያንዱን አመራር በመንቀፍ የሌላውን በመደገፍ የፓርቲ መሪዎችን ዓይነት ስብከት ይሰብካሉ። ይህ ዓይነቱ የሰባኪዎች መመሪያን አለማወቅ የቤተክርስቲያንን ዓላማና የአመራር አቅጣጫ አለማ ስተዋል ነው። ሰባኪው የግለሰብ ስም ወይም የፓርቲ ስም ሳይጠራ ፍርድ ተጓደለ ድሃ ተበደለ ብሎ ለመዝለፍም ሆነ ለመገሠጽ ይችላል። ያውም ራሱ በራሱ በቅዱሳት መጻሕፍት መነሻነት እንጂ በሌላ ተጽዕኖ የሌላ መሣሪያ በመሆን አይደለም። ድሃ ሲጮህ እሳቸው ቸል የሚሉትንና

ሊያገለግሉት የተሾሙትን ሕዝብ ሥ ቋዩና ችግር የማይመለከቱትን ባለሥልጣኖች በነሄሮድስ የደረሰውን የእግዚአብሔር መቅሰፍት አስረጅ አድርጌ ቢገስጻቸው የሐዋርያ ወጉ ነው /የሐዋ.ሥራ.12÷20-24/::

የፖለቲካ ባለሥልጣኖችን በተግሣጽ ብቻ ሳይሆን በምክርም ማገባበል ይገባል:: የያዙት ሥልጣን ከእግዚአብሔር የተገኘ መሆኑን ያለ እግዚአብሔር ፈ ቃድ ግን ምንም ሊያደርጉ አለመቻላቸውን /ዮሐ.19÷11/ ገልጦ ቢነግራቸው ያሉበትም የዳኝነት መድረክ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊያገለግሉበት የተሰጣቸው መሆኑን ቢቀበሉትም ባይቀበሉትም ማስተላለፍ ግዴታው ነው::

ስብከትና ፖለቲካ በዚህ አኳኋ ካልሆነ በቀር በቤተክርስቲያን ስም ወንጌልን እንዲያስተምር የተሰየመው ካህን በተንኮል ወይም መመሪያን ባለማወቅ በሞኝነት ወደ ፖለቲካ ውስጥ ገብቶ ከዘባረቀ ቢደግፍም ድጋፉ ቢነቅፍም ነቀፋው አያስመሰግነውም:: ይልቁንስ ሃይማኖቱን ቤተክርስቲያኑን ያስነቅፋል:: ያስጠላል:: የቤተክርስቲያን እምነትና ቀኖና ከፖለቲካ ሕግና መመሪያ የተለየ እንደመሆኑ መጠን ስብከትም ከፖለቲካ የተለየ መሆኑን በቅድሚያ አስረድተናል:: እንግዲህ የወንጌል ሰባኪዎች የተሰቀለውን ክርስቶስን ብቻ እንዲሰብኩ ይህች አነስተኛ መመሪያ በመጠኑም ቢሆን ትረዳለች::

በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ያለ ሰባኪ ስለዓለም አቀፍ የፖለቲካ አቋም የሚያውቅ መሆን አለበት:: አንድ መንግሥት በሌላው ላይ የሚያደርገውን ተጽዕኖ ማለት ጉልበታም ነኝ የሚለው መንግሥት በደካማው መንግሥት ላይ የሚያሳየው የትዕቢት ጠባይ በወንጌል ሰባኪው እንደበት መወገዝ አለበት::

አንድ መንግሥት የራሱን ርዕዮተ ዓለም ሌሎች ሕዝቦችና መንግሥትም ሁሉ እንዲይዙለት ይፈልጋል:: የእሱ ሃሳብ ተገዥዎችና ምጽዋተኞች እንዲሆኑ በሃይማኖት አሳቦና የሃይማኖት ልብስ ለብሶ መጽሐፍ ቅዱስን አስይዞ ቢጽ ሐሳውያንን በመላክ በሚሰጠው ርዳታ በማስፈራራት በሌላም በብዙ ዓይነት መንገድ ይጥራል::

ሃሳቡ ተቀባይ ቢያጣ ርዳታውን ያቆማል:: የጥፋት መልእክተኞችን እየላከ የውስጥ ለውስጥ ብጥብጥ እንዲነሣና ደም እንዲፋሰስ በጎረቤት ያሉ የወንድማማች ሀገሮችን በሐሳብ በመከፋፈል እርስ በርሳቸው እንዲፋጁ በማድረግ የሚፈጽመውን ሰይጣናዊ ወንጀል ሰባኪው ለምእመናን ማሳወቅ አለበት:: ያንን የፓለቲካ ሰዎች እንዴት እንደሚመለከቱት ሰባኪው በሰፊው ሊያስረዳ ይገባል:: ይህንንም በቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ሰዎችም ዘንድ በሰፊው ሊያስረዳ ይገባል:: ነገር ግን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ለ5,000,000 ሰዎች ሞት ምክንያት የሆነው ጦርነት እንደገና ለመቀስቀስና የሰውን ደም በከንቱ ለማፍሰስ ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ የጦር መሣሪያው ገበያ የደራ መሆኑን ገልጦ በዚህም አድራጐቱ ዓለም ከስሕተቱ የማይማር ነው፣ ካለ በኋ ሰባኪው ጦር በዓለም በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ ያደረሰውን ጉዳት

በመዘርዘር የአካል ጉድለት የሚገኙ ስንት ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን እንዳሉ፣ እንዲሁም ለሰው ልጆች መታወቂያ የሚሆኑ በብዙ ድካም የተሠሩ ዕቃዎችና የባሕል መጣሪያዎች እንደወደሙ፣ ብዙ ሕዝብ የሚኖርባቸው ከተሞች ከነዋሪዎቻቸው ጋር በሐይድሮጅን ቦምብ መጋየታቸውን በአስረጅ ጠቅሶ ጦርነትን ሲያወግዝ በጦርነት ሳቢያ በሰው ደም የሚነግዱ የጦር መሣሪያ ቸርቻሪዎችን የፖለቲካ መሪዎችንም ቢገሥጽ ሁለገብ ሰባኪ ይሆናል። በዚህ ፈንታ ማለት በእግዚአብሔር ገንዘብ ሰው ሰውን በመግደል ፋንታ ሰው የሚድንበትን የሥልጣኔ በር መክፈትና የራበው የሰው ዘር ዳቦ በልቶ የሚያድርበትን መንገድ ብንቀይስ እግዚአብሔር የሚደሰት መሆኑን በይፋ መስበክ ይገባዋል። ዓለም እንደ ልማዱ የእግዚአብሔርን ቃል አልሰማ ካለ ግን፣ ሁለቱ የጃፓን ከተሞች ሔሮሽማና ናጋሳኪ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም የጦር ወዳድ መንግሥታት እንደ ኮራዚን እንደ ቤተ ሳይዳ እንደ ሰዶምና እንደ ገሞራ ህልውናቸው ጠፍቶ የሚቀር መሆኑን ሰባኪው በማስጠንቀቂያ ቃል ማስረዳት አለበት። ጦርነት የብዙዎቻችንን ቤት አራቁቶ የብዙዎችንም ሕይወት በአስቃቂ ሁኔታ ያጠፋ ከአንዳንድ የፖለቲካ መሪዎች እንደ ሒትለርና ሙሶሎኒ ካሉ ጭንቅላት የሚመነጭ መርዝ ነው።

ስለዚህ ቤተክርስቲያን በሰው ልጆች መካከል ፍቅርን ሰላምንና እኩልነትን ትሰብካለች። ጠብን ለእኔው ብቻ ይሁን ማለትንና ከዚህም የሚመነጭ ጦርነትን ታወግዛለች።

# ምዕራፍ ስድስት

## ስብከትና ኦርቶዶክሳዊ ጠባዩ

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መድረክ ቆሞ የእግዚአብሔርን መልእክት የሚያስተላልፍ ካህን ኦርቶዶክሳዊ ለዛ ሊኖረው ይገባል። ማለት ቀደም ብሎ በመጀመሪያው ምዕራፍ እንደተናገረው የአነጋገሩ ቃና እጅግ ኮምጣጣ ያልሆነ የለዘበ /ማቴ.12÷20 ኢሳ.42÷1-6/ መሆን አለበት።

ስብከቱም ኦርቶዶክሳዊ ላህይ ኦርቶዶክሳዊ ጠባይ ሊኖረው ይገባል። አንዳንድ ሰባክያን ወንጌልን በሚያስተምሩበት ጊዜ ስለእግዚአብሔር መኖር ስለእግዚአብሔር ቀዳማዊነት ብቻ ሰብከው ይቀመጣሉ። ስለእግዚአብሔር ሕልውና በአይሁድ ቤተ መቅደስም ሆነ በእስላም መስጊድ በየጊዜው ስለሚሰበክ ይህ ስብከት የወል የሆነ ስብከት እንጂ የቤተክርስቲያን ስብከት ለመሆኑ ምልክት የለውም። ሌሎች ሰባኪያን ደግሞ ስለኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ብቻ ተናግረው በእሱ ያመንን እኛ አሁን በምን ዓይነት ሁኔታ መዳንን እንደምናገኝ መግለጫ ሳይሰጡ በዚሁ ብቻ ንግግራቸውን ይደመድማሉ። የዚህ ዓይነት ስብከትም ኦርቶዶክስ ባልሆኑ አብያተ ክርስቲያናትም ስለሚሰማ ይህ ስብከት ኦርቶዶክሳዊ አይደለም። ለስብከት ኦርቶዶክሳዊ ላህይ፣ ኦርቶዶክሳዊ ጠ

ባይ እንዲኖረው ከተፈለገ የሚከተሉትን መመሪያዎች መመልከት ይጠቅማል::

ሀ. መድረኩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንደመሆኑ መጠን በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የበዓል ቀን፣ የሷን ታሪክና ንጽሕናዋን፣ ቅድስናዋን፣ በእግዚአብሔር መመረጧን፣ በሰው ልጆች የመዳን ታሪክ ውስጥ ያደረገችውን አስተዋጽኦ፣ አምላክን መውለዷን፣ ስደቷን፣ በኋላ ለእኛ ለምእመናን ምሕረትን በማማለድ የታወቀች የታመነች አማላጅ መሆኗን ምእመናን አውቀው በእመቤታችን እንዲማጠኑ ገልጾ ገጸ ልቡናቸውን ወደ እመቤታችን መመለስ፣

ለ. የመላእክት በዓል በሚከበርበት ዕለት መላእክት በእግዚአብሔር ፊት ያላቸው የባለሟልነት ቦታ፣ የእግዚአብሔርን ምሕረት ለሰው ዘር የሰውን ጸሎትና ትሩፋት ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ የሚፈጽሙትን ቅን አገልግሎት፣ የእግዚአብሔርን ሕግ በሚጥሱ ላይ ደግሞ የእግዚአብሔር ኃይሉ መገለጫዎች መሆናቸውን፣ በቤተ ክርስቲያን አመሠራረት የፈጸሙት አገልግሎት በሚገባ ተገልጦ ድርሳናቸው ውስጥ ካሉት አንዳንድ ተአምራት አስረድቶ ምእመናንንም በመላእክት አማላጅነት ከፈጣሪያቸው ይቅርታን እንዲጠይቁ ምክር መስጠት፣

ሐ. በዓሉ የቅዱሳን እንደሆነ ቅዱሳን አበው በዓላውያን ፊት ስለ ክርስቶስ አዳኝነት መስክረው፣ በእሳት በስለት የተገደሉ ሰማዕታትም ቢሆኑ መናፍቃን ባፍ በመጣፍ ብለው የረቱ፣ ወንጌልን ዙረው ያስተማሩ፣ ምሁራንም ቢሆኑ «ኩኑ ቅዱሳነ እስመ አነሂ ቅዱስ::» እኔ ቅዱስ እንደሆንሁ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ የሚለውን መመሪያ በመከተል /ዘሌ.19÷2፣ ቀዳ ጴጥሮስ 1÷16/ ንጽሕናን ለማግኘት አርዑተ ምንኩስናን ተሸክመው ከኖሩት በመጠኑ ነካክቶ እነዚህ ቅዱሳን ለቤተክርስቲያን ትምህርትና ጠቅላላ አቋም የከፈሉትን መሥዋዕትነት በማብራራት አሁንም ከሞቱ በኋላ በቤተክርስቲያን ክብር የሚገባቸው መሆናቸውን ምእመናንም በቅዱሳን ጸሎትና ምልጃ ከፈጣሪያቸው ምሕረት የሚያስገኙ ቅዱሳንን እንዲመስሉ ማስተማር ምእመናንን ወደ ቅድስና ሕይወት ይመራል::

መ. ስለ ቤተክርስቲያን ቀኖና፣ ስለአጽዋማት:- በቤተክርስቲያን ጾም ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ ጾም ለክርስቲያኖች የሚገባ መሆኑን፣ መድኃኒታችን በምንጾምበት ጊዜ ልናደርገው የሚገባንን እንዴት እንዳስተማረን፣ በዚያም ትምህርት የጾምን ሕግ ከነአፈጻጸሙ የሠራልን መሆኑን፣ እሱም ራሱ መጾሙ፣ አያሌ ነቢያት በጾም ወደ ፈጣሪያቸው መድረሳቸው፣ በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ ጾም አምላካዊ ሕግ ሆኖ መሰጠቱ፣ ቅዱሳን ሐዋርያትና ከእነርሱም በኋላ የተነሡት ሊቃውንት የጾምን ጠቃሚነት እየሠሩ ማስተማራቸው፣ እኛም የጾምን ሕግ አክብረን ጠብቀን የያዝን እንደሆነ እግዚአብሔር ለአባቶቻችን

የሰጠውን ክብር ለእኛም የማይነፍገን መሆኑን በሰፊው አብራርቶ መስበክ፣ በእኛ ቤተክርስቲያን ስንት የጾም ወራት እንዳሉ ማሳወቅ::

ሠ. ስለ በዓላት:- በዓላት በብሉይ ኪዳን እንዴት ሲከበር እንደነበርና በሐዲስ ኪዳንም ቀኖናት የበዓላት አከባበር እንዴት እንደሆነ፣ በእኛ ቤተክርስቲያን ስንት የበዓላት ወራቶች እንዳሉና በዓል ማክበር ለዘፈን ለጨዋታ ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረቢያ እንዲሆን የተወሰነ መሆኑን፣ በዚያም ላይ በዓል ማክበር ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሕግ እንደመሆኑ መጠን በበዓላችን ቀን ልናደርጋቸው የሚገቡንን የክርስቲያን ሥነ ሥርዓቶች ማስተማር፣

ረ. ጠቅላላ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር አለማድረግ ብቻ ሳይሆን ማድረግንም የሚጠይቅ ነው:: ለምሳሌ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ካሉት ምእመናን ሀብታሞች ቢኖሩ እነዚህ ምእመናን የሰው የማይፈልጉ የራሳቸውን የማይሰጡ ቢሆኑ የሰውን ባለመፈለጋቸው ብቻ የክርስቲያንን ሥነ ምግባር አሟልተዋል ሊባሉ አይገባም:: ከእነርሱ የሚፈለገው የሰውንም አለመመኘት የራስንም ማካፈል ነውና:: በብሉይ ኪዳን ሕግ ነፍስ አትግደል ይላል:: በክርስትና ግን ለሞት ምክንያት አለመሆን ብቻ ሳይሆን ለሕይወት ምክንያት መሆን ያስፈልጋል:: ማለትም ማንኛውም ክርስቲያን ለወንድሙ ሕይወት ኃላፊነት አለበት ማለት ነው:: ወንድሙ ቢርበው ማብላት፣ ቢጠማው ማጠጣት፣ ቢራቆት ማልበስን፣ የመሳሰሉትንም ደጎና ሥራ ሁሉ ማድረግ ይገባዋል::

ሰ. በዝክር፣ በሰንበቴና በማኅበር ማዕድ ላይ በሚገኝበት ጊዜ ሰባኪው ሰንበቴም ዝክርም ማኅበርም በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ዘንድ ሲሠራበት የኖረ ክርስቲያናዊ ትውፊት መሆኑን፣ ትውልድ ሁሉ እንዲያጠናው አስረጅ ጠቅሶ ማስረዳት፣ /ለምሳሌ የሐዋ. ሥራ2÷42-46/ ሐዋርያት በጥንተ ስብከት በአንድ ላይ እየተሰበሰቡ ከጸሎት በኋላ የሚበሉትን ራት፣ በህብት በንብረት ሳይለያዩ የኖሩትን ኑሮ::

## ለሰባኪው የሚሆን ተጨማሪ ማሳሰቢያ

1. በማያውቀው ቋንቋ ጥቅስ ባይጠቅስ ጥሩ ነው:: ፍቺውን ስለማያውቀውና አነባበቡም ስለሚበላሽበት ከትዝብት ላይም እንዳይወድቅ፣

2. ከማያውቀው መጽሐፍ አይጥቀስ፣ ሰሚዎች የማያውቁ መስሎት የአንዱን ለአንዱ እየሰጠ ያጋጨው እንደሆነና ምናልባት ከሰሚዎች ውስጥ ከርሱ የበለጠ የሚያውቅ ያለ እንደሆነ ሰባኪው መሳቂያ ይሆናል:: ይህ ስሕተት ብዙ ጊዜ በመደጋገም የሚፈጸም ነው:: ይህንን ስሕተት የሚፈጽሙት ከመማራቸው በፊት ዐዋቂ ለመባል የሚፈልጉ ናቸው:: በልማድ በስሕተት ከሚጠቀሱት ጥቅሶች ለምሳሌ በሃይማኖተ አበው በሕገ መነኮሳት «ለእመ ሆርከ ብሔረ ባዕድ ኩን ከማሆሙ»

«ተልከህ ወደ ሌላ ሀገር በምትሄድበት ጊዜ እነርሱን ምሰል» የተባለውን ቃል አንዳንድ ካህናት ምንም ሳይሳቀቁ «ኩን ከማሆሙ እንዳለ ጳውሎስ» እያሉ ሲጠቅሱ ይሰማሉ። ለምሳሌ ያህል ይህን አልን እንጂ ብዙ ብዙ አሉ።

3. ምእመናን በማያውቁት ቋንቋ ባይጠቅስ የተሻለ ነው። ከጠቀሰም ጥቅሱን በየቦታው እያብራራ ቢሄድ ጥሩ ነው። እንዲያው ዝም ብሎ እየጐለተው ቢሄድ ግን ለምእመናን ከነፍስ ጋር የሚነጋገር ይመስላቸዋል። ይህ ዓይነት ጥቅስ ገበሬ አስደንግጥ ይባላል። ሰባኪው ትምህርቱንም ሆነ ጥቅሱን ምእመናን በሚሰሙት ቋንቋ ያስተላለፈ እንደሆነ ሰሚዎች አሜን ለማለት ይችላሉ።

4. በሰባኪዎች ፊት ራስን ማከክ፣ ጆሮን መኮርኮር፣ አፍንጫን መኅርግር የጭንና የጭንን መካከል ማከክ፣ እነዚህን ሁሉ ማድረግ አይገባም። እነዚህ ድርጊቶች ሁሉ የአካልን መቆሸሽ የሚያመለክቱ ስለሆነ የመጸዳጃ ሰዓትም የተለየ ሰዓት ስላላቸው ከዚህ ጋር ሰባኪው በእግዚአብሔር ፊት እንዳለ አለማሰቡን ስለሚያሳይ በልባቸው ውስጥ ሌላ ሐሳብ ሊፈጠር ስለሚችል።

5. እጅን ያለአግባብ ማወራጨትና መላ አካልን ማውረግረግ ማንዘፍዘፍ አይገባም። ሰሚዎች የሚነገራቸውን ቃል እግዚአብሔር ሳይሆን የሚመለከቱት የሰውየውን ሁኔታ ይሆናል።በርግጥ ሰው በልምዱ በሚናገርበት ጊዜ እጁን ሊሰነዝር ራሱን ሊነቀንቅ ይችላል። እንዲያው በግድ የለሽነት ዛር እንደያዘው በሽተኛ መወግሸት ግን ጤነኛ አያሰኝም።

6. እጅን በኪስ ውስጥ አስገብቶ መናገር አይገባም። እጅን ወደ ኪስ ማስገባት ሁለት ትርጉም አለው፣ አንዱ የትካዜ ሁለተኛው የኩራት ምልክት ነው። ሰባኪው በሚሰብክበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ጨብጦ እግዚአብሔርን በመፍራት በጥን ቃቄ እንጂ በትካዜ ወይም በኩራት መንፈስ ያለ መስሎ እንዳይታይ፣

7. አፍን ዋሻ አስመስሎ ከምእመናን ፊት ማፏሸክ ሰባኪውን ያስነውራል፣ እንቅልፍ ያለቀቀው ወይም የያዘው ያስመስለዋልና። ለራሱ ንቃት የሌለው ሌሎችን ለማን ቃት እንዴት ይችላል? ምእመናንም ይህን ሲያዩ አሁንም ልባቸው ወደ ሌላ ይሄድና ሰባኪውን ወደመንቀፍና ወደማማት ይደርሳሉ። ለጉዳዩ እሱ እንዳላሰበበትና እንዳልተጠ ነቀቀበት ሲያዩ የእነርሱ ልብ ወደ ሌላ ቢባክን ምን ይፈረድባቸዋል።

8. አፍን ወይም አፍንጫን መሸፈን ነጠላ እጆሮ ላይ ማንጠልጠል አይገባም። እነዚህ ሁሉ ሰባኪው በጥብቅ ሊያስብባቸው የሚገቡ የተለመዱ ስሕተቶች ናቸው። ቃል እግዚአብሔር በሚነገርበት ጊዜ እንኳን ተናጋሪው ሰሚዎችም ቢሆኑ እነዚህን ነገሮች ሊፈጽሙ አይገባቸውም። አፍን ወይም አፍንጫን መሸፈን ነጠላን እጆሮ ላይ ማንጠልጠል የኩራትና የትዕቢት ምልክቶች ናቸውና። ሰባኪው

የእግዚአብሔር አስተርጓሚ ሆኖ በምእመናን ፊት መቆሙ ከገባው እነዚህን ስሕተቶች ማስወገድ አያስቸግርም።

# በዕድሜ ደረጃ ከፋፍሎ ማስተማር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ለሚያስተምሩ መምህራን መርጃና መመሪያ:-

የሰንበት ትምህርት ማለት ምእመናን ለጸሎት ለቅዳሴ ወደ ቤተክርስቲያን በሚመጡበት ጊዜ ሕፃናትና ወጣቶች ልጆቻቸው በየዕድሜ ክልላቸው የሚያጠኑበት የሃይማኖትና የሥነሥርዓት ትምህርት ቤት ነው። በመጀመሪያው የክርስትና ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች ለጸሎት ለትምህርትና ለቅዳሴ የሚሰበሰቡት በዕለተ ሰንበት ብቻ ነበር። ያም በድብቅ በግበበ ምድር ውስጥ ነበር። የምእመናን ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ ግን በሰንበት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በዓላት የወንጌል ትምህርት ከቅዳሴ ጋር መሰጠት ተጀመረ። ስንዴ እንጂ እንክርዳድ የሌለበት መንፈሳዊት ዐውደ ቤተክርስቲያንም: ከግበ በምድር ወደ ገጸ ምድር ወጥታ ታየች። በማርቆስ እናት ቤት በኢየሩሳሌም፣ በሌሎችም ምእመናን ቤት፣ ኋላም፣ ግበበ ምድር በሮም የነበረችው ይህች ቤተክርስቲያን፣ የቅዳሴና የጸሎት የማስተማር ሥራዋን ሳታቋርጥ መቀየቷ በቤተክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቧል።

በእነዚህ ከሦስት መቶ ዓመታት በላይ በሚሆኑ የስደት ዘመኖቿ ለምእመናን፣ ለወጣቶችና፣ ለሕፃናት፣ የሚሆኑ ትምህርቶችን በመጠኑም ቢሆን ታስተምር ነበር። /ዮሐ.2÷12-14፣ ኤፌ.6÷1-15፣ ቆላ.3÷20፣ ዘጸ.20÷12 ዘዳ.6÷7/።

ትምህርትን በዕድሜ ደረጃ ከፋፍሎ በማስተማር በኩል በሐዋርያት የማስተማር ዘመን በጣም ያስቸግር ነበር። ምክንያቱም ወላጆችም እንደ ልጆቻቸው፣ ለክርስትና ትምህርት አዲሶች ስለሆኑ ነው። ቤተክርስቲያን እያደገች በሄደች ጊዜ የክርስቲያኖችን ልጆች በሃይማኖትና በሥነሥርዓት ለማሳደግ በዕድሜ ደረጃቸው ከፋፍሎ ለማስተማር አመች ሆኗል።

ከክርስቲያን ቤተሰብ ሳይሆን አዲስ ለሚመጣ አማኝ፣ ከሕፃናት ጋር ሳይሆን ለብቻ የሰንበት ትምህርት ሊሰጠው ይገባል። በአንዳንድ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ለምእመናን የተዘጋጀ የሃይማኖት ትምህርት በክፍል ይሰጣል። ፈተናም ይሰጥበታል።

በእሑድ ትምህርት ቤት ሴቶችና ወንዶች አብረው ስለሚማሩና ስለሚያስተምሩ ለደኅና የተባለው ጉዳይ በክፉ ስም እንዳይበከል ጠንቃቃ ኃላፊ ያስፈልገዋል።

## ክፍል አንድ

ዕድሜያቸው ከ7-10 ለሆኑ ሕፃናት በቅድሚያ የሚሰጡ ትምህርቶች

ሀ. ለጸሎት የሚሆኑ የ ቃል ትምህርቶች
ለ. የመዝሙር ትምህርት
ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የእመቤታችን፣ የመላእክት፣ የሰማዕታትና የቅዱሳን ታሪክ:-

1. ጸሎት፡ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ልጆች:- በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ብለን ማንኛውንም ሥራ በመጀመራችን ማንነታችን ይታወ ቃል:: ስለዚህ በሰንበት ትምህርት ቤት የሚማሩ ወጣቶች ወንዶችም ሆኑ ሴቶች መርሐ ግብር ወጥቶላቸው በመጀመሪያው ክፍላቸው በ ቃል የሚደገሙ ጸሎቶችን በተለመደው ትውፊታችን ማጥናት ይገባቸዋል::

እነዚህም የጸሎት ዓይነቶች:-
ሀ. በስመ አብና፣ ነአኩተከ:-
ለ. አቡነ ዘበሰማያትና በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል
ሐ. ጸሎተ ሃይማኖትና ቅዱስ ንሰግድ
መ. ስብሐት፣ ሰላም ለኪ፣ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም
ሠ. ውዳሴ ማርያምና አንቀጸ ብርሃን
ረ. መልክዐ ማርያምና መልክዐ ኢየሱስ

ከዚህ በተረፈ ቢጨመርበት እንደ ተመቸ ነው:: እስከ ውዳሴ ማርያም ማለት ከሀ እስከ መ ያሉት ጸሎቶች በግእዝና በአማርኛ ሌሎች ግን በግእዝ ብቻ ቢሆን መልካም ነው::

ወጣቶች በዚህ የመጀመሪያ ክፍል የሚቆዩት ለሦስት ዓመት ስለሆነ በቤተክርስቲያናችን ትልቁን የጸሎት መጽሐፍ የዳዊትን መዝሙር ቢማሩ መልካም ነው:: በማንኛውም ትምህርት አንዱን ጨርሰው ሌላውን ሲጀምሩ፣ ፈተና እየተሰጠ ነው::

2. መዝሙር፡ ምሥጢራቸው በጣም ያልረቀቀ፣ የዜማ ስንኛቸው ያልተሰረቀረቀ መዝሙሮችን በዚህ ክፍለ ትምህርት ሊያጠኑ ይገባል፣ እነዚህ መዝሙሮች በ ቃል የሚዘመሩና፣ በከበሮና በጸናጽል የሚሸበሸቡ ቢሆኑ አይከፋም:: ከዚህ በተረፈ ግን ኦርጋን፣ ፒያኖ፣ ጊታርና የመሳሰለውንም የስሜት መቀስቀሻ መሣሪያ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መዝሙር ውስጥ ማዳቀል የመዝሙሮቻችንን ስንኝና ቃና መልኩንም ጣዕሙንም ይበርዘዋል:: ከዚህ በበለጠ ደግሞ እኛንም ወጣቶቹንም የሌሎቹ ቤተሰብ ያስመስላል፣ የእሑድ ትምህርት ዓላማው ወጣቶች አቅጣጫቸውን እንዳይስቱ፣ ያባቶቻቸውን ምልክት እንዳያጡ ስለሆነ በመዝሙሩም ጥን ቃቄ ያስፈልጋል:: ያንንም ለመምሰል መኳኋት ካለማ በሰንበት ትምህርት ቤት መማር ለምን ያስፈልግ ነበር-

የመዝሙሮቹ ምሥጢር በተቻለ መጠን ሀገርን፣ ሃይማኖትንና ነፃነትን የሚያስተባብር ቢሆን በጣም ጥሩ ነው።

ወጣቶቹ በዜማ ትምህርት ጉሮሯቸው ያልታሸ ስለሆነ የተራቀቀ ዜማ ለማዜም ያስቸግራቸዋል። በዚህም ምክንያት ማጥናቱን ይተውታል። ይህ እንዳይሆን ለልጆቹ ድምጽ በሚስማማ ዜማ መዝሙሮች ቢቀርቡ ልጆቹ ደስ እያላቸው ያጠናሉ።

መዝሙሮች በግእዝም ቢሆን በአማርኛ ከተጠኑ በኋላ ታሪካቸውን ሰፋ አድርጎ ማስረዳት ይገባል።

3. የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፡ በዚህ ክፍለ ትምህርት ለወጣቶቹ የሚሰጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በእነማን እንደተጻፈ፣ መቼ እንደተጻፈ፣ ለምን እንደተጻፈ መግለጥ፣ በሰፊ ሐተታ አይደለም። ታሪኮችን ለቅሞ አውጥቶ ረጅሙን አሳጥሮ በአካባቢው አገላለጥ፣ በማያሰለች ሁኔታ ማስተማር ነው።

ለምሳሌ፦ የአዳምንና የሔዋንን ተፈጥሮ

- በጠቅላላው የሥነ ፍጥረትን አቀማመጥ
- የኖህንና የጥፋት ውኃን
- የአብርሃምንና የይስሐቅን ሁኔታ፦ አብርሃም ለእግዚአብሔር ይስሐቅ ለአብርሃም መታዘዙን በመግለጥ ልጆች ለወላጆች ቢታዘዙ እግዚአብሔር የሚባርካቸው ከሞት የሚያድናቸው መሆኑን በታሪኩ መደምደሚያ ላይ ማቅረብ፣
- የሳሙኤልን አስተዳደግ
- የሙሴን አስተዳደግና በኋላም ያሳየውን ቆራጥ እርምጃ በማስረዳት የወጣቶች ልጆችን የመስማት ፍላጎት ለማግረክ ይችላል። በዚህ ብቻ ሳይወሰን አስተማሪው ወደ አዲስ ኪዳን ታሪክም ገብቶ፣
- የገብርኤልን ብሥራት
- የጌታን ልደት፣
- የጌታን ስደት፣
- የጌታን ጥምቀት፣
- የጌታን ማስተማርና በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞቱን፣ ትንሣኤውንና ዕርገቱን፣ ዳግም ምጽአቱን፣ አጠር፣ ጣፈጥ፣ ባለ ሁኔታ ማስተማር ለልጆቹ ይጠቅማል።

የወጣቶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት እንዲስፋፋና ወደፊትም በሚያስተምሩበት ጊዜ እንዲረዳቸው የሐዋርያትን መጠራት፣ የቅዱስ ጳውሎስንም መማረክ፣ በሐዋርያት ሥራና፣ በመልእክታት ያሉትን ታሪኮች ቢነግሯቸው ልጆቹ ሰምተው አይጠግቡም።

የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ታሪክ፦ የሐናና የኢያቄም ልጅ መሆኗን፣ በሥዕለት መወለዷንና በድንግልና በብሥራተ መልአክ አምላክን መውለዷን፣ ከነልጇ ስትሰደድ የደረሰባትን መከራ፣ በጌታ

የማስተማር ጊዜ ሁሉ ከእሱ አለመለየቷን፣ ከመስቀሉም ሥር መገኘቷን፣ እረፍቷን፣ ፍልሰቷን ያደረገችውን ታምራት፣ አማላጅነቷን፣ ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች በዚህ ክፍል ትምህርት ማስተማር ይገባል፡፡

ስለ መላእክትም ተፈጥሮና ተራዳኢነት፣ የሰውን ልጆች ለመርዳት የሚላኩ መሆናቸውን፣ ለምሳሌ፡- የቅዱስ ሚካኤል፣ የቅዱስ ገብርኤልና የሠለስቱ ደቂቅን፣ ሌሎችንም ታሪኮች በመላእክት ድርሳኖች የተጻፉትን በመጽሐፍ ቅዱስም ያሉትን የመላእክት ታሪኮች ለቅሞ አጠናቅሮ፣ አማላጅነታቸውንም ማስጠናት፡፡

የሰማዕታት ታሪክ ለልጆች ስሜትን የሚቀሰቅስ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ በብሉይ ኪ... ለስቱ ደቂቅና የዳንኤል በአዲስ ኪዳን የእስጢፋኖስ፣ የቅዱስ ቂርቆስና የቅዱስ ጊዮርጊስ የሌሎችም ሰማዕታት ታሪክ ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ደማቸውን ማፍሰሳቸውንና አማላጅነታቸውን አጣጥሞ ቢተርክላቸው ወጣቶቹ እነሱን ለመምሰል ይመኛሉ፡፡

ከዓለም ጣዕም ተለይተው ገዳም አቅንተው አንድነት መሥርተው፣ በምንኩስና በቅድስና ወንጌልን በማስተማር ሕይወታቸውን ለፈጣሪያቸው ወደው ያስረከቡ ቅዱሳን፣ የእነ አቡነ ተክለሃይማኖትን፣ የእነ አቡነ ዜና ማርቆስን፣ የእነ አቡነ ፊልጶስን፣ የእነ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ታሪክ ታምራትና አማላጅነታቸውን ለወጣቶች በዚህ የሦስት ዓመት ጊዜ ማስተማር ለቤተክርስቲያናችን ትልቅ ምርት ነው፡፡

በዚህ የመጀመሪያ ክፍል ትምህርት የሚመዘገቡ ወጣቶች ልጆች በአስተማሪያቸው መሪነት በየሳምንቱ እሑድ ከተቻለም በሌሎች በዓላት በቤተክርስቲያን በሠልፍ ቁመው አስቀድሰው እንዲቆርቡ ለዚሁም አስተማሪያቸው ራሱ ቀድሶ ማቁረብ አለበት፡፡ እሱ ባልቀደሰ ጊዜ ደግሞ አስቀድሞ ቆርቦ ሥርዓቱን ማሳየት ይገባል፡፡

ለሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪዎች አሁንም በድጋሚ የምናሳስበው፣ እነዚህ ትምህርቶች ተዘጋጅተው መስጠት ብቻ ሳይሆን በየጊዜው ቴስትና ፈተና እየተደረገ፣ የሚሰጠውን ትምህርት በደንብ የሚከታተሉትን ልጆችና የማይከታተሉትን ለይተው እንዲያውቁ ነው፡፡ ፈተና ወይም ቴስት ሳይሰጥበት አባላት እያሉ ልጆችን በመመዝገብ በየሳምንቱ ሰባኪዎችን በመጋበዝ የሚሰጠው ትምህርት ግን ስብከት እንጂ የእሑድ ትምህርት አይባልም፡፡ በዚህም ዓይነት አሠራር ብዙ ዓመት ተሞክሮ ውጤት ሳይሰጥ ቀርቷል፡፡

በጸሎት በቅዳሴ ጊዜ ሕፃናት እግራቸውን ገጥመው እጃቸውን አመሳቅለው እንዲቆሙ የሥነ ሥርዓት ትምህርት የሚሰጠውም በዚህ ዕድሜ ነው፡፡ በኋላ ግን ያስቸግራል፡፡

## ክፍል ሁለት

### ዕድሜያቸው ከ10-15 ለደረሱ ልጆች የሚሰጥ ትምህርት

በክፍል አንድ በየጊዜው የተሰጣቸውን ትምህርት በፈተና አልፈው በዕድሜ ደረጃቸው ወደ ሁለተኛው ክፍል ትምህርት ሲተላለፉ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ወጣቶች የሚሰጥ ትምህርት፡-

ሀ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣
ለ. ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣
ሐ. ግእዝ፣
መ. ቅዳሴ፣

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ስንል በጽሑፍ ያለውን ሁሉ በቃል ማጥናት አይደለም፡- ወጣቱ እምነቱንና ማንነቱን ጠብቆ እንዲኖር በቀላሉ የሚያዙ ነጥቦችን ከመጽሐፍ ጨምቆ በማውጣት ማስተማር ነው፡፡

<u>ለምሳሌ</u>፡-

1. ኢትዮጵያ አሁን ያለንባት አገር መሆኗን ከነአስረጇ ው፡
2. ከክርስትና በፊት ምን እምነት እንደነበረ
3. ክርስትናን መቼ ተቀበለች፣
4. በክርስቲያንነቷ ምን ምን ችግር እንደ ደረሰባት፣
5. የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንና የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት
6. ክርስቲያን ያልሆኑ ወራሪዎች አባቶቻችንን እያረዱ መግደላቸውን
7. ክርስቲያኖች ነን ባዮችም ቤተክርስቲያናችንን እያቃጠሉ ምእመናን አባቶቻችንን፣ ገዳማውያን መነኮሳትን፣ ሊቃ ጳጳሳትን እያረዱ መፍጀታቸውን፣ አሁንም ወዳጅ መስለው በገንዘባቸው ተመክተው ቤተክርስቲያናችንን በመውረር ላይ መሆናቸውን፡- ይህንና የመሳሰለውንም በማስረዳት፣ መምህሩ ካስተማራቸው ወጣቶች በወራሪ የጠፉብንንና የተወሰዱብንን ቅርሶች፣ ሐውልቶች መጻሕፍትና ሌሎችንም ለመተካትና ለማስመለስ፣ የተቃጠሉብንን ቅርሶች፣ ሐውልቶች መጻሕፍትና ሌሎችንም ለመተካትና ለማስመለስ፣ የተቃጠሉብንን አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት እንደገና ለመሥራት፣ የተገደሉብንን ጳጳሳት፣ ካህናትና ምእመናን፣ ጀግኖች አርበኞችና አባቶች፣ ተተኪ ለመሆን፡- እዚያው በትምህርቱ ላይ እንዳሉ ይወስናሉ፡፡ ከዚህም ጋር የቤተክርስቲያናችንን በዓላት፣ አጽዋማት ልዩ ልዩ ቀኖናዎችን ሁሉ ከዚሁ ጋር አብረው ይማራሉ፡፡

በእነዚህ ጥናቶች ውስጥ ማድረግ የሚገባው ጥንቃቄ ቢኖር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያለው ሥርዓት ሁሉ፣ በቀኖና ሐዋርያት በቀኖና ሊቃውንት የታወቀና የጸደቀ ሲበረክትም የቀና እንጂ ልማዳዊ አለመሆኑን ለወጣቶች ከመግለጡ ላይ ነው፡፡

አንዳንድ አስተማሪዎች የራሳቸውን መራቀቅ ለማሳወቅ ይሁን ወይም የማስተማር ልምድ ስለሌላቸው እንደሆነ አይታወቅም ለተማሪዎቹ የቤተክርስቲያናችንን ትምህርት ሳያስጨብጡ እዚያም እዚያም በማሳየት የልጆቹን ትኩስ አእምሮ እንዲጠራጠር ያደርጉታል፤ ልቦናቸውንም ይበትኑታል:: በዚህም ምክንያት ልጆቹ የራሳቸውን እየናቁ ወደ ሌላው ይመለከታሉ፣ ያም ልክ ነው፣ ያም ልክ ነው ከሚል ዩኒቨርሳሊዝም፣ ከሚባል ስሕተት ላይ ይወድቃሉ:: ይህ ስሕተት እንዳይፈጸም የሰንበት መምህራን በሥራው ከመመደባቸው በፊት፣ ምን እንደሚያስተምሩ፣ ለማን እንደሚያስተምሩ፣ እንዴት እንደሚያስተምሩ፣ በየዓመቱ ሴሚናር እየተደረገ መማር አለባቸው:: ስብከትና የሰንበት ትምህርት አንድ አይደለም ብለናል:: የራስን ሳያውቁ የሌላውን የሚያወሩ መምህራን በታኞች እንጅ አስተማሪዎች ባይባሉ ይሻላል:: በከፍተኛም ሆነ በዝቅተኛ ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ የሚሰጠው የአዎንታ ትምህርት ነው:: ወጣቱ በቲዎሎጂ ሲበስል ደግሞ የራሱን ከሌላው ጋር የሚያወዳድርበት ትምህርት ይሰጠዋል፣ ይማረዋል፣ ያጠናዋል:: እስካሁንም በሰንበት ትምህርት ቤታችን ለምስክርነት የሚበቁ ሰዎችን ማፍራት ያልቻልነው የራሳቸውን /የራሳችንን/ ሳናስጨብጣቸው የሌላውን ሁሉ እያሳየናቸው ነው::

2. ጠቅላላ የቤተክርስቲያን ታሪክ በዚህ ክፍለ ትምህርት ለወጣቶች ይሰጣል:: ይህም ከጌታ ልደት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለውን የክርስትና ሃይማኖት ጉዞ ነው:: ይህንን ትምህርት ለሰንበት ተማሪዎች በክፍል ለማቅረብ እንደ ሌሎቹ ትምህርቶች መጭመቅና ነጥቦችን መምረጥ ያስፈልጋል:: ይኸውም:-

1. የክርስትና ሃይማኖት ማለት የአምላክ መገለጥ መሆኑን፣
2. አምላክ ከመገለጡ ማለት:- ሰው ከመሆኑ በፊት ሰዎች ከአምላክ ጋር የነበራቸው ግንኙነት እንዴት እንደነበረ፣
3. የአምላክ ሰው መሆን ለምን እንዳስፈለገ፣
4. ከልደት እስከ ዕርገት የተፈጸሙትን ድርጊቶች፣
5. ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ከሮማ ቄሳሮችና ከቢጽ ሐሳውያን ጋር ያደረጉትን ተጋድሎና የካታኮምብን ኑሮ፣
6. ከኔሮን ቄሳር ጀምሮ ቤተክርስቲያንን ያሳደዱ ቄሳሮችን ግፍና የሰማዕታትን አሟሟት፣
7. በቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ቤተክርስቲያን ከካታኮምብ ወደ ገጸ ምድር መውጣቷን፣
8. ቤተክርስቲያናችን የምትቀበላቸውን የሦስቱን ጉባኤዎች ውሳኔዎች፣ እነሱም፣

   የጉባኤ ኒቅያን 325 ዓ.ም.
   የጉባኤ ቁስጥንጥንያን 381 ዓ.ም.
   የጉባኤ ኤፌሶን 431 ዓ.ም.

9. ቤተክርስቲያናችን የምታወግዘውን የኬልቄዶንን ጉባኤ ውሳኔ 451 ዓ.ም.

10. ከኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ በኋላ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት በመለካውያን ካህናትና ነገሥታት ሲሰደድ መኖሩን፣

11. ስለ እስላሞች መነሣትና በክርስቲያኖች መካከል የነበረው ብጥብጥ መንገድ የከፈተላቸው መሆኑን፣ ኋላም ገናና ነኝ ይል የነበረው የሮማ መንግሥት በእግዚአብሔር ኃይል መውደቁንና፣ መለካውያንም እርስ በርሳቸው መለያየታቸውን፣ በዚህ ሁሉ የታሪክ ጉዞ ውስጥ ቤተክርስቲያናችን የማንንም እምነትና ባሕል ከራሷ እምነትና ባሕል ጋር ሳትቀላቅል መኖሯን፣ ለወደፊትም ወጣቶች ይህን ከተማሩ በኋላ በአባቶች ተተክተው ታሪኳን የሚመሠክሩ መሆን የሚገባቸው መሆኑን በሰፊው ያስተምራል።

ግእዝ፡-

ይህ ክፍል ትምህርት የአምስት ዓመት ጊዜ ስላለው ለሃይማኖት ትምህርት ማዕከል የሆኑትን ነጥቦች ሁሉ ያጠቃልላል። የግእዝ ቋንቋ የቤተክርስቲያናችን የአምልኮት መግለጫ ቋንቋ ነው። በቤተክርስቲያን የሚሰጠው ይልቁንም በዜማ የሚሰጠው አገልግሎት በግእዝ ነው። ስለዚህ ወጣቶች በሰንበት ትምህርት ቤት በዚህ ዕድሜያቸው የግእዝን ቋንቋ እንዲያጠኑ መምህሩ መርሐ ግብር ያወጣል።

የግእዝ ቋንቋ ስንል ዘይቤውን እንጂ ቅኔውን አይደለም። ወጣቶች በዚህ ዕድሜያቸው በመደበኛው የመንግሥት ትምህርት የአማርኛ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሰዋሰው ማጥናት ስለሚጀምሩ መምህሩ ቃላትን ከ ቃላት፣ ዐረፍተ ነገርን ከዐረፍተ ነገር፣ ሰዋሰውን ከሰዋሰው ከዚያ ጋር እያነፃፀረ ቢነግራቸው በቀላሉ ይይዙታል። በግእዝና በወጣቶች መካከል ያለውን አለመግባባት በዚህ ዓይነት በመፍታት ፊንታ መጻሕፍትን ሁሉ ወደ አማርኛ ለመመለስ መሞከር ብዙ ጊዜ ከመውሰዱም ሌላ የሃይማኖት ቃላትም ተገቢ ብሂላቸውን ያጣሉ። ነገር ግን ወጣቱንና ግእዝን የሚያገናኝ ድልድይ ሳይሠሩ ነፍሱ ትሰማዋለች በማለት የሚሰጠው አገልግሎት የወጣቶቹን መንፈሳዊ ፍላጐት ያቀጭጨዋል።

ወጣት ተማሪዎችም የግእዝን ቋንቋ በዚህ ዓይነት እንዲያስተምራቸው የሰንበት መምህራቸውን ሊያነ ቃቁት ይገባል። እስራኤላዊ ሆኖ የዕብራይስጥ፣ የግሪክ ሰው ሁኖ ጽርዕ፣ ሮማዊ ሆኖ ላቲን፣ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ግእዝ አለማወቅ፣ ነኝ ለማለት ያሳፍራልና።

የግእዝ ቅኔ ለማጥናት ግን ሰፋ ያለ ጊዜ ስለሚጠይቅ ጊዜና ፍላጐት ያላቸው ወጣቶች የሰንበት ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የግእዝ ቅኔ ቢማሩ ብዙ ሳይደክሙ በቀላሉ ሊይዙት ይችላሉ።

## 4. ቅዳሴ

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ወጣቶች የሰንበት ትምህርታቸውን የሚማሩት በቤተክርስቲያናችን ሕግ መሠረት ነው:: የቤተክርስቲያናችንንም ችግር ለመሸፈን ነው:: ስለዚህ በሰንበት ትምህርታቸው የቅዳሴ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል:: በመጀመሪያ የዲቁናውን አባባል /ግብረ ዲቁና/ ማጥናት ያስፈልጋል:: ወጣት ወንዶች በዲቁና ገብተው ሲቀድሱ ወጣት ሴቶች ተሰጥዖ ሲመልሱ ደስ ያሰኛሉና:: ከነዚህም ውስጥ የእግዚአብሔር ጥሪ የደረሰው ወጣት በቅስና በምንኩስና በጵጵስና እግዚአብሔርን ስለሚያገለግል ይህ መሠረታዊ የቅዳሴ ትምህርት በሰንበት ትምህርት ቤት መሰጠቱ በጣም ይጠቅማል::

የእግዚአብሔር ጥሪ የደረሳቸው ሴት ወጣቶችም መንነው መንኩሰው በገዳማቸው፣ በትምህርት ቤታቸው ለሚያሳድጓቸው ሕጻናት መሪዎች አስተማሪዎች ይሆናሉ:: ወደ ትዳርም ቢገቡ የሚወልዷቸውን ሕፃናት ያስተምሯቸዋል::

የቅዳሴ ትምህርት ለወጣቶች የሚሰጠው ዜማው ብቻ አይደለም ምሥጢሩንም ነው:: ለምሳሌ፣ ቅዳሴያችን ሦስት ክፍል አለው፣

1. የዝግጅት፣ /አሐዱ እስከሚባልበት ድረስ የሚደረገው/ ግብአተ መንጦላዕት፣
2. የትምህርት፣ /አሐዱ ከተባለ በኋላ መልእክታትና ወንጌል የሚነበቡበት/
3. የቅዳሴ ፍሬ ቅዳሴ፤ በእነዚህ ሦስት ክፍሎች የሚደርሱ የጸሎት ዓይነቶች በዝርዝር ለተማሪዎቹ እንዲነገራቸው ያስፈልጋል:: ከዚህም ጋር በትምህርት ቤቱ ከሚማሩ ወጣቶች የሥዕል ችሎታ ያለው ካለ ያለዚያም አስተማሪው ራሱ ጻሕሉን፣ ጽዋውን፣ ዕርፈ መስቀሉን፣ ማኅተሙን፣ መሶበ ወርቁንና ማኅፈዳቱን፣ ጽናውን፣ ሙዳዩን ዕጣኑንና ሌሎችንም የቤተክርስቲያን ንዋያት ሁሉ በሥዕል እያሳለ ከነስማቸው ከነአገልግሎታቸው ማስጠናት ይገባል:: ዲያቆኑ መስቀል ይዞ ሲሰብክ ሲያሳጥን፣ ቄሱ ጥና ይዞ ከዲያቆኑ ጋር እየዞረ ሲያጥን የሚያሳይ ሥዕል፣ ከንዋያተ ቅድሳቱ ጋር በየገጹ እየተሳለ ከማስተማሪያው ዝግጅት ጋር ቢቀርብ ደስ ያሰኛል:: ከቅዳሴው ጋር ሌላው የማይረሳው ትምህርት አስቀድሶ መቁረብ ነው:: በቅዳሴ ጊዜ ሕዋሶቻቸው ሁሉ ይማራሉ:: የሸኩራውን፣ የ ቃጭሉንና የደወሉን ድምፅ በጆሮዋቸው ይሰማሉ፤ የዕጣኑን መዐዛ ባፍንጫቸው ያሸታሉ፤ ሥዕሉን መስቀሉን በእጃቸው ይዳስሳሉ፤ ይሳለሟቸዋልም፤ ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ፤ የቅዳሴ ጸበል ይጠጣሉ:: በመጀመሪያው ክፍል ትምህርት እንደ ተነገረው ወደ ቤተክርስቲያን ለጸሎት ለቅዳሴ ሲገቡ ቀጥ ብለው፣ እግራቸውን ገጥመው፣ እጃቸውን አመሳቅለው፣ ግራና ቀኝ ሳይ ቃብዙ ሳይጋፉ፣ የሚሰጣቸውን ሁሉ በሥነ ሥርዓት እንዲቀበሉ ጸሎቱንም በሥነ ሥርዓት እንዲከታተሉ አስተማሪው ሁል ጊዜ መምከር ይገባዋል::

# ክፍል ሦስት

## ዕድሜያቸው ከ15-20 ለሆኑ ወጣቶች የሚሰጥ ትምህርት

በሁለተኛው ክፍለ ትምህርት ለአምስት አመታት በሚገባ ተከታትለው በፈተና ያለፉ፣ ወጣቶች ወደ ሦስተኛው ክፍለ ትምህርት ያልፋሉ::

በዚህ ዕድሜያቸው የሕጻንነታቸውን ወራት የሚደመድሙበት ስለሆነ አእምሯቸውም ይበስላል:: በመንግሥት ትምህርት ቤትም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ስለሆኑ ከአእምሯቸው ጋር አብሮ የሚሄድ ትምህርት በሚገባ ተዘጋጅቶ ሊቀርብላቸው ይገባል:: በሰንበት ትምህርት ቤት አሁን ሊማሩ የሚገባቸው የሚከተሉትን ሦስት ትምህርቶች ነው::

ሀ. ዶግማ፣
ለ. የስብከት ዘዴ፣
ሐ. የማኅበራዊ ኑሮ ትምህርት፣

በሚከተሉት አምስት ዓመታት እነዚህን ሦስት ትምህርቶት በሚገባ ያጠናቅቁ፣ ወደ ታችም ያሉትን ክፍሎች ለመምህሩ ረዳት እየሆኑ ያስተምራሉ::

ሀ. እዚህ ላይ የሚሰጠው የዶግማ ትምህርት፣

1. ስለ እግዚአብሔር ህልውናና የሥነ ፍጥረት አስገኝነት፣
2. ስለ ሰው ተፈጥሮና ስሕተት፣
3. በአንድ አምላክ ስለማመን፣
4. ስለ ሥላሴ፣ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ
5. ስለ አምላክ ሰው መሆንና ስለ ሰው አምላክ መሆን፣
6. ስለ አንድ አካል አንድ ባሕርይ እምነት፣
7. ስለ እመቤታችን ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና፣
8. ስለ እመቤታችን አማላጅነት፣
9. ስለመላእክት ተፈጥሮ፣
10. ስለ መላእክት አማላጅነት፣ ስለ ቅዱሳን አማላጅነት፣
11. ስለ ሰይጣን ተፈጥሮና የሰው ልጅ ጠላትነት፣
12. ስለ ትንሣኤ ሙታን፣
13. ስለ መጨረሻው ፍርድ፣ እነዚህንና የመሳሰሉትንም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አባቶች አባባል ካስተማሯቸው በኋላ የራሳቸውን እምነት ማወቃቸውን ሲያረጋግጡ፥ እነዚህን ትምህርቶች ለመለወጥና የራሳቸውንም አስተሳሰብ ለመጨመር የቋጡ መናፍቃን ዱሮም ሆነ ዛሬ መኖራቸውን፣ ስሕተታቸው እየተገለጠ ባቸው ከቤተክርስቲያንም መወገዳቸውን በጥንቃቄ ሊያስተምር ይገባዋል:: ለምሳሌ:-

    1. የሰባልዮስ፣ አባባልና መወገዙን፣
    2. የ መቅዶንዮስን አባባልና መወገዙን

3. የአርዮስን አባባልና መወገዙን፣
4. የመሐመድንና የጆሆቫው ያንን፣
5. የንስጥሮስን ስሕተት፣
6. የአውጣኪንን የቱሳሔ ትምህርት፣
7. የልዮን ቀዳማዊን ጦማርና የኬልቄዶንን ስሕተት።

የዶግማ ትምህርት ለማንኛውም ተማሪ ጠቃሚ የሚሆነው በፊት የራሱን እምነት ጠንቅቆ ከተረዳ በኋላ የሌሎቹን ሲሰማ ነው፤ ነገር ግን በፊት የራሱን እምነት ሳያጠና የሌሎቹን አባባል የነገሩት እንደሆነ ብዙ ጥርጣሬን ሊፈጥርበት ስለሚችል ይህን እንዲያስቡበት አሁንም በድጋሚ ለሰንበት ት/ቤት መምህራን አደራ እንላለን።

## ሰ. የስብከት ዘዴ ትምህርት፣

አሁን ወጣቶቹ የቤተክርስቲያንን የውስጥ ሕይወት በሚገባ ስላወቁ፣ ባደባባይ ማስተማር ብዙ ችግር አይፈጥርባቸውም። የሚያስፈልጋቸው ነገር ቢኖር ለስብከት የተደነገጉትን ሕጎች ማጥናት ነው።

ከዚህም ጋር ልጆች ድራማ ማየት ደስ ስለሚላቸው ትምህርቱንና ድራማውን ከልብ ወለድም ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንጭ እየለቀሙ ድራማ እየሠሩ ቢያሳዩ ጥሩ ነው።

<u>ለምሳሌ፦</u>

በሉቃስ ወንጌል ሉቃ15÷11-32 ታሪኩ የተመዘገበውን አባካኝ ወጣት ሁኔታ፣ አሁንም በዚህ ወንጌል የተመዘገበውን /ሉቃ16÷19-31/ ጨካኝ ባለጠጋ ሁኔታ፣ ሌሎችንም በምሳሌ ከነቢያትም ከጌታም ከሐዋርያትም ከሊቃውንትም የተሰጡትን ትምህርቶች በድራማ ቢያቀርቧቸው ወጣቶችን ብቻ ሳይሆን ወላጆችንም ከጥፋት ያድናሉ።

ከላይ እንደገለጥነው ለትምህርትና ለምክር ምሳሌ የሚሆኑ ነጥቦችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ለቅሞ አውጥቶ በድራማ ለወጣቶችም ሆነ ለምእመናን ማቅረብ ትልቅ የማስተማሪያ ዘዴ ነው። ነገር ግን፣ በጌታና በእመቤታችን የተፈጸሙ ድርጊቶችን በድራማ ማቅረብ ክልክል ነው።

<u>ለምሳሌ፦</u>

በድንግልና መውለድ፣
በድንግልና መወለድ፣
በመስቀል መሰቀል፣
ቀነዉኒ ማለት

ይህንና ይህን የመሳሰሉትን ካንድ ጊዜ በቀር ያልተፈጸሙትን ነገሮች በድራማ ማቅረብ ከስሕተትም አልፎ ጽርፈት ነው። ባጠቃይ በጌታ የተፈጸሙ ታምራት ሁሉ ለምልክት የተደረጉ የእሱ የብቻው ምልክቶች ስለሆኑ በድራማ አይቀርቡም።

በድራማ መቅረብ የሚገባቸውን ተናግረናል፤ ይህን ሥሩ፥ ይህን አትሥሩ፤ ይህን ምሰሉ፥ ይህን አትምሰሉ ለማለት ለምክርና ለተግሣጽ የሚሆኑ ብዙ ነጥቦች ስላሉ አስተማሪው እነዚህን ማሳወቅ አለበት።

## ሐ. የማኅበራዊ ሥራ ትምህርት

ከዚህ ክፍል ትምህርት በኋላ ወጣቶቹ ትዳር ይዘው ቤተሰብ ወደማስተዳደር፣ መንኩሰው ገዳማቸውን ወደ ማገልገልና ወንጌልን እያስተማሩ ወደ ምእመናን የሚሄዱ ስለሆኑ ስለ ማኅበራዊ ኑሮ ሥራ መማር ይጠቅማል። የማኅበራዊ ሥራ ስንል፣ አመራርንም ያጠቃልላል። በዚህ ክፍል ትምህርት ወጣቶቹ ሁለት ኃላፊነት አለባቸው፣

1. ስለ ራሳቸው ቤተሰብ፣
2. ስለ አካባቢያቸው፣

በዚህ ክፍል ትምህርት ማኅበራዊ ሥራ ማለት በቃል የሚሰጠውን ትምህርት በሥራ ማሳየት ማለት ነው። መርሐ ግብር አውጥቶ መምህሩ ምእመናን ወዳሉበት ሰፈር ተማሪዎቹን ይዟቸው ይሄዳል። በዚህም እንደ አካባቢው ችግር ውኃ እንደሆነ የሚቸግረው የውኃ ጉድጓድ በመቆፈር፣ መጸዳጃም እንደሆነ የመጸዳጃን ጥቅም በማስረዳት መጸዳጃ በማዘጋጀት በአጠቃላይ የሕዝቡን ችግር ለማቃለል በሚደረገው ሁሉ የቤተክርስቲያንን ተሳትፎ ለመግለጥ የሚደረግ ነው። ሃይማኖታቸውን ተምረው አውቀው ወንጌልን በማስተማር ወደ ምእመናን ልቡና ለመቅረብ የሚቻለው ችግራቸውን ለማቃለል ትብብር ሲደረግላቸው ነው።

በትዳር የሚወሰኑ ወጣቶች የማኅበራዊ ሥራ ልምምድ ካሁኑ ካላቸው በቤተሰባቸውም ሆነ በአካባቢያቸው ዘንድ መወደድና ታማኝነት ይኖራቸዋል። የሰፈር አባት ይሆናሉ። ማናቸውም ችግር የደረሰበት ሁሉ ወደነሱ ይመጣል። የሚያምን ከሆነ የእምነቱን በጎ ሥራ ሲያይ ይጠነክርለታል። የማያምን ከሆነም በጎ ሥራ በማየት ወደ እምነት ይሳባል።

ሕገ መላእክትን መርጠው በገዳም ቢቀመጡም የሙት ልጆች የሚያድጉበት፣ አረጋውያንን የሚጦሩበት፣ የበሽተኛ ማስታመሚያ ቤተ መድኃኒትና የድሆች ልጆች የሚማሩበት ት/ቤት በማቋቋም፣ አመራሩንም በማሳመር ብዙ አገልግሎት ለቤተክርስቲያናችን ለማበርከት ይችላሉ የምእመናንም ቁጥር እያደገ ይሄዳል።

በሀገራችን ብዙ ገዳማት ቢኖሩም መነኮሳቱ ከአካባቢያቸው ችግረኛ ሕዝብ ጋር በማኅበራዊ ሥራ ስለማይገናኙ ሕዝቡ የገዳማት መኖር አለመኖር የሚጠቅም ወይም የሚጐዳ መሆኑን አያውቅም። በማኅበራዊ ሥራ የሠለጠኑ ካህናት፣ መነኮሳትና መነኮሳይያት ባሉባቸው አገሮች ግን ገዳማትን የሕይወታቸው ማዕከል አድርገው ይመለከቷቸዋል። ሰውን በቀላሉ ለማሳመን ከተፈለገ በማኅበራዊ ሥራ የተደገፈ ትምህርት ያስፈልጋል።

የወጣቶችም የሰንበት ትምህርት ጥቅሙ ይህ ነው።